የሰላም ሚኒስቴር
MINISTRY OF PEACE

# የ2015 በጀት ዓመት ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት፤

ሐምሌ 2015 ዓ.ም

አዲስ አበባ

**መግቢያ፤**

የሰላም ሚኒስቴር በአገራችን የተጀመረውን ለውጥ ውጤታማ፣ ዘላቂና ተቋማዊ ለማድረግ የአስፈጻሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1263/2014 የተቋቋመ የፌዴራል መንግሥት አስፈጻሚ ተቋም ነው፡፡

ሚኒስቴር መ/ቤቱ ሲቋቋም ከተሰጡት ተልዕኮዎች ዋና ዋናዎቹ በሃገሪቱ ዘላቂና አስተማማኝ ሰላም ማስፈን፣ አገራዊ መግባባትና አንድነትን ማጎልበት፣ ፌዴራሊዝምን ማጠናከር እንዲሁም ግጭት መቀነስ እና ከሚመለከታቸው መንግስታዊ፣ መንግስታዊ ካልሆኑ አካላት እና ከዜጎች ጋር በአጋርነትና ትብብር መስራት ላይ ትኩረት ያደርጋል፡፡ በዚህ መነሻነት ሚኒስቴር መ/ቤቱ የተቋቋመበትን ዘርፈ ብዙ ተልዕኮ ለመወጣት እንዲቻል የ2015 በጀት ዓመት ዕቅድ አቅዶ ከተቋሙ አመራርና ፈጻሚዎች ጋር በዕቅዱ ዙሪያ የጋራ መግባባት በመፍጠር ወደ ተግባር ተገብቷል፡፡

በዚህ መሰረት ሪፖርቱ በአራት ክፍሎች የተደራጀ ሲሆን በክፍል አንድ ተቋማዊ የማስፈጸም አቅም፣ የሀብት አጠቃቀም እና የአገልግሎት አሰጣጥ አሰራር ማጎልበት፤ በክፍል ሁለት በቁልፍ አመላካቾች ላይ የተመሰረተ ዕቅድ አፈጻጸም ትንተና፤ በክፍል ሶስት በአፈጻጸም ሂደት ያጋጠሙ ተግዳሮቶችና የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች፤ በክፍል አራት ማጠቃለያና የቀጣይ ትኩረት አቅጣጫዎች፤ በክፍል አምስት የአፈጻጸም ማትሪክስ፤ ተካቶ የተቋሙ የ2015 በጀት ዓመት ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

**ተቋማዊ ርዕይ፣ ተልዕኮ እና እሴቶች፣**

**ርዕይ**

ሰላም፣ የዜግነት ክብር እና ህብረ-ብሄራዊ አንድነት አድጎ ማየት፣

**ተልዕኮ**

የዜጋውን፣ የቤተሰብንና የማህበረሰብን ሰላምን በማስጠበቅና በማስከበር፣ ብሔራዊ መግባባትንና አገራዊ አንድነትን በማሳደግ፣ የፌዴራል ስርዓቱን በማጠናከር፣ በቀድሞ ተገኝነት ግጭትን በማስተዳደር፣ ቀጣናዊና አህጉራዊ ትብብርና ትስስርን በማጎልበት እንዲሁም ተቋማዊነትን በማሳደግ ሁለንተናዊና ዘላቂ ሰላም መገንባት ነው፡፡

**እሴቶች**

***ሀገር-ወዳድነት፡-*** ለህብረ-ብሔራዊ አንድነት በፅናት የሚቆም፣ ማህበረሰባዊ ሀብቶችን እና ብሔራዊ ጥቅሞችን የሚያከብር፣ የሚንከባከብና የሚያሳድግ፣ ለህዝብ እና ለሀገር ታማኝ፣

**ሰላማዊነት፡-** የራሱን ውስጠ ሰላም ያረጋገጠ፣ ለግለሰብ፣ ለቤተሰብና ለማህበረሰብ ሰላም እንዲጠበቅ እና እንዲከበር በእምነት የሚሰራ፣ በስነ-ምግባር የታነፀ፣ ከራሱ በላይ የሚያስብና የሚሰጥ፤

**ህጋዊነት፡-** ለዜጋው ክብር ሰጥቶ አገልግሎት መስጠትን የህይወት መርሁ ያደረገ፣ ህግና መርህን የዕለት ተዕለተ ተግባሩና መገለጫው ያደረገ፣ ፍታሃዊነት፣

**ምክንያታዊነት፡-** አመለካከቱ፣ እምነቱ እና ድርጊቱ በነባራዊ ሁኔታዎች እና በመረጃዎች ላይ የተመሰረተ፣ ለመማር እና ለሌሎች ለማካፈል ክፍት የሆነ፣ ለሚወስዳቸው እርምጃዎች ሙሉ ሃላፊነት የሚወስድ፤

**አለም-አቀፋዊነት፡-** ከአካባቢ አጥር ወጥቶ የሚያስብና የሚሰራ፣ ብዝሃነትን አብሮነትንና በጋራ ማደግን፣ ለአለም አቀፍ ለውጦች እራሱን ዝግጁ ያደረገና የሚማር፣

## I. ተቋማዊ የማስፈጸም አቅም፣ የሀብት አጠቃቀም እና የአገልግሎት አሰጣጥ አሰራር ከማጎልበት አንጻር የተከናወኑ ተግባራት፤

### 1.1. የዕቅድ፣ ሪፖርት እና ፈጻሚ አካላትን ማዘጋጀት፤

ሚኒስቴር መ/ቤቱ ወደ 2015 በጀት ዓመት ተግባራት ከመገባቱ በፊት በ2014 በጀት ዓመት አፈጻጸም ላይ ጠንካራና ደካማ ጎኖች በመለየት በአመራርና በሰራተኛ ደረጃ በመገምገምና ተገቢውን ግብዓትና ትምህርት በመውሰድ ለ2015 በጀት አመት እቅድ እንደ መነሻነት ተወስዷል።

የ2015 በጀት ዓመት ዕቅድ ዝግጅት በተለይም በፕላንና ልማት ሚኒስቴር የቅርብ ክትትልና ድጋፍ እንዲሁም በተቋሙ አመራርና ሰራተኞች ተሳትፎ እንዲዘጋጅ ተደርጓል። በተጨማሪም የ2014 በጀት ዓመት ሪፖርት እና በ2015 ዕቅድ ዝግጅት ላይ በአጠቃላይ ሰራተኛ ደረጃ ውይይት ተደርጎበት እንዲዳብር እና የስራ ክፍሎች ዕቅዳቸውን ለባለሙያዎች እንዲያወርዱ ተደርጓል።

የሚኒስቴር መ/ቤቱን የውስጥ አሰራር በተለይም ሀብትን በአግባቡ ለመጠቀም የሚያስችል፣ የንብረት አጠቃቀምና አሰራር ስርዓትን ለማሻሻል የሚረዱ መመሪያዎችና ስታንዳርዶች በማዘጋጀትና በማጽደቅ ወደ ስራ ተገብቷል።

### 1.2. ተቋማዊ የለውጥና አቅም ግንባታ ተግባራት፤

ሚኒስቴር መ/ቤቱ በ2015 ከያዛቸዉ ቁልፍ ስራዎች አንዱ የሰላም ፖሊሲውን መሰረት ያደረገ የ10 ዓመት የዘላቂ ሰላም ፕሮግራምና በየአምስት ዓመቱ የሚፈፀሙ እና ቅድሚያ የተሰጣቸውን ሶስት ፕሮጀክቶችን በውስጥ አቅም ማዘጋጀትና መተግባር ነዉ። የፕሮግራምና ፕሮጀክቶች ዝግጅት መነሻ የሆነው የእሳቤ ለውጥ (Paradigm shift) ተቋሙ እንደአዲስ ከተደራጀ በኋላ አሁን ያለዉን ስር የሰደደ አገራዊ የሰላም እጦት ረጅም ርዕይ በሰነቀ፣ ሁሉንም ባለድርሻ አካላት ባቀናጀ፣ በተሟላ መልኩ ባሳተፈ እና በየደረጃዉ ባለቤትነት በፈጠረ አዲስ እሳቤ መስራት ነዉ።

በዚህ መሰረት በከፍተኛ አመራሮች የቅርብ አመራርና ድጋፍ እየተሰጠው ሰነዶችን ለማዘጋጀት የተደራጀው ቡድን በመጀመሪያ ደረጃ ለ10 ዓመት የሚዘልቅና በመላዉ ኢትዮጵያ የሚተገበር አንድ "የዘላቂና ሁለንተናዊ ሰላም ፕሮግራም" አዘጋጅቷል።

የፕሮግራሙ ዋና አላማ በ2024 በአገራችን ዘላቂና ሁለንተናዊ ሰላም ሰፍኖ ለማየት ከተቆራረጠና ቁጥቁጥ የሰላም ስራዎች በመውጣት በላቀ እሳቤ እና ቅንጅት መስራትን ታሳቢ ያደረገ ነው። በፕሮግራሙ ላይ በተቋም ደረጃ መግባባት ከተደረሰ በኋላ በቀጣይ ተከታታይ ዓመታት ፕሮጀክታይዝድ ሆነዉ በመንግስት፣ በህዝብና በልማት አጋሮች የሚደገፉ በርካታ የፕሮጀክት ሀሳቦች ተለይተው ወጥተዋል። ከነዚህ የፕሮጀክት ሀሳቦች ውስጥ ለዘላቂና ሁለንተናዊ ሰላም ስራዉ በመጀመሪያው ረድፍ ላይ ሆነው እንዲፈፀሙ ቅድሚያ ተሰጥቷቸዉ የተዘጋጁት

**አንደኛ፣** "የቅጭት ቅድመ ማስጠንቀቂያና ምላሽ ስርዓት ፕሮጀክት" ነው። ዋና አላማዎቹም በቴክኖሎጂ የታገዘ አገር አቀፍ የሁኔታ መቀበያ ክፍሎችን በማቋቋምና በማጠናከር ፈጣን ምላሽ የመስጠት አቅምን ማሳደግ፣ ግጭትን አስቀድሞ በመከላከል የዜጎችን ሰላምና ደህንነት እንዲጠበቅ ማድረግ እና የሰላምና ጸጥታ ተቋማዊ አቅም እንዲጎለብት ማድረግ ናቸው። ይህ ሲሆን ግጭቶችን መከላከልና በዘላቂነት መፍታት ይቻላል።

**ሁለተኛ፣** "የሰላም ብሄራዊ በጎ ፈቃድ ማህበረሰብ አገልግሎት ፕሮጀክት" ነው፡፡ ዋና አላማዎችም ህብረ-ብሔራዊ አንድነት አስተሳሰብና ድርጊት ማሳደግ፣ በጎ ፈቃደኝነትን ለዘላቂ ሰላም ግንባታ ማዋል፣ እና ተቋማዊ የማስፈጸም አቅም ማሳደግ ናቸው፡፡ በዚህም የሰላምና የህብረ-ብሔራዊ አንድነት በጎ ፈቃድ አገልግሎትን ማሳደግ ይቻላል፡፡

**ሶስተኛ፡-** "የተመረጡ የግጭት ቀጣናዎችን ወደ ሰላምና ልማት የማሸጋገር ፕሮጀክት" ነው፡፡ ዋና አላማዎቹም የታጠቁ አማጽያን ሃይሎችን ትጥቅ ማስፈታት፣ መልሶ ማቋቋም፣ ሽምግልና፣ እርቀሰላም እና ይቅር መባባል ችግሮችን በዘላቂነት መፍታት፣ የህግ የበላይነትን በማረጋገጥ በአካባቢዎቹ ህገ-ወጥ ድርጊቶችንና ወንጀሎችን ማስወገድ፣ ጠንካራ የመንግስታትና የህዝብ ለህዝብ ግንኙነት ማሳደግ፣ የኢኮኖሚ እና ማህበራዊ አገልግሎት የጋራ ተጠቃሚነትን ማሳደግ፣ እና የማህበረሰቡንና የተቋማትን አቅም መገንባት ናቸው፡፡ በዚህም የተመረጡ የግጭት አካባቢዎችን ወደ ዘላቂ ሰላምና ልማት የማሸጋገር ግብ ይሳካል፡፡

ሰነዶቹ ስታንዳርዳቸዉን የጠበቁ ለማድረግ ለውጪ የመስኩ ባለሙያዎች ማለትም ለአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ በአገራዊና ቀጣናዊ ሰላምና ግጭት ላይ ጥናትና ምርምር ለሚያደርጉ እንዲሁም በግጭት መከላከልና አፈታት ሰፊ ልምድ ላላቸዉ አገር በቀል የሲቪክ ማህበራት በመስጠት ከ10 ቀናት በላይ ጊዜ ወስደዉ እንዲተቹና ግብዓት እንዲሰጡ በማድረግ ሰነዶቹ እንዲዳብሩና ደረጃቸዉን የጠበቁ እንዲሆኑ ተደርጓል ፡፡

በረቂቅ ደረጃ የተዘጋጁ ሰነዶችን ከትግራይና ኦሮሚያ ክልሎች በስተቀር በሁሉም ክልሎችና የከተማ አስተዳደሮች በአካል በመገኘት ከየክልሉ ከ30 እስከ 40 በጠቅላላው 445 (396 ወንድ እና 49 ሴት) ለሚሆኑ ለካቢኔዉና ጉዳዩ ለሚመለከታቸዉ መሪ ተቋማት ከፍተኛ አመራሮች የማስተዋወቅ እና የጋራ መግባባት የመፍጠር ስራዎች ተሰርተዋል፡፡

በሌላ በኩልም የኢትዮጵያ የሰላም ምክር ቤት ምስረታ ጉባኤ ላይ የክልል ሰላምና ፀጥታ ቢሮ ሃላፊዎች፣ የሃይማኖት ተቋማት ጉባኤ የበላይ ጠባቂዎች፣ የፓለቲካ ድርጅቶች የጋራ ምክር ቤት፣ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሰላምና ፀጥታ ቋሚ ኮሚቴዎች፣ የተለያዩ ሲቪክ ማህበራት በድምሩ 117 (ወንድ 102 ሴቶች 15) አመራሮች በተገኙበት ሰነዶቹ ቀርበውና ምክክር ተደርጎባቸው ግብዓቶች ተሰባስበዋል፡፡

በነዚህ የምክክር መድረኮች ዘላቂና ሁለንተናዊ ሰላም ለመገንባት ፕሮግራሙና የተመረጡ ፕሮጀክቶች ስኬት ወሳኝ በመሆኑ ላይ የጋራ መግባት ተፈጥሯል፡፡ በተጨማሪም የፌዴራልና የክልል ተቋማት ለፕሮግራሙና ፕሮጀክቶች ውጤታማነት የበኩላቸውን ሚና በቅንጅት፣ በመናበብና በተጠያቂነት መፈጸም የሚያስችል የተልዕኮ እና የሚና ግልጽነት ተጥሯል፡፡ ሰነዶቹም በተገኘው ግብዓት እንዲዳብሩ ተደርጓል፡፡ በመድረኮቹ የተነሱ ጉዳዮች ዝርዝር መረጃ ራሱን ችሎ ለተቋማዊ ዕውቀት በሚሆን መልኩ ተሰንዷል፡፡

በዚህ መልኩ ዳብረው የተዘጋጁ የፕሮግራምና ፕሮጀክት ሰነዶች በኢንግሊዘኛ እንዲተረጎሙ በማድረግ በሀብት ማሰባሰብና በአፈጻጸም አግባቦች ላይ ከዋና ዋና የልማት አጋሮችና ሲቪክ ማህበራት አመራሮች ጋር  ምክክር ተደርጓል፡፡ በዚህም በፕሮግራሙና ፕሮጀክቶች እሳቤ እና

የአፈጻጸም አቅጣጫዎች ላይ የጋራ መግባባት ከመደረሱም በላይ ለማስፈጸም የሚያስፈለግውን ሀብት በጋራ ለማሰባሰብ በሚያስችል አሰራር ላይ ከስምምነት ተደርሷል፡፡

በሌላ በኩልም ለመንግስት ውሳኔ ቀርቦ የነበረው የኢፌዲሪ የሰላም ፖሊሲ በፕላንና ልማት ሚኒስቴር በተዘጋጀው የፖሊሲ ማንዋል መሰረት ማስተካከያዎች የተደረጉ ሲሆን ከፖሊሲ ፈጻሚዎች ጋር የማናበብ (Policy Alignement) እና የጋራ መግባባት ተፈጥሯል፡፡ በዚህም በቀጣይ ፖሊሲው በፕላንና ልማት ሚኒስቴር በኩል ለሚኒስትሮች ም/ቤት ቀርቦ እንደሚጸድቅ ይጠበቃል፡፡ እንዲሁም ከሰላም ፖሊሰው የተቀዳ የሰላም ብሄራዊ በጎ ፈቃድ አገልግሎት ስትራቴጂ ረቂቅ ሰነድ ማዘጋጀት ተችሏል፡፡

ተቋማዊ አቅምን ለማሳደግ እንዲቻል የውጪ ልምድ ለመቀመር በታየዘው ዕቅድ መሰረት ሁለት አመራሮች በሩዋንዳ ትምህርታዊ ጉዞ በማድረግ እንዲሁም በአሜሪካ ሃገር በተዘጋጀ ኮንፈረንስ ላይ ተሳትፎ ተደርጓል፡፡ በነዚህ መድረኮች ማህበረሰብ ያሳተፈ ሰላምና ልማት፣ የስነ-ልቦና እና አካላዊ ጉዳት ህክምና ሂደት ተቋማዊ አደረጃጀት፣ ትጥቅ የፈቱ አካላትን ተሃድሶ እና መልሶ በማቋቋም እና በመቀላቀል ሂደት፣ የሰላም አስተምህሮቶች፤ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች እና አጋር አካላት ተሳትፎ እና የሃይማኖት ተቋማት በሰላም ግንባታ ባላቸው ሚና ዙሪያ ለሃገርና ለተቋም የሚጠቅሙ ልምዶች ተገኝተዋል፡፡ የተገኙ ልምዶችም ተቀምረው ለተቋሙ አመራሮችና ሰራተኞች ቀርቧል፡፡

በተቋሙ የውስጥ የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት የአገልግሎት አሰጣጥ ለማሻሻል የአሰራር ስርዓትና የግንኙነት አግባብን መመሪያ በማዘጋጀት ወደስራ ተገብቷል ፡፡

በተቋሙ የሚሰጡ አገልግሎቶች ተገልጋይ ተኮር፣ ቀልጣፋ፣ ፍትሀዊ እና ግልፀኝነት የሰፈነበት እንዲሆን ለማድረግ እና የተገልጋዮችን እርካታ በማሳደግ መልካም አስተዳደርን ለማስፈን እንዲያስችል የዜጎች ቻርተር ረቂቅ ሰነድ የተዘጋጀ ሲሆን ከተቋሙ የከፍተኛ አመራር ውሳኔ በኋላ ወደ ተግባር እንዲገባ ይደረጋል፡፡ የተገልጋይ ዕርካታ ለማሳደግና መልካም አስተዳደር ለማስፈን እንዲቻል ክፍተቶችንና የአግልግሎት አሰጣጥ ችግሮችን ለመለየት ጥናት እየተደረገ ሲሆን ከጥናቱ በሚመነጩ ጉዳዮች ዙሪያ ከሚመለከታቸው የስራ ክፍሎች ጋር የማስተካከያ እርምጃዎች እንዲወሰድ የማድረግ ስራ እየተከናወነ ይገኛሉ፡፡

በስራ አፈጻጸማቸው እና በታታሪነታቸው ወደ ፊት የወጡ የተቋሙን ሰራተኞች ለማበረታታትና እውቅና ለመስጠት የሚያስችል ውጤትን መሰረት ያደረገ የማበረታቻ እና እውቅና አሰጣጥ የአፈፃጸም መመሪያ የተዘጋጀ ሲሆን በበላይ አመራሩ ከጸደቀ በኋላ ወደ ተግባር የሚገባ ይሆናል፡፡

ወረቀት አልባ አሰራርን ለማጠናከር እና ለተገልጋዮች መረጃ ተደራሽ ማድረግ የሚያስችሉ ስራዎችን የመስራትና የተለያዩ መረጃዎችን በሶፍት ኮፒ እንዲዘጋጁ ተደርጓል፡፡

የቅሬታና መልካም አስተዳደር ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችል የጥቆማ ማሰባሰቢያና መቀበያ ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ እየተደረገ ይገኛል፡፡ የመልካም አስተዳደር ጉዳዮችን የሚመለከት ሪፖርት እየተዘጋጀ በጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት የመልካም አስተዳደር ጉዳዮች ክትትል ዘርፍ እንዲላክ ተደርጋል ፡፡

### 1.3. የሰው ሀብት ልማት እና አስተዳደር አሰራርና ውጤታማነት፤

በሲቪል ሰርቪስ ፀድቆ በመጣው የደረጃ ማሻሻያ መሰረት በ30 የስራ መደቦች የደረጃ ማሻሻያ ተከናውኗል፤ እንዲሁም በክፍት የስራ መደቦች ላይ ከዚህ ቀደም ምደባ ላላገኙ ሰራተኞች በሁለት ዙር ውድድድር በማከናወን መስፈርቱን ላሟሉ 15 ሰራተኞች ስምሪት ተከናውኗል፤ 35 ሰራተኞች ወደ ተጠሪ ተቋማትና ወደ ሌሎች ተቋማት እንዲመደቡ ተደርጓል፡፡

በረጅም ጊዜ ትምህርትና ስልጠና በመጀመሪያ ዲግሪ 7፣ በማስተርስ ዲግሪ 8 እና በፒኤችዲ 1 በድምሩ 16 ባለሙያዎች ትምህርታቸውን በመከታተል ላይ ይገኛሉ፤

በአጭር ጊዜ ስልጠና

- ✓ 10 ሰራተኞች በተቀናጀ የሲቪል ሰርቪስ መረጃ አያያዝ ስርዓት (ISMIS)፣
- ✓ 2 ሰራተኞች በኦንላይን የሰው ኃብት አስተዳደር፣
- ✓ 2 ሰራተኞች በእውቀት አስተዳደር፣
- ✓ 7 ሰራተኞት በለውጥ መሳሪያዎች ትግበራና ሥራ አመራር፣
- ✓ 3 ሰራተኞት በእቅድና በጀት ዝግጅትና ክትትል፣
- ✓ 6 ሰራተኞች በሂሳብ መዝገብ አያያዝ፣
- ✓ 2 በፌዴራል መንግሥት የሂሳብ አያያዝ፣
- ✓ 3 ሰራተኞች የፋይናንሻያል ኦዲት ማንዋል
- ✓ 2 ሰራተኞት የፋይናንሻያል ኦዲት እና IFMIS፣
- ✓ 2 ሰራተኞት በፌዴራል መንግሥት የክዋኔ ኦዲት እና የፋይናንስ አያያዝ ላይ፣
- ✓ 10 ሰራተኞት በህገ መንግሥት፣ በግጭት መከላከል፣ በአመራርና ዲሞክራሲ
- ✓ 60 ሠራተኞች የፌደራሊዝም ጽንሰ ሀሳብ እና በመንግስታት ግንኙነት የክልልና የፌዴራል ግንኙነት ስርዓት ስልጠና
- ✓ 264 ሰራተኞት በለውጥ፣ ጠንካራ የሥራ ባህል እና ፕሮቶኮልና ኢትኪቲ፣
- ✓ 131 ሠራተኞች Transformational Leadership፣ Creative Problem Solving and Decision Making፣ Attitudinal Transformation፣ Time and Stress Management እና ውጤታማ የመንግሥት አገልግሎት አሰጣጥ

በድምሩ 506 የተቋሙ ሰራተኞች 14 የተለያዩ ርአሶች ላይ ስልጠናዎች እንዲያገኙ በማድረግ አቅማቸው እንዲገነባ ተደርጓል፡፡

7 ሰራተኞች በዝውውር፣ 4 በጡረታና 7 በራሳቸው ፈቃድ 12 ሰራተኞች በምደባ ቦታ ያላገኙ በአጠቃላይ የ30 ሰራተኞች የስንብት ሥራ ተከናውኗል፡፡

37 የዋስትና፣ 72 ልዩ ልዩና የትብብር/ድጋፍ ደብዳቤ ለ25 ሰራተኞች የስራ ልምድ ማስረጃ፤ ለ156 ሠራተኞች የዓመት ፈቃድ፣ ለ240 ሰራተኞች የአመት ፈቃድ ዝውውር አስተዳደርዊ ስራዎች ተሰርተዋል ፡፡

የሰርተኛውን የቁጠባ ባህል ከማሳድግ አንጻር 18 አዲስ አባላት በገንዘብና ቁጠባ ብድር ህብረት ሥራ ማህበር የተመዘገቡ ሲሆን፣ በበጀት ዓመቱ 26 የማህበሩ አባላት ብር 1,444,155.25 የብድር ተጠቃሚ መሆናቸውን በአሁኑ ሰዓት አጠቃላይ የየማህበሩ ካፒታል ብር 4,835,770.40 ደርሷል፡፡

ለተቋሙ የተፈቀደው የስራ መደቦች ብዛት 275 ሲሆን ምደባ ያገኙ ሰራተኞች ብዛት 261 ናቸው ፡፡ ከእነዚህ ውስጥ (ወንድ 140 ሴት 121) ሲሆን የሴቶች ድርሻ 46 በመቶ ነው፡፡

## 1.4. የፋይናንስና ንብረት አስተዳደር አሰራርንና ውጤታማነት፤

### ሀ. የበጀት አጠቃቀም ውጤታማነት፤

ለሚኒስቴር መ/ቤቱ በ2015 በጀት ዓመት በአጠቃላይ 886,987,719 የተፈቀደ ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር 879,360,112 (99.14%) ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ በዝርዝር ሲታይ፡

- ✓ ለመደበኛ በጀት ብር 119,937,719 ሲሆን በሥራ ላይ የዋለ በጀት ብር 118,432,581 (98.74%) ነው፡፡
- ✓ ለበጎ ፈቃድ ፕሮጀክት ብር 767,050,000 ሲሆን በሥራ ላይ የዋለ በጀት ብር 760,936,532 (99.2%) ነው፡፡

### ለ. ፋይናንስ አሰራር ውጤታማነት፤

የፋይናንስ ህግና ደንብን መሰረት ያደረገ የሂሳብ አሰራር በመከተል ክፍያዎችን የመፈጸምና ወቅታዊ ሪፖርት የማዘጋጀት ስራ ተሰርቷል፡፡ ዓመታዊ የፋይናንስ ሪፖርት ማዘጋጀት ተችሏል፡፡

ከየሥራ ክፍሎች በሚቀርበው የጥሬ ገንዘብ ፍላጎት መረጃ መሠረት የመደበኛና የካፒታል በጀት ወርሃዊ የጥሬ ገንዘብ ጥያቄ ተዘጋጅቶ ለገንዘብ ሚኒስቴር በማቅረብ ማስፈቀድ ተችሏል፡፡

ለረጅም ጊዜ ሳይወራረዱ የቆዩ የቅድመ ክፍያን ተሰብሳቢ ሂሳቦችን የማጥራትና የመለየት ተግባራት ተከናውኗል፡፡ከሃይማኖት ተቋማት ምዝገባ ክፍያ 300.000.00 ሺ ብር ገቢ ለማሰባሰብ ታቅዶ 351.640.00 ብር ከአገልግሎት እና ቅጣት ክፍያ ገቢ መሰብሰብ ተችሏል፡፡ አፈጻጸሙም 100% ነው፡፡

የ2015 በጀት ዓመት የግዥ እቅድ በኤሌክትሮኒክስ የግዥ ዘዴ EGP በሲስተም እንዲታቀድ በተሰጠው አቅጣጫ መሰረት ከየስራ ክፍሎች የግዥ ፍላጎት እንዲሰበሰብ የተደረገ ሲሆን ይህንንም በማጠቃለል በኤሌክትሮኒክስ ግዥ EGP ሲሰተም በማስገባት ለግዥ ባለስልጣን ተልኳል፡፡ በተመሳሳይ ከ2015 ዓ.ም እስከ 2017 ዓ.ም ያለውን የማእቀፍ የግዥ ፍላጎት እቅድ በኤሌክትሮኒክስ ግዥ EGP በሲሰተም ተልኳል፡፡ የተለያዩ የዕቃና አግልግሎት ግዥዎችን በኤሌክትሮኒክስ ግዥ EGP ሲስተም በመጠቀም ግዥ ተፈጽሟል፡፡

### ሐ. የኦዲት ቁጥጥር፤

የ2014 በጀት ዓመት ማጠቃለያ የሣጥን ጥሬ ገንዘብ፤ የባንክ ሂሳብ ባላንስ፤ ሥራ ላይ ያልዋሉ የአላቂ ዕቃዎች ቆጠራ በማድረግ የፈሰስ ሂሳብ ሪፖርት ለገንዘብ ሚኒስቴር ትሬዠሪ መምሪያ እና ለተቋሙ የበላይ አመራሮች ቀርቧል፡፡ እንዲሁም የ2015 በጀት ዓመት ከሐምሌ 2014 እስከ ግንቦት 2015 ዓ.ም ድረስ ወርሀዊ የሳጥን ሂሳብ ቆጠራ ኦዲት በማድረግ ሪፖርቱን ለሚመለከታቸው አካላት እንዲደርስ ተደርጓል፡፡

የሥጋት አካባቢዎች ተብለው በተለዩት ግዥ፤ ውሎ አበል፤ ነዳጅ፤ ጥገና እንዲሁም የሆቴል መስተንግዶ አገልግሎቶች ወጪዎችን መሰረት ተደርጎ የተቋሙን የ2014 በጀት ዓመት አራተኛው ሩብ ዓመት የፋይናንስ/የህጋዊነት ኦዲት በማከናወን ሪፖርት ለሚመለከታቸው ቀርቧል፡፡

የ2015 በጀት ዓመት ከአንደኛው ሩብ ዓመት እስከ ሶስተኛው ሩብ ዓመት ድረስ የፋይናንስ/የህጋዊነት ኦዲት በማከናወን ሪፖርት ለሚመለከታቸው ሁሉ ተልኳል፡፡

መንግስት በመስሪያ ቤታችን በኩል ለሃይማኖት ተቋማት ጉባኤ ድጋፍ የሚያደርገውን ገንዘብ ተቋሙ ላይ በመገኘት የኦዲት ስራው ተከናውኖ ሪፖርት ለሚመለከታቸው ሁሉ ቀርቧል፡፡

በኦዲት ግኝት አስተያየት ሪፖርት መሰረት ኦዲት ለተደረገው ክፍልም ሆነ ለሚመለከታቸው ባለሙያዎችና አመራሮች ሙያዊ ድጋፍ ማድረግና የማማከር ሥራ ያለማቋረጥ ተከናውኗል፡፡

በውጭ ኦዲተሮች በተገኙ ግኝቶች መሰረት የማስተካከያ መርሃ ግብር በማውጣት በከፍተኛ አመራሩ ጥብቅ ክትትል የማስተካከያ እርምጃዎች እየተወሰዱ ይገኛል፡፡ ለአብነትም ተሰብሳቢ ሂሳብ ከ360 ሚሊየን ወደ 61 ሚሊየን ማውረድ እንዲሁም የተከፋይ ሂሳብ 135 ሚሊዮን ወደ 28 ሚሊዮን ማውረድ ተችሏል፡፡

**መ. የንብረት አያያዝ፤**

የቋሚ እና የአላቂ ንብረቶች መጋዝን ተለይቶ እንዲደራጅ ተደርጓል፤ ለ70 ተሽከርካሪዎች አመታዊ ምርመራ ክላዉዶ ተደርጎ ቦሎ ተለጥፏል፣ የተሽከርካሪዎች መረጃን በዘመናዊ መልክ/ በሶፍት ኮፒ የማደራጀት ስራ ተሰርቷል

የሚወገዱ ንብረቶችን በመለየት የማስወገድ ስራ የተሰራ ሲሆን ከዚህም 639,000 ብር ገቢ ማድረግ ተችሏል፡፡

የበጎ ፈቃድ ስራን ከማጠናከር አንጻር የስልጠና ማዕከል ለተባበሩን ዩኒቨርሲቲዎች፣ ለክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች በድምሩ 9720 ታብሌት በስጦታ መልክ ተበርክቶላቸዋል፡፡ እንዲሁም ለመከላከያ ሰራዊት 5,000 የእጅ ሳሙናና 5,000 የዱቄት ሳሙና የፅዳት ዕቃዎች ድጋፍ ተደርጓል፡ :

## 1.5. የኢንፎርሜሽን፣ ኮሙኒኬሽን እና ቴክኖሎጂ አሰራርንና ውጤታማነትን ማሳደግ፤

በስራ ላይ ባለው ብሔራዊ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ምዝገባ እና አስተዳደር ስርዓት ላይ በ10 ክልሎችና በ2 ከተማ አስተዳደሮች ለሚገኙ አስተባባሪዎችና ለሠላም ሚኒስቴር ባለሙያዎች በአጠቃላይ ለ32 ባለሙያዎች የአሰልጣኞች ስልጠና ተሰጥቷል፡፡ እንዲሁም በ4 ክላስተር ለ274 የክልል፣ ከተማና ዞን አስተባባሪዎች በድምሩ ለ306 አካላት ስልጠናውን መስጠት ተችሏል፡፡ በተጨማሪም ሲስተሙ በኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር ፍተሻ ተደርጎለት አስተያየት እና ማሻሻያ ሃሳቦች ታክሎበታል፡፡ እንዲሁም ሲስተሙን የማሻሻል ስራ ተጀምሯል፡፡

የ6ኛ ዙር የወጣቶች በጎ ፈቃድ ምዝገባ፣ ስልጠና እና ምደባ በለማው ሲስተም በመታገዝ ተሰርቷል፡ ፡ እንዲሁም የ7ኛው ዙር ምዝገባ በኦንላይን በጎፈቃደኞች ተመዝግበው በስልጠና ወስደዋል፡፡፡፡

የሰላም ሚኒስቴር እንግዶች መግቢያ መመሪያ እና ኮምፒዩተራይዝድ ሲስተም ከኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር ጋር በመሆን ተዘጋጅቶ ከሰላም ሚኒስቴር መዋቅር ጋር በማጣጣም ፍተሻ እየተደረገ ይገኛል፡፡

የደህንነት ካሜራ ሲስተም ዝርጋታ በማድረግ በየወለሉ ካሜራዎች ተገጥመው ስራ ጀምረዋል፡፡

ከኢትዮ ቴሌኮም በተገኘ አገልግሎት የሰላም ሚኒስቴር ኦፊሻል ኢሜይል ተዘጋጅቶ የሃላፊዎች እና ባለሙያዎች አካውንት ተዘጋጅቶ ስራ ላይ ውሏል፡፡

በኢ-ሰርቪስ የሚደረገው የሃይማኖቶች ምዝገባ እና ፈቃድ አሰጣጥ ስርዓት ቴክኒካዊ ድጋፍ እየተሰጠ በመስራት ላይ ይገኛል፡፡

ከኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር ጋር በመሆን የሰላም ሚኒስቴር ድረ- ገፅ በአዲስ መልክ ተሰርቷል፡፡ የሙከራ ስራ ተጠናቆ አጭር ስልጠና እና ላውንቺንግ በማድግ ለስራ ዝግጁ ሆኗል፡፡

የሰራተኞች የሰዓት ፊርማ በጣት አሻራ እንዲሆን በማድረግ ስራ ማስጀመር ተችሏል፡፡

የተሸከርካሪ መረጃ (ፕሮፋይል) መመዝገቢያ መለስተኛ ዳታቤዝ ተዘጋጅቷል፡፡

### 1.6. የአጋርነት እና የህዝብ ግንኙነት አሰራርንና ውጤታማነትን ማሳደግ፤

#### ሀ. የአጋርነት አካላት ቅንጅታዊ አሰራርና ተሳትፎ፤

የተቋሙን ተልዕኮ ለማሳካት የተቀረጹ ፕሮጀክቶችን ወደ ተግባር ለማስገባት በተቋሙ ከፍተኛ አመራሮች ከተለያዩ የውጭ አጋር አካላት ጋር ሃብት ማፈላለግ ሂደት ላይ ውይይቶች ተደርገዋል፡፡

በትምህርት ተቋማት ሰላማዊ የመማር ማስተማር ለመፍጠር ከትምህርት ሚ/ር ጋር በትብብርና በአጋርነት ለመስራት መግባቢያ ሰነድ ተፈርሟል፡፡ በትብብር ከሚሰሩ ተግባራት ውስጥ በትምህርት ተቋማት ሰላምን የመገንባት፣ በትምህርት ስርዓቱ እንዲካተት የማድረግ፤ ብሄራዊ መግባባትን የማጎልበት፣ የበጎ አድራጎት ስራዎችን ባህል የማድረግ፣ ግጭቶችን የመከላከልና ሲከሰቱም የሰላም አደረጃጀቶችን በማቋቋምና በማጠናከር ግጭቶችን መፍታት፡፡ በዚህ መሰረት ከሁለቱ ተቋማት የተወጣጣ ግብረ-ሃይል ተቋቁሞ የትግበራ ዕቅድ እንዲሁም ቀጣይ ተልዕኮዎች ሊያሳኩ የሚችሉ ስትራቴጂክ ጉዳዮች/far reaching implications/ ተዘጋጅቶና በሁለቱም ተቋማት የበላይ ሃላፊዎች ጸድቆ ወደ ስራ ተገብቷል፡፡

ከኢትዮጵያ የሲቪል ድርጅቶች ካውንስል እና የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት ጋር በሃገራዊ ምክክር ሂደቱ የኮሚሽኑን ተልዕኮና ሃላፊነት ባከበረ መልኩ ማህበረሰቡ ላይ ግንዛቤ ለመፍጠርና በሂደቱ የሚኖረውን ተሳትፎ ለማጉላት የሚያስችል ስራ ለመስራት ስምምነት ተፈጥሯል፡፡ ይህ ስምምነት በሶስቱ ዘርፎች ማለትም በመንግስት፣ በፖለቲካ ፓርቲዎች እና በሲቪል ማህበራት መካከል የነበረውን እርስበርስ የመጠራጠርና የመገፋፋት ታሪክ ቀርፎ ለሰላምና ለሃገር ግንባታ በጋራ ሊሰሩ የሚያስችላቸው ነው፡፡

ከፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን፣ ከፍትህና ሕግ ኢንስቲትዩት፣ ከኢትዮጵያዊነት የዜጎች መብት ማስከበሪያ ድርጅት፣ ከMDS (Mobile digital screen service) እና ከዊዝ ኪድስ ከሚባል ሀገር በቀል ተቋም ጋር የመግባቢያ ሰነድ (MoU) በመፈራረም ወደ ስራ ተገብቷል፡፡

በኮሪያ መንግስት ድጋፍ በኦሮሚያ እና ሱማሌ ክልሎች ተደጋጋሚ ግጭቶች በሚከሰትባቸው 10 ወረዳዎች የተከሰቱ ግጭቶች እና ያደረሰውን ጉዳት ጥናት ተደርጓል፡፡ጥናቱን መሰረት በማድረግ በግጭት የተጎዱ እና የተፈናቀሉ የማህበረሰብ ክፍሎችን ማህበረዊ እና ኢኮኖሚያዊ ድጋፍ ለመስጠት እና ለማቋቋም እንዲሁም ችግሮቻቸውን በዘላቂነት ለመፍታት የ10 ሚሊዩን ዶላር ፕሮጀክት በጋራ ተቀርጾ MOU በመፈራረም ወደ ትግበራ ተገብቷል፡፡

**ለ. የህዝብ ግንኙነት አሰራርንና ውጤታማነት፤**

ፈጣን ወቅታዊ እና ትክክለኛ መረጃ በመስጠት የህብረተቡን የመረጃ ፍላጎት ለማርካት ልዩ ልዩ የዜና ዘገባዎች 128 ጊዜ ለማከናወን ታቅዶ 180 የተለያዩ ዘገባዎችን መዘገብ በተለያዩ የኤሌክትሮኒክስና ሶሻል ሚዲያም ሽፋን እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡

የፌስቡክ ገጻችን በ2014 በጀት ዓመት መጨረሻ ላይ ከነበረው 188 ሺ የተከታይ ቁጥር ወደ 212 ሺህ 078 ከፍ ብሏል፡፡ የትዊተር ገፁን ተከታዮች ቁጥር ደግሞ በ2014 በጀት ዓመት መጨረሻ ላይ ከነበረው 101 ሺ 200 ወደ 104 ሺህ 400 ማድረስ ተችሏል፡፡

በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ለውጭ ግንኙነትና የሰላም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ያቀረበውን የመጀመሪያ ሩብ እና ግማሽ ዓመት ሪፖርትና ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትሩ ሀገራዊ የሰላምና ጸጥታ ሁኔታን አስመልክቶ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሰጡትን ማብራሪያ መሰረት በማድረግ እና የፌዴራሊዝምና የግጭት አስተዳደር ላይ የተሰሩ ስራዎችን ላይ 11 በግራፊክስ እና 4 በቪዲዮ የተሰሩ ዜናዎች በፌስቡክ ገፅ አየር ላይ እንዲውሉ ተደርጓል፡፡

የተቋማችንን ዩቱብ ቻናል ስራ ለማስጀመር 29 አዳዲስ ቪዲዮዎች ተለቀዋል፡፡ 102 ተከታዮችን ማፍራት የተቻለ ሲሆን ቀጣይ ተቋማዊ የሳይበር ሰራዊት በመገንባት እና የኮሙኒኬሽን ካውንስል በማቋቋም ተጠናክሮ የሚሰራበት ይሆናል፡፡ በተጨማሪም የተቋሙን ዌብ ሳይት ከሚያበለጽጉ አካላት ጋር መረጃ የመመገብና የክትትል ስራ ተሰርቷል፡፡

የብሔራዊ የበጎ ፈቃድ የማህበረሰብ አገልግሎት ፕሮግራምን አስመልክቶ በጎ ፈቃደኞች ወደ ዩኒቨርስቲ እንዲገቡ ጥሪዎችን የማስተላለፍ ስራ የተሰራ ሲሆን በአምስቱም ዩኒቨርሲቲዎች ማለትም /በባህር ዳር፤ በዋቻሞ፤ በጂማ፤ በወላይታ ሶዶ እና በደብረ ማርቆስ/ በእንኳን ደህና መጣችሁና በምረቃ- ፕሮግራሙ ላይ ለተሳታፊዎች የሚቀርቡ የ34 ደቂቃ የቪዲዮ መልዕክቶችን እና የ6 ደቂቃ የፎቶ ቅንብር በራስ አቅም በማዘጋጀት እንዲተላለፉ የማድረግና ዘገባዎችን የማጋራትና በማህበራዊ ሚዲያ ገጻችን በማጋራት በወላይታ ሶዶ እና በዋቻሞ ዩኒቨርሲቲ የምረቃ ፕሮግራም ቀጥታ የማስተላለፍ ተግባር ተከናውኗል፡፡

የብሔራዊ የበጎ ፈቃድ የማህበረሰብ አገልግሎት ፕሮግራም ተሳታፊ የሆኑት በጎ ፈቃደኛ ወጣት ብርሃኔ አሳየን ተሞክሮን ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ህዝቦች ክልል ቤንች ሸኮ ዞን ጊዲ ወረዳ ድረስ በመሄድና ቃለ ምልልስ በማድረግ በተቋሙ የፌስ ቡክ ገፅ የተለቀቀ ሲሆን በርካቶች ከታሪኩ መማር ችለዋል፡፡ የ17 ደቂቃ ዶክመንተሪም ተዘጋጅቶ ለበጎ ፈቃደኞች በተዘጋጀው የእውቅና መርሃ ግብር ላይ እንዲተላለፍ ተደርጓል፡፡

እንዲሁም ተቋሙ በቋሚነት የአየር ሰዓት እንዲኖረው ለማድረግ ታቅዶ ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን የአሰራር ስርዓቱን ተከትሎ ጨረታ በማስወጣት 20 ደቂቃ ርዝማኔ ያለው 16 ፕሮግራም ለማዘጋጀት ዋልታ ሚዲያና ኮሙኒኬሽን ያሸነፈ ሲሆን በበጀት ዓመቱ 16ቱ ፕሮግራሞች ተሰርተው አየር ላይ ውሏል፡፡

አዲስ የአየር ሰዓት ለመግዛት ጨረታ በማውጣትና ሚዲያዎችን በማወዳደር ዋልታ ሚዲያና ኮሙኒኬሽን ጨረታውን ያሸነፈ ሲሆን በአሁኑ ሰዓት 26 የቴሌቪዥንና የሬዲዮ ፕሮግራሞችን ተቀርፆ እየተላለፈ ይገኛል፡፡

ወቅታዊ ክዋኔዎችን /Events/ የማስተባበር፤ የማቀናጀትና የመምራት ተግባራት እየተከናወኑ የሚገኝ ሲሆን ጳጉሜ 3 ቀን 2014 ዓ.ም የተከበረውን ሀገር አቀፍ የሰላም ቀንን ምክንያት በማድረግ ፕሮግራሙን በማስተባበር የሰላም ፖል እንዲተከል ተደርጓል፡፡

በአጠቃላይ በማህበራዊ ሚዲያ ከተላለፉ180 ዜናዎች መካከል136 ዜናዎች በድግግሞሽ በዋልታ ቴሊቪዥን፣ በኢቲቪ፣ በኦቢኤን፣ በፋና፣ በአሚኮ፤ በአዲስ ቲቪ፣በደቡብ ቴሊቪዥን የሚዲያ ሽፋን ያገኙ ሲሆን በጀርመን ድምፅ ሬዲዮ/DW/ 4 ዜናዎች፣ በአሜሪካ ድምፅ ራዲዮ 4 ዜናዎች፣ በሃዲያ ቴሊቪዥን 2 በድሬዳዋ ቴሊቪዥን 3 ዜናዎች፣ በኢቢኤስ ቴሊቪዥን 3 ዜናዎች፤ በአሃዱ ቴሊቪዥን 1፤ በአሻም ቴሊቪዥን 1እና በወላይታ ቴሊቪዥን 2 ዜና አየር ላይ ውሏል፡፡

በየዕለቱ የመደበኛና የማህበራዊ ሚዲያዎችን ክትትልና ዳሰሳ በማድረግ የሚዲያ ሞኒተሪንግ ስራ (ለኮሙኒኬሽን ስራችን አጋዥ የሆኑ መረጃዎችን የመለየትና የመተንተን) ስራ የተሰራ ሲሆን መረጃውንም ለሚመለከተው አካል የማጋራት ስራ እየተሰራ ይገኛል፡፡

በተቋሙ UTS ላይ የተለያዩ ወቅታዊ መረጃዎችን የመልቀቅ ስራ እየተሰራ ይገኛል፡፡ 30 ዓለም-አቀፋዊ፤ ብሔራዊና ሐይማኖታዊ በዓላትንና ሌሎች ወቅታዊ ክስተቶችን በመመርኮዝ መልዕክቶችን በመቅረጽ ተላልፏል፡፡

ለአማራ ሚዲያ ኮርፖሬሽን፤ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት፤ ለኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት ለዋልታ ሚዲያና ኮሙዩኒኬሽን ኮርፖሬት እና ለፋና ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬት ከከፍተኛ አመራሩ ጋር በመምከር የቃለ መጠይቅ መድረክ የማመቻቸት ስራ ተሰርቷል፡፡

ተቋሙን በመረጃ የሚገልጹ 04 ቴሌቪዥኖች በየኮሊደሮች ተሰቅለው አገልግሎት ለመስጠት ተዘጋጅተዋል፡፡

ሰላም የውስጥ መጽሔትን በአመት 4 ጊዜ ለማዘጋጀትና ለማሰራጨት ታቅዶ 3 በማዘጋጀት የማሰራጨት ስራ ተሰርቷል፡፡

ተቋሙ የራሱ የሆነ ቤተ-መጽሐፍት እንዲኖረው ለማድረግ ግብዓት የማሰባሰብና ልምድ የመቅሰም ስራ የተሰራ ሲሆን በአሁኑ ሰዓት ቤተ-መፅፍቱ ለተጠቃሚዎች አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል፡፡ በተጨማሪም ክፍትና ዲጂታል ቤተ-መጽሃፍት ለመጀመር ግብዓት የማሰባሰብ ተግባር እየተከናወነ

ሲሆን በዚህ መሰረት ከፎረም ኦፍ ፌዴሬሽን 42 መጽሀፍት እንዲሁም ከፌዴራሊዝምና ግጭት አስተዳደር ሚኒስትር ዴኤታ 82 መጽሃፍት ማሰባበሰብ እና ከመከላከያ ሚኒስቴር ‹‹የዕለት ቀለበት›› የሚል 20 መጽሐፍት በመግዛት ቤተመጽሃፍቱን ማጠናከር ተችሏል። የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ከ4ኛ ዙር ጀምሮ በአቀባባል፣ በስልጠና፣ ምርቃት እና ስምሪት የኮሙንኬሽን ስራዎች ተሰርቷል። እንዲሁም የተቋሙ አመራሮች በየደረጃ ግንዛቤ የማስጨበጥ ስራዎችን መስራት ተችሏል ።

## 1.7. የስነ ምግባርና ፀረ ሙስና የክትትል ሥራዎችን ማጠናከር፤

ባለፈው ዓመት የአመራሩና የሰራተኛው የሃብት ምዝገባ በማንዋል ሙሉ ለሙሉ ምዝገባ የተደረገ ሲሆን፤ አሁን ላይ ምዝገባው በኦንላይን ሲስተም እንዲደረግ በተቀመጠው አቅጣጫ መሰረት የከፍተኛ አመራሩን የሃብት መጠን መረጃ በማሰባሰብ በኦንላይን የሃብት ምዝገባ ማካሄድ ተችሏል፡

የተቋሙ ሰራተኞችና አመራሮች በጠቅላላ የትምህርት ማስረጃ ህጋዊነት የማረጋገጥ ስራ ከየተማሩበት ዩኒቨርሲቲው የተጣራ መረጃ ተሰብስቧል::

በበጀት ዓመቱ ሁለት መድረኮች በማዘጋጀት የስነ ምግባር ስልጠና ለሰራተኞች ለመስጠት በታቀደው መሰረት እንድ መድረክ በማዘጋጀት ለሰራኞች ስልጠና ተሰቷል።

በተቋሙ ብልሹ አሰራርን ለመከላከል እንዲቻል በልዩ ሁኔታ ክትትል እየተደረገ ያለ ሲሆን በዚህ አግባብ ከላፕቶፕ ግዥ ጋር ተያይዞ ችግር ባለባቸው ሰባት የተቋሙ ሰራተኞች ላይ ቀላልና ከባድ የዲስፒሊን እርምጃ ተወስዷል። ከሌሎች ብልሹ አሰራሮች ጋር ተያይዞ ተጠያቂነት የማስፈን ስራ እየተሰራ ይገኛል። በአጠቃላይ ቀደም ሲል የነበሩ ብልሹ አሰራሮችን (ለአብነት ከግዥና ከአበል ክፍያ) ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን በልዩ ትኩረት የማስተካከል ስራዎች ተሰርቷል።

በዓለም አቀፍ ደረጃ ለ19ኛ በሀገራችን ደግሞ ለ18ኛ ጊዜ “ሙስናን መታገል በተግባር” በሚል መሪ ቃል በተቋማችን በዓሉን በድመቀት ማክበር ተችሏል። በተጨማሪም አለም አቀፍ የፀረ ሙስናን ቀን አስመልክቶ ከኢንሳ፣ ከአርቴፍሻል ኢንተለጀንሲ እና ከፀረ ሙስነ ኮሚሽን ጋር በጋራ በመሆን በዓሉን በድምቀት ማክበር ተችሏል።

የተቋሙን ጥቅም ከማስከበር አንጻር ከተለያዩ ድርጅቶችና ግለሰቦች የቀረቡት ክሶችን በፍርድ ቤት እና በሌሎች ፍትህ አካላት ተቋሙን በመወከል በህግ አግባብ ክርክር ማድረግ ተችሏል። እንዲሁም የተለያዩ የህግ ሰነዶችን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ማዘጋጀት ተችሏል። ለአብነት የሃገር ውስጥ መፈናቀልን ለመከላከልና ጥበቃና ድጋፍ ለማድረግ በሚዘጋጀው ረቂቅ አዋጅ ላይ መሳተፍ ተችሏል።

የኢትዮጵያ ርሆቦት ቤተክርስትያን መ/ቤታችን በሃይማት ጣልቃ ተገብቶብኛል ክስ በተመለከተ የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን ከመረመረ እና ካከራከረን በኋላ ቀደም ሲል ውሳኔ ወደ ሰጠው የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ግራ ቀኙን ያከራክር ብሎ በመወሰኑ በፌ/ከ/ፍ/ቤት ክርክር እያደረግን ሲሆን ጉዳዩ በቀጠሮ ላይ የሚገኝ ነው።

### 1.8. የሴቶችና ማሕበራዊ ተሳታፊነትንና ተጠቃሚነትን ማሳደግ፤

በመ/ቤታችን በጽዳት ሰራተኝነት ተመድበው በማገልገል ላይ ያሉት 20 ሴት ሰራተኞች ራሳቸውን መደጎም እንዲችሉ ተቋሙ ባደረገላቸው የገንዘብ ድጋፍ በትርፍ ጊዜያቸው የሻይ ቡና ሥራ እንዲጀምሩ ተደርጓል፡፡ በዚህም በመጠኑም ቢሆን ማህበራዊ ችግሮቻቸውን ማቃለል ተችሏል፡፡

እንዲሁም ለተቋሙና ሌሎች ተቋማት ሠራተኞች የጊዜ፣ ወጪ እና ምቹ የስራ ካባቢን ከመፍጠር አኳያ አስተዋጽኦ አበርክቷል ፡፡

የህጻናት ማቆያ በማደራጀት ሰራተኞች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡ ከጤና ሚኒስቴር የተለያዩ የህፃናት መጫወቻዎችን በድጋፍ በማግኘት ለህፃናት ማቆያው እንዲውል ተደርጓል፡፡

የሴት ሰራተኞችን አቅም ግንባታ ስልጠና በተመለከተ ለ100 ሴት ሰራተኞች በተለያዩ ርዕሶች ላይ ስልጠናዎችን ለመስጠት ታቅዶ ለ75 ሴቶች ሰልጠና ጠሰጥቷል፡፡

12 ሴት ሰራተኞች ወደ አመራር ለማብቃት እንዲቻል በTransformational Leadership፣ Team building and Commuication Skills ላይ ስልጠና እንዲወስዱ ተደርጓል፡፡

### 1.9. የበጎ አድራጎት እና የማህበረሰብ አገልግሎት ሥራዎችን ማሳደግ፤

ሚኒስቴር መ/ቤታችን ከሚያከናውናቸው የክረምት በጎ ፈቃድ አገልግሎት ሥራዎች የቂርቆስ ክ/ከተማ ወረዳ ሁለት 4 ቤቶች እንዲሁም በኦሮሚያ ክልል ባሌ ዞን ጎባ ከተማ 10 ቤቶች ለመስራት ታቅዶ የህብረተሰቡን ተሳትፎ በማከል 23 ቤቶች በድምሩ 27 ቤቶች ግንባታ እና እድሳት ተጠናቆ ባለቤቶቹ ወደ ቤታቸው እንዲገቡ ተደርጓል፡፡ በዚህም የአካባቢው ማህበረሰብና የዞንና የከተማ አስተዳደሩ ከሚኒስቴር መ/ቤታችን ጋር ያለው ትስስርና አብሮነት ከመጠናከሩም በላይ በከፍተኛ የኑሮ ጫና ውስጥ የነበሩ ዜጎቻችንን ችግር መቅረፍ ተችሏል፡፡ እንዲሁም በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል አሶሳ ከተማ የ9 አረጋዊያን እና አቅመ ደካሞች ቤት እድሳ ስራ ተጀምሯል፡፡

ሚኒስቴር መ/ቤታችን ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ጋር በመተባበር ግምቱ 90,000 ብር የሆነ ሁለት ዊልቸር እንዲሁም ከግለሰቦች በድጋፍ የተገኘ 57 ብርድ ልብስ በማሰባሰብ ለአቅመ ደካማ የህብረተሰ ክፍሎች በስጦታ አበርክቷል፡፡ በተጨማሪ በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ ላሉ 100 ተማሪዎች የቦርሳ፣ የደብተርና ስክርቢቶ ድጋፍ ተደርጓል፡፡ ለመከላከያ ሰራዊት እገዛ ለማድረግ ሰላሳ የተቋሙ አመራርና ሰራተኞች የደም ልገሳ አድርገዋል፡፡

## II. የቁልፍ ውጤት አመልካቾች (KPI) ላይ የተመሰረተ የዕቅድ አፈጻጸም ተግባራት፤

## 2. አዎንታዊ ሰላም ማሳደግ ተግባራት፤

### 2.1. በአዎንታዊ ሰላም ግንባታ ያደገ የሃይማኖት ተቋማት ተሳትፎና የአገልግሎት አሰጣጥ፤

#### 2.1.1. በሃማኖት ተቋማቶች ፍላጎት መሰረት በተደረገ ድጋፍ ያደገ የሃይማኖት ተቋማት ውስጣዊ ሰላም፤

በተለያዩ ሃይማኖት ተቋማት ውስጠ ሰላም እንዲሰፍን፣ በአመራሮቻቸው መካከል የተከሰተው የውስጥ አለመግባባት እንዲፈታ፣ በመተዳደሪያ ደንባቸው መሠረት እንዲሰሩ እና ማስተካከያ እንዲያደርጉ ምክክር የተደረገ ሲሆን፡-

- ✓ በኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት መጅሊስ አመራሮች ምርጫ ዲሞክራሲያዊ ሆኖ እንዲጠናቀቅ ድጋፍ በመደረጉ ሰላማዊ የስልጣን ሽግግር ተደርጓል፡፡ እንዲሁም በአማራ ክልል እና በፌደራሉ የመጅሊስ አመራር የነበረው ልዩነት በሰላም ሚ/ር የበላይ አመራር እና በአማራ ክልል አመራር ድጋፍ ተደርጎ ችግሮቻቸውን በውይይት ፈተው በአማራ ክልል አዲስ የመጅሊስ አመራር ምርጫ ተካሄዶ ሰላማዊ የስልጣን ርክክብም ተደርጓል፡፡
- ✓ የምስራቅ ጎጃም ሀገረ ስብከት በቅባት እምነት ተከታዮች እና በተዋህዶ እምነት ተከታዮች መካከል የነበረው ችግር በቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔ አዲስ ጳጳስ ተመድቧል፡፡ አዲስ የተመደቡት ጳጳስና የመንግስት አካል በሰሩት የተቀናጀ ስራ ጥያቄ ከነበራቸው 8 ወረዳዎች ውስጥ 7ቱ የተስማሙ ሲሆን አንዱ ወረዳ (ግንደወይን) ተጨማሪ ስራ እንደሚጠይቅ ከክልሉ ጋር የጋራ ግንዛቤ ተይዟል፡፡ ይህ በመሆኑም መካረሮች እና ውጥረቶች ቀንሰዋል፡፡ እንዲሁም በአዊ ዞን ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ እና በምዕመኑ መካከል የነበረውን ችግር ለመፍታት ቅዱስ ሲኖዶስ ኮሚቴ አዋቅሮ ከላከ በኋላ በጊዜዊት ጳጳሱን በማንሳቱ የነበረው ውስጣዊ ውጥረትና አለመግባባት ተቀርፏል፡፡ በባህር ዳር በተደረገው ሃይማኖት ለሰላም ኮንፈረንስ ይህን ማረጋገጥ ተችሏል፡፡
- ✓ የተለያ የሃይማኖት ተቋማት በተደረገላቸው የአመራር ድጋፍ መሰረት በመተዳደሪያ ደንባቸው መሠረት በጠቅላላ ጉባዔ ውሳኔ እንዲያገኙና በውስጣቸው ያለው የአሰራርና የአመራር ሁኔታ አንዲጠናከር ድጋፍ ተደርጓል፡፡ (ለአብነትም፡ ዘሪዲም ክራይስ ኦፍ ጋድ፣ ላይት ቤረርስ ሚኒስቲሪ፤ የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ሮሆቦት ቤተክርስቲያን ይጠቀሳሉ)
- ✓ በኦርቶዶክስ ውስጥ የነበሩ ክፍተቶች የባሰ ቀውስ እዳይመጣ መከላከል ተችሏል፡፡ የሀገር ሽማግሌዎች፣ ከፍተኛ የመንግስት የሥራ ሃላፊዎችና አመራሮች ያደረጉት ጥረት እንደተጠበቀ ሆኖ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ያጋጠማቸው የውስጥ አለመግባባት ችግሩ በእርቅ እንዲፈታ በመደረጉ የራሳቸውን ውስጣዊ ችግሮች መፍታት ችለዋል፡፡

### 2.1.2. ለሃይማኖት ተቋማቶች በተሰጠ ድጋፍ ያደገ የሃይማኖት ተቋማቶች የእርስ በእርስ መቻቻል፤

በተለያዩ ሃይማኖት ተቋማት አና አመራሮች መካከል የእርስ በእርስ መቻቻል እንዲጎለብት በአዋሳ ከተማ 220 እና በድሬደዋ ከተማ 140 በድምሩ ለ360 ለሚሆኑ የሃይማኖት እና የመንግስት ተቋማት አመራሮች እና ታዋቂ ግለሰቦች በተገኙበት የሃይማኖት አስተምሮዎች ለሰላም ግንባታ ያላቸውን ሚና እና ሃይማኖት እና መንግስት ያላቸውን ግንኙነት ማጠናከር በሚሉት ርዕሶች ዙሪያ ስልጠና እና ምክክር በማድረግ የጋራ ግንዛቤ ተይዟል፡፡ አፈጻጸሙም 90% ሲሆን ከዚህ ውስጥ የሴቶች ተሳትፎ 11% ነው፡፡ በመድረኩም በሀይማኖት ተቋማት መካከል አለመግባባቶችና ችግሮች ሲያጋጥሙ በጋራ ጉባኤያቸው አማካይነት በምክክር መፈታት እንዳለበት የጋራ መግባባት ላይ ተደርሷል፡፡

ስተርሊንግ ፋውንዴሽን በሰጠው ድጋፍ መሰረት በአራት የክልል ከተሞች **ሃይማኖት ለሰላም** በሚል ኮንፍረንስ ለማካሄድ ታቅዶ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ (ሚዛን አማን)፤ በአማራ ክልል (ባህር

ዳር)፤ ኦሮሚያ (ጅማ)፣ ቤ/ጉሙዝ (አሶሳ) እና በሶማሌ ክልል (ጅግ ጅጋ) ማካሄድ ተችሏል፡፡ በነዚህ 5 ክልሎች 435 ያህል ተሳታፊዎች ለማወያየት ታቅዶ 437 ያህል (100.%) ተከናውኗል፡፡ በመድረኩም በ3 አጀንዳዎች (ሃይማኖቶች በውስጣቸው፣ በመካከላቸውና ከመንግስት ጋር ስላላቸው ግንኙነት ዙሪያ ምክክር ተካሄዷል፡፡ በሁሉም መድረኮች ላይ በተደረጉ ውይይቶች ከተሳታፊዎች ከተነሱት አንኳር ነጥቦች ለአብነት የሚከተሉት ቀርበዋል፡፡

- ✓ ከፋ ዞን ቦንጋ ከተማ ውስጥ ሚጣ በምትባል አካባቢ ያሉ 4 ቤተ እምነቶች ተደማምጠውና ተከባብረው የእምነት ስርዓታቸውን እያከበሩ መሆኑ፣
- ✓ የከተማ ፕላን እና ካርታ አሰጣጥ ዙሪያ አሳታፊ በሆነ መንገድ በህዝብ እየተገመገመ ውሳኔ እየተሰጠበት መሆኑ (የደ/ም/ኢት የከተማ ፐላን ቢሮ)፣
- ✓ ሁሉም ቤተ-እምነቶችና አባቶች ከዘር፣ ከቋንቋ ልዩነቶች ወጥተን ሃይማኖታዊ ትዕዛዛትን መከተል እንዳለባቸው አስተያየት መሰጠቱ፣
- ✓ መንግስት በቤተ-እምነቶች ውስጥ ችግር ሲፈጠር ለመደገፍ የሚያደርገው ጥረት (ከአማራ ክልል የደሴ አመራር በአርያቱ ተመስግኗል፣)
- ✓ በመንግት መዋቅር ውስጥ ግለሰቦች በሚፈጥሩት አድሎአዊ አሰራር ምክንያት የሃይማኖቱ ተከታዮች እርስ በርስ መጠራጠር እና ግጭት ውስጥ እንዳይገቡ የዕምነት መሪዎችን አሳትፎ መንግሰት እርምጃ መወሰድ እንዳለበት፡፡

### 2.1.3. የጎለበተ የመንግስትና የሃይማኖት ተቋማት መልካም ግንኙነት፤

የኢትዮጵያ ሃይማኖት ተቋማት ጉባዔ ዕቅድ አፈጻጸም በመገምገም ድጋፍ የተደረገ ሲሆን የታዩ ጥንካሬዎች እንዲቀጥሉ እንዲሁም ክፍተቶች እንዲታረሙ የጋራ መግባባት ላይ ተደርሷል፡፡ መተዳደሪያ ደንባቸው መሠረት እንዲሰሩ አቅጣጫ ተቀምጧል፡፡

የሃይማኖት ተቋማት እና መንግስት መልካም ግንኙነት ለማጠናከር እንዲቻል 101 ለሚሆኑ ከሁሉም ክልሎች እና ከተማ አስተዳደሮች የሰላምና ጸጥታ ቢሮ እና የሃይማኖት ጉዳዮች ዳይሬክተሮች በተገኙበት እቅድ ኦሬንቴሽን እና በስራ ክንውን ዙሪያ ግምገማ ተካሄዷል፡፡

ሃይማኖት ነክ የመልካም አስተዳደር ቅሬታዎችን ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን እንዲፈቱ ክትትል የተደረገ ሲሆን ከቀረቡ 61 ቅሬታዎች መካከል 43 ተፈተዋል፡፡

የሃይማኖት እና የእምነት ነጻነት መብት አተገባበር በተሻለ የሕግ ማዕቀፍ እንዲመራ ለማድረግ በተያዘው እቅድ መሰረት አዋጅ ለማዘጋጀት የሚረዳ መነሻ ጥናት እየተዘጋጀ ይገኛል፡፡ ለአዋጁ ዝግጅትም ከወዲሁ በጥናት የተደገፈ መረጃ ለማሰባሰብ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የህግ ትምህርት ክፍል ጋር በቅንጅት እየተሰራ ይገኛል፡፡

የኢትዮጵያ ሃይማኖት ተቋማት ጉባዔ ዕቅድ አፈጻጸም ግምገማ በማድረግ እና በመተዳደሪያ ደንባቸው መሠረት እንዲሄዱ ጉባዔውን ለማጠናከር የሚያስችል ከ7ቱም የሃይማኖት ተቋማት የበላይ ጠባቂ አባቶች እና ቦርዶች ጋር የሰላም ሚ/ር የበላይ አመራሮች በተገኙበት የምክክር መድረክ ተካሄዶ የመፍትሄ አቅጣጫ ተቀምጧል፡፡ ከጉባዔ አባላት የተወከሉ አካላትን ኮሚቴ በማቋቋም ዕቅድ አውጥተው ወደ ሥራ እንዲገቡ ድጋፍ ተደርጓል፡፡

ጎንደር ከተማ (በአረዳ እና ማራኪ ክ/ከተሞች መካከል በሚገኘው በጊዮርጊስ የኦርቶዶክስ የፀበል ቦታ እና ሃጅ ኤልያስ ተብሎ በሚጠራው በመካነ መቃብር መካከል በነበረው የወሰን ችግር ምክንያት ይከሰት የነበረው ግጭት የከተማ አስተዳደሩ የሁለቱ እምነት ተቋማት አባቶች በተገኙበት ካርታ ፕላን ርክብብ ስነስርአት ተካሂዶ ችግርን ለመፍታት መቻሉ፡፡

በኦርቶዶክስ ዕምነት መካከል ተከስቶ በነበረው ችግር የመንግስት አመራሮች ከዕምነቱ መሪዎች እና ከተቋማቱ ጋር በመሆን ድጋፍ በማድረጋቸው አንጻራዊ ሰላም ተፈጥሯል፡ ችግሮች ተፈተውም ነገሮች ወደነበሩበት ተመልሰዋል፡

በጅግጅጋ ከተማ (ሶማሌ ክልል) በሃይማኖት መቻቻል ዙሪያ መልካም ተሞክሮ የተገኘበት ሲሆን በክልሉ የሃይማትን አጀንዳ በትኩረት በመያዝ በየጊዜው እያወያዩ ሲሆን ሁሉም የዕምነት መሪዎች በመመካከር ችግሮችን ይፈታሉ፡ ያስታርቃሉ፡፡ ችግር የፈጠሩ ግለሰቦች በአካባቢው ባህል መሰረት ካሳ እንዲከፍሉ ያደርጋሉ፡፡

### 2.1.4. የሃይማኖት ተቋማት በህብረተሰብ ሰላም ግንባታ ያላቸው ተሳትፎና ሚና ማሳደግ፤

የሃይማኖት ተቋማት አባቶች እና ተቋማቱ በጦርነት ለተጎዱና በግጭት ምክንያት ለተፈናቀሉ ወገኖች ተገቢውን ድጋፍ ያደረጉ ሲሆን፡፡ በዚህም፡

- ✓ በአማራ ክልል ሰሜንና ደቡብ ወሎ እንዲሁም ሰሜን ጎንደር፣ በጦርነቱ ከቤት ንብረታቸው ለተፈናቀሉ የገንዘብና ልዩ ልዩ ድጋፎች ተደርጓል፡፡
- ✓ በቤኒሻንጉል ጉምዝ ክልል በመተከል ዞን እና ካማሽ ዞን በጦርነት ምክንያት የተፈናቀሉት ወደ ቀያቸው በመመለስ እና በማስታረቅ ስራ የሃይማኖት አባቶች ተሳትፈዋል፡፡
- ✓ በጎንደር ከተማ በእስልምናና በኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች መካከል የተከሰተው ግጭት በሽምግልና እንዲፈታ የሁለቱም የሃይማኖት አባቶች ድጋፍ አድርገዋል፡፡
- ✓ የሃይማኖት አባቶች በኦሮሚያ ገላን ከተማ በኦርቶዶክስና መካነኢየሱስ እምነት ተከታዮች መካከል የተፈጠረውን ግጭትን በምክክር እና ውይይት እንዲፈታ ጥረት አድርገዋል፡፡
- ✓ በጉራጌ ዞን ወልቂጤ ከተማ በአካባቢው ማህበረሰብ እና በመንግስት መካከል የተፈጠረውን ግጭት ለማርገብ በአካባቢው ያሉ የሃይማኖት መሪዎች የነበረውን ውጥረት እንዲረግብ በማድረግ የአርያነት ሚና ተጫውተዋል፡፡
- ✓ በድሬዳዋ በመስጊድ ኮሚቴዎች መካከል (በነባርና በአዲስ ኮሚቴዎች) የነበረው መካረር በእርቅና በይቅርታ እንዲፈታ የሙስሊም አባቶችና የጎሳ መሪዎች ድጋፍ አድርገዋል፡፡
- ✓ በሻሸመኔ ከተማ የሀይማኖት አባቶችና የሀገር ሽማግሌዎች በጋራ የሰላም ኮሚቴ መስርተዉ ለከተማቸው ሰላም እየሰሩ ይገኛሉ፡፡

### 2.1.5. ለሃይማኖት ተቋማት የተሰጠ የፈቃድ ምዝገባ እድሳትና ተጓዳኝ አገልግሎት፤

ለ7 አዳዲስ ተቋማት የህጋዊ ማረጋገጫ ሠርተፊኬት ለመስጠት ታቅዶ ለ15 ተሰጥቷል፡፡ ለ80 ነባር የሃይማኖት ተቋማት የምዝገባ የሠርተፊኬት የእድሳት አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ 82 ተከናውኗል፡ እንዲሁም ለ450 የሃይማኖት ተቋማት ልዩ ልዩ ተዛማጅ አገልግሎቶችን ለመስጠት

ታቅዶ 350 ተከናውኗል፡፡ ከላይ የተሰጡት አገልግሎች አማካይ አፈጻጸም 83% ሲሆን በውጤቱም የሃይማኖት ተቋማት ህጋዊ እና ሰላማዊ ሆነው እንዲንቀሳቀሱ አግዟል፡፡

## 2.2. በማህበረሰብ ተሳትፎ ያደገ አዎንታዊ ሰላም፤

### 2.2.1. በማህበረሰብ ምክክር ያደገ የዜጎች ሰላማዊነትና ችግር ፈቺነት፤

የክልል ሰላምና ፀጥታ ቢሮ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች፣ የትምህርት እና የሲቪል ሰርቪስ ቢሮ ተወካዮች በድምሩ 102 (የሴቶች ተሳትፎ 14.7%) አመራርና ባለሙያዎች በተገኙበት የማህበረሰብ እና በሲቪል ሰርቪስ ሴክተር ምክክር መድረኮች ውጤታማነት ላይ እና በየክልሉ እየተሰሩ ያሉ የሀይማኖት ጉዳዮች ስራ ጠንካራና ደካማ ጎኖችን ግምገማዊ ምክክር ማካሄድ ተችሏል፡፡ በመድረኩም የሀረሪ ክልል የማህበረሰብ ተኮር ምክክር አፈጻጸም ተሞክሮ ቀርቦ ትምህርት ተወስዶበታል፡፡

ከክልሎች በተወሰደው የማህበረሰብ ተኮር የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት መሠረት ከደቡብ ክልል፣ ከሱማሌ እና ከአፋር ክልሎች በስተቀር በሌሎቹ ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች በአካባቢያዊ እና በወቅታዊ ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ በመወያየት የመፍትሔ አቅጣጫዎችን አስቀምጠዋል፡፡ በሂደቱም 8,178,725 የማህበረሰብ ክፍሎች ለማሳተፍ ታቅዶ ወንድ 4,796,087 ሴት 2,902,689 ድምር 7,698,949 ሲሆን አፈጻጸሙም 94.13% ነው፡፡ የሴቶች ተሳትፎም 35.5% ነው፡፡ በማህበረሰብ ምክክር መድረኮች የመጡ ለውጦች ለዓብነት ያህል፡-

- ✓ የማህበረሰብ ምክክር አንዳንድ ክልሎች (ሀረሪ ክልል) በአግባቡ በመጠቀም የህብረተሰቡን ጥያቄዎችና ሀሳቦችን በማዳመጥ በተወሰነ ደረጃም ቢሆን የሚመለከታቸው አካላት ምላሽ እንዲሰጡበት እየተደረገ ይገኛል፡፡
- ✓ መድረኩን ባካሄዱ ክልሎች ችግሮችን ማህበረሰቡ በራሱ አቅም እየተፈታና የመፍትሔው ባለቤት እየሆነ መምጣቱ
- ✓ እርስ በእርስ ሃሳብን የሚለዋወጡበትና የሚተዋወቅበት መድረክ እየሆነ መምጣቱ፣
- ✓ የምክክር ጽንሰ-ሀሳብ በማህበረሰቡ፣ በአመራሩና በአስተባባሪ ባለሙያዎች መካከል እያደገ መምጣቱ፤
- ✓ በተለይ በአካባቢ ሰላምና ፀጥታ ስራዎች (የአካባቢውን ሰላም በሮንድ መጠበቅ፤ ፀጉረ ልውጦችን መከታተል) እና በአካባቢ ጥበቃና የልማት ስራዎች ላይ የነቃ ተሳትፎ እያደረጉ መሆናቸው ለአብነት (ሀረሪ ክልል፣ ሲዳማ ክልል፣ አዲስ አበባ እና ድሬዳዋ ከተሞች)
- ✓ የምክክር መድረኮቹ ባመጡት የለውጥ ጅማሮ ለሕገወጥ ተግባራት ሊውሉ የነበሩ የጦር መሣሪያዎችን ወደ መንግስት ገቢ የተደረገበት ሁኔታ መታየቱ፤ (አማራ ክልል)

ከላይ የተጠቀሱ ለውጦች እንደተጠበቁ ሆነው ለየት ባለ መንገድ አንደ ትምህርት የሚወሰዱ 2 ክልሎችን ማለትም የደ/ምዕራብ ኢትዮጵያ እና የአማራ ክልልን ዘርዘር በማድረግ በማህበረሰብ ምክክር ያሳዩትን ተነሳሽነትና ያመጡትን ለውጥ አንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

**ደ/ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል፡** ለበርካታ ጊዜያት ሸፍተው የቆዩ ከ58 በላይ ወጣቶች በማህበረሰብ ምክክር አማካኝነት ከነትጥቃቸው ወደ ሰላማዊ ህይወት እንዲመለሱ ተደርጓል፡፡ በዚህ የማህበረሰብ ምክክር ወቅት የጎላ ድርሻ የነበራቸው ሽማግሌች፤ የሃይማኖት አባቶች (በተለይ ቴፒ አካባቢ)፤ የጎሳ መሪዎች ከፍተኛ አበርክቶ አድርገዋል፡፡

በምዕራብ ኦሞ ዞን (በኛጋቶም እና ሱርማ ወረዳዎች) የማህበረሰብ ምክክር ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን በማስቀርት ተጨባጭ ለውጦችን አምጥቷል፡፡ ለአብነት፡ አንድ ወንድ ወጣት ሚስት ለማግባት ክላሽ ከብቶች መስጠት ይጠበቅበት ነበር፡፡ ይህን ለማስቀረት ከማህበረሰቡ ጋር በተደረገ ውይይት (በተለይም ከመኤሚት ማህበረሰብ ጋር) በተደረገው ሰፊና ተደጋጋሚ ውይይት ክላሽ እና ከዚህ በፊት በባህሉ የሚጠየቀውን ከበት መስጠት ሳይጠበቅበት ጋብቻ እንደተፈቀደ ስምምነት ላይ በመደረሱ ይህ በህግ እንዲደገፍ ለማድረግ ጥያቄው ከቀበሌ ጀምሮ በማንሳት በአሁኑ ሰዓት ለክልል ም/ቤት ሊቀርብ ችሏል፡፡ የሱሪና የዴሮ ወረዳዎች በተደጋጋሚ ወደ ግጭት ገብተው የነበሩ ሲሆን በአሁኑ ሰዓት በተደረገው የማህበረሰብ ምክክር የኩታ ገጠም ቀበሌዎችን ወደ ሰላማዊነት እንዲመለሱ ተደርጓል፡፡

**አማራ ክልል** ከ4,000 በላይ ግለሰቦች በጦርነቱ ወቅት ከመከላከያ፤ ከፌዴራል ፖሊስ፤ ከክልሉ ልዩ ሓይል እየከዱ ወደ ማህበረሰቡ ከተሰወሩና ኢ-መደበኛ አደረጃጀት በመጠቀም ማህበረሰቡን ሲያውኩ ከቆዩ በኋላ ማህበረሰቡ በራሱ አደረጃጀት እና በውይይቱ በማጋለጥ ፡

- ✓ መሳሪያቸውን ለመንግስት እንዲያስረክቡ አድርጓል፡፡
- ✓ በማህበረሰብ ውይይት በተደረገው ርብርብም ኢ-መደበኛ አደረጃጀት ተጠቅሞ ህዝብን የማወክ አዝማሚያ ቀንሷል፡፡

ማህበረሰቡ በራሱ አነሳሽነት የሰፈር አደረጃጀት እና የብሎክ አደረጃጀት በመያዝ እርስ በእርስ የመማማር እና የመገማገም እንዲሁም የመቆጣጠር አካሄድን በመከተል ውጤታማ እየሆኑ ነው፡፡ ለአብነት፡

- ✓ በጎንደር ከተማ በሚደረገው የማህበረሰብ ውይይት አማካኝት ከመንግስት ታጣቂ ውጭ አንድም ግለሰብ ህገ-ወጥ መሳሪያ ይዞ የሚንቀሳቀስ ካለመኖሩም በተጨማሪ ከዚህ በፊት የነበረው ስርዓት አልባ ተኩስ በከተማው ውስጥ የለም፡፡ እንዲሁም በዚሁ ከተማ ታዋቂ ግለሰቦች፤ የሃይማኖት አባቶች እያስተባበሩት የሰላም ካውንስል አደረጃጀት ተፈጥሮ ሰላማቸውን እየጠበቁ ነው፡፡
- ✓ በህግ ማስከበር ዘመቻ ወቅት አብዛኛው የጸጥታ ሃይል ወደ ግንባር በዘመተበት ወቅት ማህበረሰቡ ራሱን አደራጅቶ እና ከአካባቢው አስተዳደር ጋር በመቀናጀት ማህበረሰቡ ራሱን ከመጠበቅም አልፎ የመንግስት ተቋማትን በመጠበቅ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡

በማህበረሰብ ውይይት የተሻለ አፈፃፀም ያላቸው ዞኖችና ወረዳዎች በተመለከተ (ሰሜን ወሎ፣ ሰሜን ጎንደር ዞን (ዳባት እና ደባርቅ ዙሪያ ወረዳ)፣ ዋግኽምራ ብሄረሰብ ዞን እና ሰሜን ሸዋ ዞን (አሳግርት፣ ምንጃር ሸንኮራና አንፆኪያ ገምዛ ወረዳዎች) የተሻለ ተሞክሮ ያላቸው ሲሆን በእነዚህ አካባቢዎች በመንግስትና ማህበረሰቡ መካከል መተማመን ሊፈጠር ችሏል፡፡ ለአብነትም፡

- ✓ በህብረተሰቡ ውስጥ ከአፈር ማዳበሪያ አቅርቦትና ዋጋ መጋነን ምክንያት የተዛቡ አመለካከቶችን በውይይት በማስረዳት መግባባት ላይ ተደርሷል፡፡
- ✓ ግድያ ፈፅመው ከህግ የራቁ ወንጀለኞች ለህግ የማቅረብና የማስታረቅ ስራ ተሰርቷል፣
- ✓ ህብረተሰቡ የሰላም ባለቤት በመሆን በየአካባቢው ተደራጅቶ የጥበቃና ሌሎች የጸጥታ ስራዎችን ማከናወን ችሏል፡፡ በዚህም የተዘረፉ ንብረቶችንና ፀጉረ ልውጦችን መቆጣጠር ተችሏል፡
- ✓ የህብረተሰቡን የጋራ መጠቀሚያ/የወል/መሬቶች ከወረራ መከላከልና መጠበቅ የተቻለ ሲሆን የተወረሩትንም የማስመለስ ስራ ተሰርቷል (በሰሜን ጎንደር ዞን ከ17 ሄክታር በላይ በህገ ወጥ መንገድ የተያዙ መሬቶችን ማስለቀቅ ተችሏል)፣

በተጎራባች ብሄረሰቦች መካከል የሚነሱ አለመግባባቶችን በውይይት መፍታት ተችሏል፡፡ ለአብነትም፡

- ✓ በሰሜን ሸዋ እና ኦሮሞ ብሄረሰብ ዞኖች ተጎራባች ወረዳዎች መካካል የሚነሱ አለመግባባቶች በውይይትና በሰላም መፍታት ተችሏል፡
- ✓ ተቋርጠው የነበሩ እንደ ሰንበቴ ገበያ ያሉ የማህበራዊ አገልግሎት መስጫ ተቋማት ወደ ነበሩበት ለመመለስ ተችሏል፡፡
- ✓ በግጭት ምክንያት ተዘግተው የነበሩ መንገዶች ተከፍተዋል፣
- ✓ ሳይታረሱ የቀሩ መሬቶች እንዲታረሱና ለልማት እንዲውሉ ተደርጓል፡፡

በማዕከላዊና ምዕራብ ጎንደር የሚንቀሳቀስ በርካታ የቅማንት ጽንፈኛ ቡድን በሰላም ካውንስልና በውይይት ለመንግስት እጃቸውን ሰጠው ወደ ህብረተሰቡ እንዲቀላቀል ተደርጓል፡፡ በዚህም ከጎንደር መተማ አካባቢ ይታይ የነበረው የፀጥታ ችግር አሁን ሙሉ በሙሉ ሰላማዊ ሆኗል፡፡ የሰው እገታ ወንጀል በእጅጉ ቀንሷል፣

**ጋምቤላ ክልል፡-** በአኙዋክና በኑዌር መካከል የነበረው ግጭት እና ውጥረት እየቀነሰ መምጣትና አንጻራዊ ሰላም መስፈኑ፣

**ቤኒሻንጉል/ጉሙዝ ክልል፡-** በክልሉ ውስጥ በተለያየ ምክንያት የተፈናቀሉ ወገኖች ወደ ነበሩበት ቦታ እንዲመለሱ መደረጉ፣ የታጠቁ ሃይሎች ትጥቃቸውን ፈተው ወደ ማህበረሰቡ እንዲቀላቁ መደረጉ፣

**ሲዳማ፡** በኦሮሚያና ሲዳማ አዋሳኝ አካባቢዎች የግጭት መንስኤ የነበሩ የመሬት አጀንዳዎች በሁለቱ ጎረቤት ማህበረሰቦች በተደረገ ምክክር በጋራ እንዲጠቀሙ የተደረገ ሲሆን ከ30ሺ በላይ ችግኝ ተክለውም በጋራ እየተንከባከቡና እየጠበቁ ይገኛሉ፡፡ ከዚህ በፊት የነበረውንም ችግር ፈተው በጋራ ተግባብተው እየተጠቀሙ ነው፡፡

- ✓ በሃዋሳ ከተማ የነበረን የነጠቃና ዝርፊያ ችግርን ከምክክር በኃላ በተፈጠረ የሮንድ አደረጃጀት ሌቦችን የማጋለጥ ስራ በመሰራቱ ፊት የነበረው ችግር ሊቀረፍ አስችሏል፡
- ✓ በሚኒስትሮች ምክር ቤት የሰላም ቀን እንዲከበር በተቀመጠው አቅጣጫ መሰረት ከሴቶችና ማህበራዊ ሚ/ር እና ከፍትህ ሚ/ር ጋር በጋራ **"ሠላም ለኢትዮጵያ"** በሚል መሪ ቃል በሀገር

አቀፍ ደረጃ በተለያዩ ዝግጅቶች በዓሉ በደመቀ ሁኔታ ተከብሯል፡፡ በወቅቱም በርካታ የመንግስት ከፍተኛ ኃላፊዎች በተገኙበት የሰላም መልዕክቶች በማስተላለፍ ዜጎች ስለ ሰላም እንዲወያዩ አስችሏል፡፡ እንዲሁም በወቅቱ የፓናል ውይይት ማካሄድ፣ የእግር ጉዞ የማድረግ፣ የኪነ ጥበብ ስራዎች የማቅረብ፣ የሰላም ፖል የመትከል እንዲሁም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሰላም መንገድ የመሰየም ስራዎች ተሰርተዋል፡፡ በተጨማሪም ለሰላም ስራዎች በጎ አስተዋጽኦ ላበረከቱ ተቋማት/ቡድኖች እውቅናና ሽልማት ተሰጥቷል፡፡ በተመሳሳይ ከአፋር፣ አማራና ኦሮሚያ ክልሎች (በነበረው የጸጥታ ችግር ምክንያት) በስተቀር በሁሉም ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች በተለያዩ ዝግጅቶች በዓሉን አክብረዋል፡፡ የተጀመረው የሰላም ፖል በተደረገው የአመራር እና የባለሙያ ክትትል ከዚህ በፊት በነበረዉ የግንባታ አፈፃፀም ችግር ምክንያት ተስተካክሎ ስራው በተሻለ መንገድ ተጠናቋል፡፡

ለሀገራዊ የሰላም ልኬት (peace index) ለማጥናት ከኢንተር ፒስ ድርጅት ጋር በተደረሰው ስምምነት መሰረት በደቡብ፣ በሲዳማ፣ በደቡብ ምዕራብ ክልሎች በተመረጡ ወረዳዎችና ቀበሌዎች ላይ መነሻ እንዲሆን የዳሰሳ ጥናቱ ተደርጎ የመጀመሪያ ደረጃ የጥናት ሪፖርት ተዘጋጅቶ ቀርቧል፡፡ ይህ ናሙና የሰላም ልኬት ጥናት ለተቋሙ ካውንስል አባላት ቀርቦ ግብዓት የተሰጠበት ሲሆን እነዚህ ግብዓችና አስተያየቶች በጥናቱ እንዲካተቱ ተደርጓል፡፡ ቀጣይ አመራሩ በሚሰጠው ውሳኔ መሰረትና ጥናቱን ያጠናው ድርጅትና ለጥናቱ ድጋፍ ያደረገው ኢንተርፒስ በሚያርጉት የጋራ ውሳኔ መሰረት ጥናቱን በይፋ አረጋግጦ (Launching program) የሰላም ሚኒስቴር የበላይ ሃላፊዎችና ሌሎች የመንግሰት ከፍተኛ አካላት በጥቅሉ 98 ተሳታፊዎች በተገኙበት በሸራተን አዲስ በይፋ የተበሰረና የተጠናው ፓይለት ፕሮግራም አገራዊ ይዘት እንዲኖረውና ተጨማሪ 6 ክልሎች ጥናቱ እንዲጀምር ከበቂ መልዕክቶች ጋር ተላልፈዋል፡፡

### 2.2.2. በመንግስት ሰራተኞች ምክክር ያደገ የተቋማትና የሰራተኞች ሰላማዊነት ምጣኔ፤

የመንግስት ሰራተኞች የምክክር መድረክ ለማካሄድ ከፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ጋር በቅንጅት ለመስራት የሚያስችል የመግባቢያ ሰነድ (MoU) እና ዝርዝር የማስተግበሪያ የጋራ ዕቅድ ተዘጋጅቷል፡፡ ሆኖም በተያዘው ዕቅድ መሰረት ስራውን ማስቀጠል ያልተቻለው ከሲ/ሰርቪስ ኮሚሽን ጋር በተደረገው ምክክር ኮሚሽኑ የሲቪል ሰርቪስ ፖሊሲ በማዘጋጀት ላይ በመሆኑ ፖሊሲው እንደተጠናቀቀ ምክክሩ ከፖሊሲው ውይይት ጋር ተቀናጅቶ እንደሚከናወን በመግለጹ እና በዘርፋችን አመራርም በዚሁ አካሄድ ስለታመነበት በቀጣይ በሁለቱ ተቋማት በጋራ ታቅዶ የሚፈጸም ይሆናል፡፡

### 2.2.3. የሰላም አደረጃጀቶች ለአዎንታዊ ሰላም ያበረከቱት አስተዋጽኦና ውጤታማነት፤

ከፌዴራልና ከክልሎች የተወጣጡ 111 የተለያዩ ባለድርሻ አካላት (የሴቶች ተሳትፎም 10%) የተሳተፉበት የኢትዮጵያ የሰላም ምክር ቤት ምስረታ ጉባኤ የተካሄደ ሲሆን በምስረታ ጉባኤው ላይ የሰላም ምክር ቤት ማቋቋሚያ መመሪያ፣ የሠላም ፖሊሲ እና የዘላቂ ሰላም ግንባታ ፕሮግራምና ፕሮጀክት ሰነዶች ቀርበው ውይይት በማድረግ የጋራ ግንዛቤ እንዲያዝ ተደርጓል፡፡ ተሳታፊዎችም በሰላም ግንባታና ብሔራዊ መግባባት ስራዎች ላይ ከምንጊዜውም በተሻለ ሁኔታ የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ለማበርከት ዝግጁነታቸውን ገልጸዋል፡፡

ከትምህርት ሚ/ር ጋር ባደረግነው መግባቢያ ስምምነትና የጋራ መሪ ዕቅድ መሰረት ከ41 ዩኒቨርሲቲዎች ከተወጣጡ የሰላም ፎረም አመራሮች፣ የተማሪ ህብረት አመራሮች እና የዩኒቨርሲቲ ፕሬዝዳንት ጽ/ቤት ኃላፊዎች በተገኙበት የሰላም ፎረሞቹን የ6 ወራት ዕቅድ አፈፃፀም ተገምግሞ ጠንካራና ደካማ አፈፃፀሞች ተለይተው አቅጣጫ ተሰጥቷል፣ በተሻሻለው የሰላም ፎረም መመሪያ ዙሪያም ግብዓት የተሰጠበት ሲሆን መመሪያው በሰላም ሚኒስቴር እና በትምህርት ሚኒስቴር የህግ ባለሙያዎችና በሚመለከታቸው አካላት ዳብሮ የስራ መመሪያ እንደሚሆን መግባባት ላይ ተደርሷል፡ ፡ በመድረኩ ይሳተፋሉ ተብሎ የታቀደው 176 ሲሆኑ የተገኙ 170 ናቸው፡፡ አፈጻጸሙም 90% ሲሆን የሴቶች ተሳትፎም 24% ነው፡፡

በዩኒቨርሲቲ የሰላም ፎረሞች እና በትምህርት ቤቶች የሰላም ክበባት በተደረጉ እንቅስቃሴዎች የታዩ መሻሻሎች

- ✓ በመንግስት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሰላም ፎረሙን በ45 ዩኒቨርስቲዎች ለማጠናከር ታስቦ በ35ት ዩኒቨርስቲዎች ማቋቋም የተቻለ ሲሆን በእነዚህ ዩኒቨርስቲዎችም ወንድ 13,276 ሴት 8,377 ድምር 21,653 የፎረም አባላት ተደራጅተዋል፡፡ ፎረሙን የሚመሩት አስፈፃሚዎችም ወንድ 287 ሴት 115 ድምር 402 ናቸዉ፡፡ 7 ዩንቨርስቲዎች (ደባርቅ፣ ደንቢዶሎ፣ መቀሌ፣ መቅደላ፣ ራያ እና ወልዲያ ዩኒቨርሲቲዎች ፎረሙ ያልተቋቋመባቸው ሲሆኑ ዋናው ምክንያትም በነበረዉ የፀጥታ ችግር ምክንያት ሲሆን 3 ዩኒቨርስቲዎች የሃዋሳ ዩንቨርስቲ፣ የእንጂባራ ዩኒቨርስቲ እና የኮተቤ ሜትሮፓሊቲያን ዩኒቨርሲቲዎች ደግሞ መረጃው በሚገባ ተደራጅቶ አልደረሰም፡፡
- ✓ በተመሳሳይ የሰላም ክበብን ከ5ኛ -12ኛ ክፍል ለማደራጀት በተሰራዉ ጅምር ስራ መሰረት ከደቡብ ህዝቦች፣ ጋምቤላ፣ አፋር እና ከድሬደዋ ክልሎች በስተቀር በሌሎች ክልሎች የሰላም ክበባቱን የማደራጀት ስራዉ ተጀምሯል፡፡ በዚህም ከ5ኛ -8ኛ ክፍል ያሉ ትምህርት ቤቶች ብዛት 20,560 ሲሆኑ ከነዚህ ዉስጥ በ18,201 ት/ቤቶች ክበባት የማደራጀት ስራ ተሰርቷል፡ ፡ በእነዚህ ት/ቤቶች ወንድ 3,993,739 እና ሴት 1,664,987 በድምሩ 5,658,726 ተማሪዎች ያሉ ሲሆን ከነዚህ ዉስጥ ወንድ 333,985 ሴት 767,221 ድምር 1,101,206 ተማሪዎች በሰላም ክበባት ታቅፈዋል፡፡
- ✓ ከ9 -12ኛ ክፍል ያሉ ትምህርት ቤቶች ብዛት 2,645 ሲሆን ከዚህ ዉስጥም 2251 ት/ቤቶች ክበባት የተዋቀሩባቸው ናቸዉ፡፡ በእነዚህ ት/ቤቶች ጠቅላላ ተማሪ ብዛት ወንድ 1,000,597 ሴት 1,942,014 ድምር 2,942,611 ሲሆን ከዚህ ዉስጥ ወንድ 452,486 ሴት 462,659 ድምር 915,145 ተማሪዎች በክበባት ታቅፈዋል፡፡

የዘላቂ ሰላም ግንባታው ሂደቱን ለማሳለጥ ደረጃዉን የጠበቀ የሰላም ግንባታ ማሰልጠኛ ማንዋል <<Peace Building training manual>> እንዲዘጋጅ በተያዘው ዕቅድ መሰረት የማሰልጠኛ ማንዋል ከኢጋድ ጋር በመተባበር በአማካሪዎች ተዘጋጅቶ የቀረበ ሲሆን በረቂቅ ደረጃ የተዘጋጀው ማኑዋል የተቋሙና የክልል አመራሮችና ባለሙያዎች የተሳተፉበት ዎርክሾፕ ተካሄዶበት ግብዓት ማሰባሰብ ተችሏል፡፡ የተዘጋጀው ማንዋሉም ለምሁራን፣ ለባለሙያ እና ለማበረሰቡ በሚመጥን መልኩ የተዘጋጀ ሲሆን ሳይንሳዊ እውቀትን ከባህላዊ እና አገር በቀል እውቀት ጋር በማዋሃድ

ለመጠቀም የሚያስችል ነው፡፡ የሁሉንም ክልሎች ነባራዊ ሁኔታ ያካተተና በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉ መልካም የሰላም ባህሎችንና ልመዶችን ለመጠቀም ታሳቢ በማድረግም ሲዘጋጅ ችሏል፡፡

ከኢትዮጵያ ሙሉ ወንጌል አማኞች ቤተ ክርስቲያን ልማት ኮሚሽን ጋር በመተባበር በሰላም ክበባት አደረጃጃትና አስፈላጊነት፣ ለማህበረሰብ ምክክር ውጤታማት የምንከተላቸው ምክክር ስልቶችስ እንዲሁም የሀይማኖቶች አስተምህሮ ለሰላም ግንባታ ያላቸው ሚና በሚሉ ርዕሶች የአስልጣኞች ስልጠና (TOT) ተካሂዷል፡፡ በስልጠናው ከየክልሉ የተወጣጡ የሰላም ግንባታ ዳይሬክተሮችና ባለሙያዎች፤ የሀይማኖትና እምነት ጉዳዮች ዳይሬክተሮች፤ ከሲቪል ሰርቪስ የተወከሉ አመራሮችና ባለሙያዎች፤ ከትምህርት ሚ/ር እና ከየክልሉ ትምህርት ቢሮዎች አመራሮችና ባለሙያዎች 150 የአስልጣኞች ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ ወንድ 75 ሴት 26 ድምር 101 ተሳትፈዋል፡፡ እንደዚሁም ቀሪው 50 (25 ሴት) ሰልጣኞች TOT ስልጠና ከUN-Women እና ከተቋማችን ሴቶች ስራ አስፈጻሚ የስራ ክፍል ጋር በመቀናጀት የተሰጠ በመሆኑ አጠቃላይ አፈጻጸሙ 100% (ወንድ 149 ሴት 51) ሲሆን የሴቶች ተሳትፎ 25.5% ነው፡፡

የሰላም ግንባታ ስራዎች ያመጡትን ለውጥ ለማወቅ የስተርሊንግ ፋውንዴሽን በሰጠው የፋይናንስ ድጋፍ የዳሰሳ ጥናት ለማድረግ በተያዘው አቅድ መሰረት ጥናቱን የሚያካሂዱ አማካሪዎች ውድድር ተካሄዶ አሸናፊው ድርጅት ስራው ተጀምሯል፡፡

## 3. የሀገር መንግስት ግንባታን ማጎልበት፤

### 3.1. በበጎፈቃደኞች ተሳትፎ የጎለበተ ህብረ-ብሄራዊ አንድነት፤

#### 3.1.1. ከየክልሉ ተመልምለው የበጎ ፈቃደኝነት ስልጠና የወሰዱና ያጠናቀቁ ሰልጣኞች፤

በአስተሳሳብ ለውጥ፣ በተወዳዳሪ ዜጋ እና በሀገር ግንባታ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ እስከ 2015 ዓ.ም የበጀት ዓመቱ በአጠቃላይ በድምሩ 14,774 በጎ ፈቃደኞችን በማሰልጠንና ማሰማራት ተችሏል፡፡

በተመሳሳይ የ5ኛ ዙር ጀምሮ የስልጠና ምልመላና መረጣ ማሻሻያ የተደረገ ሲሆን ዲግሪ የትምህርት ደረጃ ማግኘት የተቸገሩት ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮችን በመለየት ከሌቬል-5 ጀምሮ እንዲመዘገቡ ተደርጓል፡፡ በዚህ መሰረት በ6ኛ ዙር 10,000 በጎ ፈቃደኞችን ለማሰልጠን ታቅዶ 6,714 ማሰልጠን ተችሏል፡፡ አፈጻጸሙም 67.14% ነው፡፡ እንዲሁም በ7ኛ ዙር 2,000 ታቅዶ 1,423 ነው አፈጻጸሙ 71.15 % ሲሆን የሴቶች ተሳትፎ 32% ነው፡፡ በአጠቃላይ እስከ አሁን 42,540 በማሰልጠን ወደ ሁሉም ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ከትውልድ ቦታቸው ውጭ ማሰማራት ተችሏል፡፡

የሰላም ብሄራዊ በጎ ፈቃድ አገልግሎት ሰልጣኞች መተዳደሪያ የስነ-ምግባር ኮድ፣ ደንብ እና ስትራቴጂ በማዘጋጀት ለሚመለከተው አካል መላክ የተቻለ ሲሆን የማሰልጠኛ ማኑዋሎችን ለህትመት ዝግጁ ማድረግ ተችሏል፡፡

የሰላም ብሄራዊ በጎ ፈቃድ ስራን ቀልጣፋና ውጤታማ ለማድረግ በበለጸገው ድህረ-ገጽ አጠቃቀም ላይ ስራውን የሚያስተባብሩ በየደረጃ ላሉ አካላት ስልጠና መስጠት ተችሏል፡፡

የብሄራዊ በጎ ፈቃድ ስራን በዕውቀት ከመምራትና ከማስተባባር አንጻር በመሪ ስራ አስፈጻሚ ስር ላሉት አመራሮችና ባለሙያዎች የብሄራዊ በጎ ፈቃድ ማሰልጠኛ ሠነዶች Soft Skills for Positive Youth Development, Citizen Competency and Nation Building Modules እና የስልጠና

አሰጣጥ ዘዴ ላይ ስልጠና መስጠት ተችሏል። እንዲሁም በሦስት የእርስ በርስ የመማማሪያ ሰነዶች ተዘጋጅተው ለስምንት የቡድን አባላት ስልጠና ተሰጥቷል።

የብሄራዊ በጎ ፈቃድ ማህበረሰብ አገልግሎት ስልጠና ሞጁሎችን ተደራሽነት ከማሳደግ አንጻር የቅድመ ህትመት ስራዎች ማከናወን ተችሏል።

የሰላም ብሄራዊ በጎ ፈቃድ ማህበረሰብ አገልግሎት ስራን በዌብኔር ለማህበረሰቡ ተደራሽ ማድረግ ተችሏል።

### 3.1.2. በተሰጠ ስልጠና የበጎ ፈቃደኞች አገራዊ አመለካከት ለውጥ እድገት፤

በስልጠና ወቅት ሰልጣኞቹ በጎ ፈቃደኝነትን በአመለካከት፣ በሥራ ዕድል ፈጣራ እና በሀገር ግንባታ የተሻለ ግንዛቤ መያዝ ችለዋል። በተጨማሪም የሀገር ፍቅር ስሜት የሚገልጹ እና የባህል ልውውጥ መድረኮችን በማዘጋጀት የሰልጣኞችን ግንዛቤ እንዲያድግ ተደርጓል።

በተሰጡት ስልጠናዎች የበጎ ፈቃደኞች አገራዊ አመለካከት ለውጥ እድገት የቅድመ እና ድህረ-ስልጠና ፈተና በማካሄድ ትንተና የተደረገ ሲሆን የስልጠናዎቹ አማካይ ውጤት (48.2%) ወደ (79.5%) ማሻሻል ተችሏል። የዕድገት መሻሻል 31.3% ነው።

በበጀት ዓመቱ ሶስት ተከታታይ ዙሮች ስልጠና የተሰጠ ሲሆን በስልጠና ላይ እያሉ የማህበረሰብ አገልግሎት መስጠት ተችሏል። ይህም ወደ ገንዘብ ሲቀየር 21,746,960 ብር ይሆናል። ከዚህ ባሻገር በጎነትን በተግባር በማሳየት ለማህራዊ ትስስርና ህብረ-ብሄራዊ አንድነት ትልቅ አስተዋጽኦ አበርክተዋል።

### 3.1.3. ከስልጠና በኋላ ከክልላቸው ውጭ ተሰማርተው አገልግሎት የሰጡ በጎ-ፈቃደኞች፤

በበጀት ዓመቱ ሰልጥኖ በማገልገል ላይ የሚገኙ በጎ ፈቃደኞች ቁጥር 4ኛ ዙር ወንድ 2,843 ሴት 1,337 ድምር 4,180፣ 5ኛ ዙር ወንድ 4,501 ሴት 2,136 ድምር 6,637 ጠቅላላ ድምር ወንድ 7,344 ሴት 3,473 ጠቅላላ ድምር 10,817 ናቸው። እንደዚሁም በ6ኛ ዙር የብሄራዊ በጎ ፈቃድ አገልግሎት 7,130 ወጣቶች ለማሰማራት ታቅዶ ለ6,714 (94.1%) ወጣቶች ስልጠና አጠናቆ ስምርት መስጠት ተችሏል። እንዲሁም 7ኛ ዙር ወንድ 958 ሴት 445 ድምር 1403፣ ባጠቃላይ ወንድ 12874 ሴት 6,060 ድምር 18,934 ሲሆን የሴቶች ተሳትፎ 32% ነው።

በበጀት ዓመቱ የአገልግሎት ጊዜያቸውን አጠናቆ ሽኝት የተደረገላቸው 18,580 በጎ ፈቃደኞች በየደረጃው ሽኝት ማድረግ የተቻለ ሲሆን በጎነት የህይወት ዘመን ተግባራቸው አድርጎ እንዲቀጥሉ መልዕክት ተላልፏል።

የአገልግሎት ጊዜያቸውን ካጠናቀቁ በጎ ፈቃደኞች መካከል በመንግስት ተቋማት፣ መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች እና በግላቸው በጠቅላላው 1,720 የስራ ዕድል ተፈጥሮላቸዋል።

### 3.1.4. በጎ ፈቃደኞች በተሰማሩበት አካባቢ የሰጡት ማህበራዊ አገልግሎቶችና የሰላም ስራዎች፤

በጎ ፈቃደኞቹ በስምሪት ወቅት ለተለያዩ ማህረሰብ ክፍሎች በጎነት፣ አብሮነት፣ ማህበራዊ ትስስር፣ ሠላም ግንባታና ብሄራዊ መግባባት ላይ ግንዛቤ የማስጨበጥ ስራ ተሰርቷል። ይህም 2,000,000 ማህበረሰብ ክፍሎች ግንዛቤ ለማስጨበጥ ታቅዶ ወንድ 2,062,347 ሴት 1,231,920 በድምሩ

3,294,257 **(164.7%)** የማህበረሰብ ክፍሎች እና የተለያዩ ባለድርሻ አካላት ግንዛቤ የመፍጠራ ስራ ተሰርቷል፡፡

ቤተሰብ ከማፍራት አንፃር 10,355 በጎ ፈቃደኞች ቤተሰብ ለማፍራት ታቅዶ **8,371 (ወንድ 5,034 ሴት 3,337)** (80.8%) የብሄራዊ በጎ ፈቃደኛ ወጣቶች በተመደቡበት ቦታ ቤተሰብ እንዲያፈሩ በማድረግ ያፈሩትን ቤተሰብ እና ወላጅ ቤተሰቦቻቸዉን የማገናኘት ስራ ተሰርቷል፡፡ ማህበራዊ ችግሮችን ከመፍታት አንፃር በዓመቱ 890 የአቅመ ደካማ ቤቶች ለመገንባት ታቅዶ በበጀት ዓመቱ 815 (91.5 %) መገንባት መቻሉ (የተጠቃሚ አባዋራ/ እማዋራ ብዛት ወንድ 252 ሴት 357)፣ 678 የአቅመ ደካማ ቤቶች ለማደስ ታቅዶ 637 (94%)ማደስ መቻሉ 1452 (የተጠቃሚ አባዋራ/ እማዋራ ብዛት ወንድ 281 ሴት 453 )፣ **5,000,000** ችግኝ ለመትከል ታቅዶ 3,912,156 (78.2 %) መተከሉ፣ 76,023 ሄ/ር የአቅመ ደካሞች የእርሻ ስራ በማገዝ 152046 (92317 እማዋራ እና 59,729 አባዋራ) ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፤ **5,283.5** የጎዳና ተዳዳሪዎችና አቅመ ደካማዎችን ምሳ ለማብላት ታቅዶ 13,258 (ወንድ 7,186 እና ሴት 6,072) 251% ማብላት ተችሏል፡፡ እንዲሁም 76,023 ሄ/ር የአቅመ ደካሞች የእርሻ ስራ በማገዝ 152,046 (9,2317 እማዋራ እና 59,729 አባዋራ) ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፤ እንዲሁም 7,288 ዩቲለስ ደም መለገስ ተችሏል፡ ፡

በጤና ተቋማት ላይ የተመደቡ በጎፈቃደኞች በጤና፣ በስነተዋልዶ፣ በስነምግብ እና በንጽህና አጠባበቅ ላይ ለ80,080 የህብረተሰብ ክፍል የተለያዩ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ ተሰርቷል፤

በብሄራዊ በጎ ፈቃደኛ ወጣቶች በተለያዩ የጤና ከላዎች፣ ጤና ጣቢያዎችና ሆስፒታሎች ላይ በመገኘት ታማሚዎችን የመጠየቅና ምግብ የማጋራት ስራ ተሰርቷል፤ (ድጋፍ የተደረገላቸዉ ህሙማን 39,276 ናቸው)፡፡

በበጎ ፍቃደኞች በ10 ክልሎችና ሁለት ከተማ አስተዳዳር ዉስጥ በሚገኙ 165 ትምህርት ቤቶች ውስጥ ለ24,242 ወንድና ለ5,896 ሴት በድምሩ 82,738 ተማሪዎች የማጠናከርያ ትምህርት ተሰጥቷል፤

በበጎ ፈቃደኞች በማህበረሰብ አገልግሎት የተከናወኑ ተግባራት ወደ ገንዘብ ሲቀየር በጠቃላይ 564,400,991 ብር ግምት አገልግሎት መስጠት ተችሏል፡፡

በበጀት ዓመቱ የብሄራዊ በጎ ፈቃድ ማህበረሰብ አገልግሎት ከተጀመረ ጊዜ ጀምሮ የላቀ አፈፃፀም ላስመዘገቡ 180 ብሔራዊ በጎ ፈቃደኞች፣ ለ10 ክልሎችና 2 ከተማ አስተዳደሮች እንዲሁም ለ6 ዩኒቨርሲቲዎች የእውቅናና ማበረታቻ ሽልማት በመስጠት የብሔራዊ በጎ ፈቃድ አገልግሎት የህይወት ዘመን ተግበራቸው እንዲያደርጉ ማድረግ ተችሏል፡፡

በብሄራዊ በጎ ፈቃድ ማህበረሰብ አገልግሎት ላይ በተደረገው ድጋፍና ክትትል የበጎ ፈቃደኞቹ የስራ ክህሎት ተሻሽሏል፣ በጎ ፈቃደኞቹ መቻቻልና አብሮነትን በተግባር አሳይተዋል፣ የማህበረሰቡን እሴት፣ ቋንቋ፣ ባህልና ወግ የማወቅ ዕድል አግኝተዋል (አንድ በጎ ፈቃደኛ በደቡብ ክልል የም ልዩ ወረዳ ማህረሰብ አኗኗር ታሪክ መጽሐፍ ጽፎ ማሳተም ችሏል) እንዲሁም በደቡብ ምዕራብ በሸካ ዞን አንድት በጎ ፈቃደኛ የአግልግሎት ጊዘዋን ካጠናቀቀች ቦኋላ ለማህበረሰቡ የግል ትምህርት ቤት

በመክፈት መምህራኖችን በመቅጠር 83 ህፃናት 6 መምራኖችንና ሞግዝቶችን በመቅጠር ማስተማር ችላለች በመሆኑም ለአከባቢው ማህረሰብ የነበራቸው አመለካከት ተቀይሯል፡፡

### 3.1.5. በጎ-ፈቃደኞች በቆይታቸው ወቅት ከተሰማሩበት አካባቢ ያገኙት የህይወት ልምድና ግንዛቤ፤

በበጀት ዓመቱ የበጎ ፈቃደኞች የህይወት ክህሎት፣ ልምድና ግንዛቤን ከ60% ወደ 90% ማሳደግ ታቅዶ 85.6% ማድረስ የተቻለ ሲሆን አፈጻጸሙ 95.1% ነው፡፡ ይህም በጎ ፈቃደኞቹ ለአገረ መንግስት ግንባታ  አስተዋጽኦ ማበርከት መጀመራቸው፤ በጋራ የመኖርና አብሮ የማደግ አስተሳሰብ መጎልበቱ፣ የሚኖሩበትን ማህበረሰብ ወግና ባህል ለምደው በሰላም እየኖሩ መሆኑ፤ ስለ ተመደቡበት ማህበረሰብ የነበራቸው አመለካከት መለወጥ መቻሉ፤ ከማህበረሰቡ ጋር ከፍተኛ ትስስር መፍጠር ችሏል፤ ኢትዮጵያዊ ስሜት እየተፈጠረ መሆኑ (በአካባቢው ያለውን ባህል ማድነቅ፣ ቋንቋውን መልመድ፣ ከወጣቱ ጋር ከፍተኛ ወዳጅነት መፍጠር)፤ ችግሮችን በራሳቸው አቅም ለመፍታት ጥረት እያደረጉ መሆኑ፣ በጋራ የመሥራት፣ እና ልዩነትን በውይይት መፍታት እንደሚቻል ልምድ ማግኘታቸው፣ የሙያና አገልሎት ክህሎትና ማግኘት መቻላቸው፣ ራስን የመምራት ልምድ ማግኘታቸው እና ብዘሃነት ለሀገራዊ የአንድነት መሠረት መሆኑ መረዳት መቻላቸው ወ.ዘ.ተ፡፡

ከUNDP ጋር በመቀናጀት የሁለት ዓመት የብሄራዊ በጎ ፈቃድ ማህበረሰብ አገልግሎት ውጤታማነት የዳሰሳ ጥናት በ8 ክልሎች፣ በ24 ወረዳዎች እንዲሁም ከ32 ማህበረሰብ ናሙና በመውሰድ ጥናት የተደረገ ሲሆን በተካሄደ ጥናት እንዲሁም በሁሉም ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች በተደረገ የድህረ ስምሪት ጥናት መሰረት የሰላም በጎ ፈቃድ ያመጣው ውጤት በዋናነት የህይወት ክህሎት፣ ልምድና ግንዛቤን ከ60% ወደ 90% ለማሳደግ ታቅዶ 85.6 % ማድረስ የተቻለ ሲሆን አፈጻጸሙ 95.1% ነው፡፡ **በዚህም መሰረት ለአብነት የተገኙ ውጤቶች** ፡-

- ✓ ለሌላ አካባቢ ማህረሰብ የነበራቸው አመለካከት መለወጥና ከህብረተሰቡ ጋር ከፍተኛ ትስስር መፍጠር መቻሉ፤ በጋራ የመኖርና አብሮ የማደግ አስተሳሰብ መጎልበቱ፣
- ✓ በበጎ ፈቃደኛ ወጣቶች ዘንድ ከፍተኛ የሆነ ሀገራዊ ስሜት ተፈጥሯል፤የብሄራዊ በጎ ፈቃደኞች በየአከባቢያቸዉ በነበሩበት ወቅት ለሌላው ማህበረሰብ የነበራቸዉ የተሳሳተ ግንዛቤ ተቀርፎ ኢትዮጵያ ዉስጥ በኢትዮጵያ ጠላቶች የሚናፈሰዉ አሉባልታ ወሬ እንደሆነ በሚገባ ተገንዝበዋል፤
- ✓ የማህበረሰቡን እሴት፣ ቋንቋ፣ ባህልና ወግ የማወቅ ዕድል አግኝተዋል (አንድ በጎ ፈቃደኛ በደቡብ ክልል የም ልዩ ወረዳ ማህረሰብ አኗኗር ታሪክ መጽሐፍ ጽፎ ማሳተም ችሏል)
- ✓ የበጎ ፈቃደኞች የስራ ክህሎትና ራስን የመምራት ልምድ መሻሻሉ (በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ መዋዕለ ህጻናት በመክፈት ለህብረተሰቡ አገልግሎት መስጠት መቻሉ) ከአካባቢው ወጣቶች ጋር ከፍተኛ ወዳጅነት በመፍጠርና በጋራ በመሥራት የስራ ባህል እንዲዳብር ማስቻሉ፤
- ✓ በጎ ፈቃደኞቹ ችግሮችን በራሳቸው አቅም ለመፍታት ጥረት እያደረጉ መሆኑ፣ ልዩነትን በውይይት መፍታት እንደሚቻል ልምድ ማግኘታቸው፣ ብሎም ብዘሃነት ለሀገራዊ የአንድነት መሠረት መሆኑ መረዳት መቻላቸው እና ለአገረ መንግስት ግንባታ አስተዋጽኦ ማበርከት መጀመሩ፤

- ✓ በቆይታ ጊዜያቸው የላቀ አፈጻጸም ያስመዘገቡ ቁጥራቸው 180 የሚሆኑ በጎ ፈቃደኞች፣ ለ12ቱ ክልሎች እና 6 ዩኒቨርሲቲዎች የዕውቅናና ማበረታቻ በማድረግ ለክረምት በጎ ፈቃድ ስራ ንቅናቄ ተፈጥሯል፡፡

## 3.2. ለህብረ- ብሔራዊ አንድነትና ብሔራዊ መግባባት እድገት የዋሉ ድልብ ማህበራዊ ሃብቶች፤

### 3.2.1. ከሠላምና ሀገር ግንባታ አንፃር የተለዩ አዎንታዊ እሴቶችና አሉታዊ ልማዶችን መለየት፤

ከሁሉም የሀገራችን አካባቢዎች በጥናት የተለዩ ለሰላም ግንባታና ብሄራዊ መግባባት አስተዋጽኦ ያላቸውን 72 ማህበራዊ ሀብቶች በሚመለከታቸው ባለሙያዎችና ምሁራን በማስተቸትና ተጨማሪ የድርሳናት ማጣቀሻና ግብዓት በማካተት ታትሟል፣ ይህም ማህበረ-ባህላዊ እሴቶቻችንን ከማስተዋወቅ፣ ከመደበኛ የሰላም ግንባታ ስራዎቻችን ጋር አቀናጅቶ ለመጠቀም እና ለትውልድ ለማስተላለፍ ትልቅ ፋይዳ ይኖረዋል፡፡

በማህበረሰባችን ውስጥ የሚተገበሩ አዎንታዊ እሴቶች እና አሉታዊ ልማዶች ተለይተዋል፡፡ የማህበረሰባችንን የዕለት ተዕለት ግንኙነት ያጠናከሩ አብሮነትና ትብብርን ያዳበሩ እንደ ሃይማኖተኛነት፣ ቤተሰባዊነትና የሽምግልና ስርዓት በተጨማሪም ከዚህ ቀደም በማህበረሰባችን ሲወገዙ የነበሩ አሁን ላይ ግን እየተለመዱ የመጡ ግንኙነት እየሸረሸሩና ልማትን እያደናቀፉ ያሉ እንደ ሌብነት፣ ሱሰኝነት፣ ጊዜ አባካኝነት ጨምሮ በጠቅላላው 13 አዎንታዊ እና አሉታዊ ልምዶች ተለይተውና ተተንትነው በብሮሽር መልክ ተዘጋጅተዋል፡፡

### 3.2.2. በተለዩት አዎንታዊ እሴቶችና አሉታዊ ልማዶች ላይ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመወያየት የተፈጠረ የጋራ ግንዛቤ፤

የማህበረ-ባህላዊ ሃብቶች የስልጠና ሰነድ ማዘጋጀት ተችሏል፣ በዚህ መሰረት 145 ከሚሆኑ ከልዩ ልዩ የማህበረሰብ ክፍሎች (ከሀገር ሽማግሌዎች፣ የሃይማኖት አባቶች፣ ሴቶችና ወጣቶች) ጋር ማህበረ ባህላዊ ሀብቶች የሚገኙበትን ወቅታዊ ይዞታ፤ እንዲሁም እነዚህን ሃብቶች ለሰላምና ለእርቅ ስለመጠቀምና ለትውልድ ከማስተላለፍ አንጻር በተከናወኑና መከናወን ስለሚገባቸው ተግባራት ዙሪያ ሰፊ ውይይት ማድረግ ተችሏል፡፡ የማህበረ-ባህላዊ ሃብቶች የስልጠና ሰነድም ተዘጋጅቷል፣

### 3.2.3. የተለዩ አዎንታዊ እሴቶች ስርጸት

የማህበራዊ ሃብቶቻችን መፅሃፍ ለተለያዩ ቤተ-መፅኃፍቶች፣ አንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ት/ት ቤቶች፣ ለክልል ቢሮዎች በጠቅላላው 350 እትሞች ተሰራጭተዋል፡

የተለዩ አዎንታዊ እሴቶች እና አሉታዊ ልማዶች በብሮሽር መልክ ተዘጋጅተዋል፡፡

መስቀል እና የሰማዕታት ቀን በዓላት አስመልክት ያላቸው ማህበራዊ ፋይዳ ላይ ፅሁፎች ተዘጋጅተዋል፡፡ በማህበራዊ ሃብቶቻችን ዙሪያ በምሁራን ዌቢናር ውይይት ተደርጎ እንዲሰራጭ ተደርጓል፡፡

### 3.3. በልሂቃን ተሳትፎ ያደገ ብሔራዊ መግባባት፤

### 3.3.1. የዋና ዋና አገራዊ ጥቅሞችና አገራዊ መገለጫዎችና ህዝባዊ ፖሊሲዎችን በጥናት መለየት

በዋና ዋና ሀገራዊ ጥቅሞች፣ አገራዊ እሴቶችና ሀገራዊ ማንነት ላይ ሰነድ ለማዘጋጀት ታቅዶ በአሁኑ ሰዓት መነሻ ሰነድ የተዘጋጀ ሲሆን የእቅድ አፈፃፀሙ 85 % ነው፡፡ እነዚህንም ሰነዶች ባለሙያዎች እንዲገመግሟቸው በማድረግ በዕሳቤዎቹ፣ በሰነዶቹ ቅርፅ እና በይዘታቸው ላይ ተጨማሪ ምሁራን እና ባለድርሻ አካላት በተገኙበት ግብዓት የማሰባሰብ ስራ በአርባምንጭ ከተማ ለ3 ቀናት ተካሄዷል፡፡ በተጨማሪም በርዕሰ ጉዳዮቹ ላይ በዌቢናር ምሁራን እንዲወያዩበት በማድረግ ማህበረሰቡ ላይ ግንዛቤ የመፍጠር ስራ ተሰርቷል፡፡

### 3.3.2. በሃገራዊ አጀንዳዎች ላይ ሊሂቃንን በማወያየት ያደገ የልሂቃን መግባባት፤

600 ለሚደርሱ የተለያዩ ልሂቃን በመሰረታዊ ሃገራዊ ጉዳዮች ላይ ውይይት ለማካሄድ ታቅዶ

- ✓ ‹‹**በሀገራዊ ምክክሩ የሚዲያ ሚና**›› በሚል ርዕስ 52 (29 ወንድ እና 23 ሴት) የሚዲያ ባለሙያዎች
- ✓ ‹‹**በሀገራዊ ምክክሩ የንግድ ተቋማትና የልማት ድርጅቶች ሚና**›› በሚል ርዕስ 65 (49 ወንድ እና 16 ሴት) የንግድ ተቋማትና የልማት ድርጅቶች ኃላፊዎች
- ✓ ‹‹**የሽግግር ፍትህና ዴሞክራሲ ለተሳካ ሃገራዊ መግባባት**›› በሚል ርዕስ 45 (35 ወንድ እና 10 ሴት) የፖለቲካ ፓርቲ ድርጅት አመራሮች፣
- ✓ ‹‹**በሀገራዊ ምክክሩ የሲቪል ማህበረሰብ ሚና**›› በሚል ርእስ 97 (59 ወንድ እና 38 ሴት) ለሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች አመራርና አባላት፣
- ✓ ‹‹**በሀገራዊ ምክክሩ የምሁራን ሚና**›› በሚል ርዕስ 158 (81 ወንድ እና 77 ሴት) ለምሁራን ጋር ምክክሮችን አካሄደናል፡፡
- ✓ ‹‹**ድህረ-ግጭት የኢኮኖሚ መልሶ ማቋቋም፣ ኢንቨስትመንት መልሶ ግንባታ እና ንግድ ለዘላቂ ሰላም**›› በሚል ኢንተርናሽናል ፕራይቬት ኢንተርፕራይዝስ ሴንተር (CIPE) ከተባለ ተቋም ጋር በጋራ በትግራይ ክልል ከሁሉም ክልሎች የንግድ ቻምበርና ዘርፍ ማህበራት የተውጣጡ 158 (ወንድ 133 እና ሴት 25) ተሳታፊዎች በተገኙበት የውይይት መድረክ ተካሄዷል፣ እንዲሁም በትግራይ፣ አማራ እና አፋር ክልሎች መካከል የንግድ ትስስሩ የሚያንሰራራበትን ሁኔታ ምክክር ተካሄዷል፡፡

በአጠቃላይ 575 (386 ወንድ እና 189 ሴት) ተሳታፊዎች በምክክሩ ተሳትፈዋል፡፡ ይህም አፈፃፀም ታቅዶ ከነበረው 600 አንፃር 95.83% ነው፡፡ በተጨማሪም የፌደራል እና የክልል አስፈፃሚ አካላት **በሃገራዊ ምክክሩ፣ በብሄራዊ መግባባት እና ማህበረ-ባህላዊ ሃብቶቻችንን ከማስፋፋት** አንፃር በሚኖራቸው ሚና እና የጋራ ስራችን ላይ ውይይት ተካሂዷል፡፡ በዚህም መድረክ 180 ተሳታፊዎች ለማሳተፍ ታቅዶ 145 (ወንድ 98 እና ሴት 57) ተሳታፊዎች በማሳተፍ የእቅዱን 80% ለማሳካት ተችሏል፡፡

‹‹**የአገር ግንባታና የምሁራን ሚና**›› በሚል ርዕስ መንግስት በአገር አቀፍ ደረጃ በሁሉም የመንግስትና የግል የትምህር ተቋማት (የዩኒቨርሲቲዎችና የመደበኛ ትምህር ቤቶች) 26,356 ምሁራኖችን በውይይቱ ማሳተፍ ተችሏል፡፡

**በወሳኝ ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ፡-**

- ✓ ሲዳማ ክልል 75,327 የመንግስት መዋቅር፣ ምሁራን፣ ልሂቃን፣ ሴቶች፣ ወጣቶች፣ አካል ጉዳተኞች፣ የስፖርት ማህበረሰብ እና ማህበረሰብ አንቂዎች አወያይተዋል፡፡
- ✓ በኦሮሚያ ክልል 3,732,787 የመንግስት መዋቅር፣ ምሁራን፣ ልሂቃን፣ አባገዳዎች እና የሃይማኖት አባቶች፣ ሴቶች፣ ወጣቶች እና አካል ጉዳተኞች አካል ጉዳተኞች አወያይተዋል፡፡
- ✓ አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር 1,216 የመንግስት መዋቅር፣ ልሂቃን፣ ሴቶች፣ ወጣቶች እና የስፖርት ማህበረሰብ አወያይተዋል፡፡
- ✓ አማራ ክልል ደሴ ከተማ፣ 1,484 (ወንድ 982 እና ሴት 502) አወያይተዋል፡፡
- ✓ ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ 88,153 የመንግስት መዋቅር፣ ምሁራን፣ ልሂቃን፣ ሴቶች እና ወጣቶች አወያይተዋል፡፡
- ✓ እነዚህም ምክክሮች በወሳኝ ሃገራዊ ጉዳይ ላይ በልሂቃን እና በማህበረሰብ ተወካዮች ላይ የተቀራረበ አመለካከት ከመፍጠር እና የጋራ መግባባት ከመፍጠር አንፃር ትልቅ ፋይዳ አላቸው፡፡ ይህም በተለያዩ ማህበረሰብ ተወካዮች ጋር ምክክር ለማስፋፋት ያቀድነውን እቅድ ከ100% በላይ እንድናሳካ አስችሎናል፡፡

ከሁሉም ክልል የተወጣጡ 139 (ወንድ 118 እና ሴት 21) የመንግስት መዋቅር ተሳታፊዎች ‹‹በሀገራዊ ምክክሩ የመንግስት መዋቅር ሚና›› በሚል ስልጠና የተሰጠ ሲሆን ይህ ስልጠና ወደ ታች ወርዶ ማለትም በኦሮሚያ ክልል፣ በሲዳማና በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ለ612,848 (ወንድ 321,567 እና ሴት 291,281) የመንግስት መዋቅር ባለሙያዎች ስልጠናውን የማውረድ ስራ ተከናውኗል፡፡ ይህም በብሔራዊ መግባባት ዙሪያ የሰላምና ፀጥታ መዋቅሩ አቅም ከፍ ለማድረግ ጠቅሚል፡፡

‹‹**የአድዋ ድል በዓል ለአገራዊ አንድነትና ጀግንነት**›› በሚል ርዕስ 1,500 (775 ወንድ እና 725 ሴት) የሰላም ሚ/ር፣ ብሔራዊ ደህንነት፣ አርቴፍሻል ኢንተለጀንስና ፋይናንስ ደህንነት አመራሮችና ሰራተኞች ጋር ምክክር ተካሂዷል፡፡

‹‹**ማህበረ-ባህላዊ እሴቶቻችን ለተሳካ ሃገራዊ ምክክር**›› በሚል ርዕስ 135 (125 ወንድ እና 10 ሴት) የሃይማኖት አባቶች፣ የሃገር ሽማግሌዎች እና የሴትና የወጣት ተወካዮች ጋር ምክክር የተካሄደ ሲሆን ከተያዘውም 250 እቅድ አንፃር 54% ነው፡፡

በምክክር መድረኩ ከተሰበሰበው የእርካታ ሰርቬይ መጠይቅ መረዳት የሚቻለው የምክክር መድረኩ ለተሳታፊዎች ከፍተኛ ግንዛቤና መግባባት የፈጠረ መሆኑ፣ በቀጣይ የሚካሄደው ሀገራዊ ምክክር መድረክ የሀገሪቱን መሰረታዊ ችግሮች እንደሚፈታና እንደ ሀገር ያለው አስተዋጽኦ ከፍተኛ በመሆኑ ምክክሩ ችግር ይፈታል በሚል ተስፋ የጫረና፤ የምክክር ሂደቱ ይሳካ ዘንድ ለመደገፍ ተነሳሽነት እንደፈጠረ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

ቅን ልቦች ከተባለ የበጎ ስራ ድርጅት ጋር በመተባበር ለአርቲስቶችና ለአክቲቪስቶች **"ማህበራዊ ሚዲያው ለሰላም ግንባታ"** በሚል መሪ ቃል በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ አማካኝነት ስልጠና መስጠት ተችሏል፡፡ የተቋሙን አርማ (እርግብ እና ሰላማችን እጃችን ነው የሚል መሪ ቃል ያለበት **የሰላም መንደር በዚህ ፔጅ የሀገራችንን ሰላም ለማረጋገጥ ከዘር እና ከሃይማኖት ከፍ ብለን አንድነታችንን የምናስከብርበት ነው!!** በሚል የቴሌግራም ቻናል ተከፍቶ 1730 ተጠቃሚዎች (ተከታዮች) ሚዛናዊና ገንቢ አስተያየት በመስጠት የተቋሙን ዓላማ ለህብረተሰቡ በማዳረስ ስራዎችን እየሰሩ ነው፡፡ ይሄንን ቻናል ሁሉም የተቋሙ አመራርና ሰራኞች መጠቀም እንዲችሉ ከኮሚኒሽኑ ጋር መግባባት ተደርሷል፡፡

### 3.3.3. የዋና ዋና አገራዊ ጥቅሞችና አገራዊ መገለጫዎች ስርጸት

ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ በዌቢናርና በውስን ቡድን ውይይት እንዲካሄድ፣ እንዲቀረፅና ለማህበረሰብ እንዲዳረስ ማድረግ ስራ 6 ጊዜ ለማካሄድ የታቀደ ሲሆን 4 ጊዜ የዌቢናር እና የሚዲያ ማብራሪያዎች በተጨማሪም ከኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት (ኢዜአ) ጋር በመተባበር የፌደራል ተቋማት ተወካዮች፣ ምሁራን፣ ተፅዕኖ ፈጣሪ ግለሰቦች፣ ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች እና ሌሎች በተገኙበት በሃገራዊ ማንነት፣ ጥቅም እና እሴቶች ላይ ፅሁፎች ቀርበው ጥልቅ ውይይት ተካሄዷል፡ ፡ ውይይቱም በተለያዩ መደበኛ እና ማህበራዊ ሚዲያዎች እንዲተላለፍ በማድረግ ማህበረሰባችን ላይ ግንዛቤ ማስፋት ተችሏል፡፡ ይህም እቅድ አፈፃፀሙን 83.3 % ያደርሰዋል፡፡

## 4. የግጭት ተጋላጭነትን መቀነስና ግጭት የማስተዳደር አቅምን ማሳደግ፤

### 4.1. በማዕከል፣ በክልሎችና በከተማ እስተዳዳሮች የተናበበ የቅድመ ግጭት ሁኔታ መከታተያ ክፍል በማደራጀት ግጭቶችን አስቀድሞ መከላከል፤

### 4.1.1. በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈ የግጭት ቅድመ ማስጠንቀቂያ ፈጣን ምላሽ ሥርዓት፣

በማዕከል፣ በክልሎች እና በከተማ አስተዳደሮች የግጭት ቅድመ ማስጠንቀቂያና ፈጣን ምላሽ የሁኔታ መከታተያ ክፍል በቴክኖሎጂ ተሚልተው እንዲደራጁ ለማድረግ በታቀደው መሰረት ከኢትዮ-ቴሉኮም ነፃ የጥሪና የአጭር ፅሁፍ አገልግሎት መስጫ ማዕከል በIVR ሲስተም የAvaya ሶፍትዌር ግዥ በመፈጸም፣ በመዘርጋትና በቴክኖሎጂ በማስተሳሰር ዜጎች የግጭት ሁኔታ መረጃ የሚሰጡበት የመረጃ ልውውጥ ስርዓቱን ማዘመን ተችሏል፡፡

የቴሌግራምና ዋትስአፕ ፕላት ፎርሞችን በመጠቀም እና የመረጃ ልውውጡን ለመደገፍ 1349 ታብሌቶችን ድጋፍ (ለአፋር፣ አማራ፣ ኦሮሚያ፣ ቢኒሻንጉል ጉሙዝ፣ ጋምቤላ፣ ሶማሌ፣ ሐረሪ፣ ድሬዳዋ፣ አዲስ አበባ፣ ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ እና ሲዳማ ክልሎች) ተሰራጭቷል፡፡ እንዲሁም ከጉምሩክ ኮሚሽን በተገኘ ድጋፍ 25 ላፕቶፕ፣ 5 ቴሌቪዥን፣ 10 ዋይፋይ ዲቪይስ አንድ ስዊች ለ5 ክልሎች (ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ፣ ቤንሻንጉል ጉምዝ፣ አፋር፣ ኦሮሚያና አማራ) የሁኔታ መከታተያ ክፍሎችን ለማቋቋም ድጋፍ ተደርጓል፡፡ እንዲሁም በኮሪያ መንግስት በተደረገ ድጋፍ ለ10 ወረዳዎች የሁኔታ መቀበያ ክፍሎችን በማቋቋም በቁሳቁስና በቴክኖሎጂ ድጋፍ ለማድረግ የዴስክቶፕ፣ ኮምፒውተር፣ የጠረጴዛና የወንበር ግዥ እቅድ ተዘጋጅቶ የግዥ ስራው በሂደት ላይ ይገኛል፡፡

በግጭት ቅድመ ማስጠንቀቂያና ፈጣን ምላሽ፣ በግጭት አስተዳደርና አፈታት፣ በጥላቻ ንግግር አዋጅ፣ የሌሎች አገራት ተሞክሮ እንዲሁም የመገናኛ ብዙሀን የግጭት ሙያዊ አዘጋገብ መርሆዎች ጽንሰ ሀሳብና አሰራር ላይ ለ1119 አመራሮች፣ ባለሙያዎች፣ የዩኒቨርሲቲ መምህራን፣ የጄስቲስ ፎር ኦል ባለሙያዎች፣ ከዲስቲኒ ኢትዮጵያ፣ ከሁሉም ክልል ለተውጣጡ የመገናኛ ብዙኃን ሀላፊዎች፣ የሙያ ማህበራት፣ ጋዜጠኞች፣ ቡሎጎሮች፣ የሲቪክ ማህበራት ተወካዩች፣ የኃይማኖት ተቋማት ጋዜጠኞች እና የስካውት ወጣት አመራሮች የአሰልጣኞች ሥልጠና መስጠት ተችሏል፡፡ ስልጠናውን የወሰዱ አካላትም በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ፣ በጋምቤላ፣ በደቡብ፣ በኦሮሚያ እንዲሁም በሲዳማ ክልል ወረዳ ላሉ አመራሮችና ባለሙያዎች ስልጠና በመስጠት በግጭት ቅድመ ማስጠንቀቂያና ምላሽ እንዲሁም በግጭት አስተዳደር ጽንሰ ሀሳብና አሰራር ዙሪያ በቂ ግንዛቤ፣ እውቀትና ክህሎት ተፈጥሯል፡፡

በተጨማሪ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ለ200 የሰላም ሰራዊት አባላቶች እንዲሁም 35 ከክልል እና ከተማ አስተዳደር ለመጡ የግጭት ቅድመ-ማስጠንቀቂያ አመራሮችና ባለሙያዎች የግጭት መረጃ አሰባበሰብ ላይ፤ በቅድመ-ማስጠንቀቂያ የግንዛቤ ማስጨበጫ እና የነፃ ጥሪ ማዕከልን 962 ቁጥርን የማስተዋወቅ ስራ ተከናውኗል፡፡ በዚህም የተገኘ ውጤት፡

- ✓ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዘ የመረጃ ልውውጥና አያያዝ ስርዓት አድጓል፣
- ✓ በተደረገው የቴክኖሎጂ ድጋፍ እና በተዘረጋው የአሰራር ስርአት የግጭት መረጃዎች እንዲቀላጠፉ በማገዙ ወቅታዊ መረጃዎች ለማዕከል የሁኔታ መከታተያ ክፍል እንዲደርሱ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክቷል፡፡ በመሆኑም የግጭት ቅድመ ማስጠንቀቂያና ፈጣን ምላሽ ትንተና ሪፖርት ለሚመለከተው ምላሽ ሰጪ አካል ማቅረብ አስችሏል፡፡

### 4.1.2. ፈጣን ምላሽ ያገኙ የቅድመ ማስጠንቀቂያ መረጃዎች ምጣኔ በተመለከተ፡-

በማዕከልና በክልሎች የግጭት ቅድመ ማስጠንቀቂያና ፈጣን ምላሽ የሁኔታ መከታተያ ክፍል የተሰበሰበና የተተነተነ መረጃን በተመለከተ፡-

| ውጤት | | መለኪያ | |
|---|---|---|---|
| ከክልሎች እና ከሌሎች የመረጃ ምንጮች የተላለፈ የግጭት ቅድመ ማስጠንቀቂያ መረጃዎች | የግጭት አመላካች | በቁጥር | 186 |
| | የግጭት ክስተት | በቁጥር | 205 |
| | የግጭት ሁኔታ | በቁጥር | 72 |
| | የጠቅላላ መረጃ ብዛት | በቁጥር | 463 |
| ፈጣን ምላሽ ያገኘ መረጃ | | በመቶኛ | 70.2 |
| በተሰጠ ፈጣን ምላሽ ቀድሞ መከላከል የተቻለ ግጭት | | በቁጥር | 325 |

ከግጭት ሁኔታ መከታተያ ክፍል በሚገኘው ጥሬ መረጃ መሰረት 48 ሳምንታዊ፣ 12 ወርሃዊ፣ 4 የሩብ ዓመት፣ እና 1 አመታዊ የግጭት ሁኔታ ትንተና ተሰርቶ በየደረጃው ላሉ ምላሽ ሰጪ አካል እንዲደርስ ተደርጓል፡፡

በአገር አቀፍ ደረጃ የግጭት ተጋላጭ እና አዋሳኝ አካባቢዎችን የሚያሳይ የትንተና ሰነድ ለማዘጋጀት በታቀደው መሰረት (150 ወረዳዎች እና በከተማ አካባቢ የሚገኙ ዘጠኝ የኢንቨስትመንት

ቦታዎችን) ከክልሎች ጋር በመሆን መለየት ተችሏል፡፡ በቀጣይ ቀሪ ወራት በትኩረት ወደ ሰላማዊ ቀጠና ለማሸጋገር የሚሰራባቸው 50 ቅድሚያ የሚሰጣቸው የግጭት ተጋላጭ ወረዳዎች ተለይተው እቅድ ወጥቶላቸው ወደ ስራ ተገብቷል፡፡

ከ2010-2014 ዓ.ም በኢትዮጵያ የግጭት ሁኔታ እና አዝማሚያ ጥልቅ ጥናት ለማካሄድ በታቀደው መሰረት ጥልቅ ጥናቱን የሚያከናውኑ አካላት ተለይተው የቅድመ ዝግጅት ስራዎችን በማጠናቀቅ ወደስራ እንዲገቡ ተደርጓል፡፡ በዚህ መሰረት አገራዊ የግጭት አካባቢዎችን የመለየት ስራ፣ መሰረታዊ ችግሮችና ዋና ዋና ተዋናዮችን ያካተተት የመጀመሪያ ረቂቅ ሰነድ ተጠናቋል፡፡ በሰነዱ ላይ የሰላም ሚ/ር የማኔጅመንት ካውንስል አባላት፣ የሁሉም ክልል የሰላምና ፀጥታ ቢሮ ከፍተኛ ባለሙያዎች፣ ከአዲስ አበባ የኒቨርስቲ ሰላምና ጸጥታና ከፌዴራሊዝም ት/ት ክፍል፣ ከኢትዮጵያ ሰላም ተቋም እንዲሁም Life and Peace Institution (LPI) ተጋባዥ እንግዶች በተገኙበት የጥናት ሰነዱ ቀርቦ ሰፊ ውይይት የተደረገበት ሲሆን የተሰጡ ግብዓቶች እና ሌሎች ተጨማሪ ስራዎች ተካተው የጥናት ሰነዱ ሙሉ በሙሉ ተጠናቋል፡፡ በቀጣይ የበጀት ዓመት የጥናቱን የመፍትሄ ሀሳቦች መሰረት በማድረግ የእቅድ አካል ተደርጎ ወደ ትግበራ ይገባል፡፡

አገር አቀፍ የግጭት ቅድመ ማስጠንቀቂያ እና ምላሽ አስተባባሪ ግብረ ኃይል ማቋቋሚያ ረቂቅ ደንብ በማዘጋጀት ሰነዱን ለማዳበር የሚያስችሉ ግብዓት መስጠት ለሚችሉ አካላት በመላክ ግብዓት የማሰባሰብ ተግባር እየተከናወነ ሲሆን ሂደቱ ሲጠናቀቅም ለሚመለከታቸው አካላት ለውይይት የሚቀርብ ይሆናል፡፡

ቅድመ ማስጠንቀቂያና ፈጣን ምላሽ የአሰራር መመሪያ አዘጋጅቶ ወደ ሥራ ለማስገባት በታቀደው መሰረት ሰነዱ ተዘጋጅቶ እና በባለሙያዎች እንዲሁም በካውንስል አባላት ዳብሯል፡፡ በቀጣይ ከክልሎች ጋርም የጋራ ውይይት በማካሄድ እና የሚሰጡ ግብዓቶችን በማካተት ተግባራዊ የሚደረግ ይሆናል፡፡

የግጭት አመላካች መረጃ መሰረት በማድረግ ወቅታዊ የቅድመ ግጭት አመላካች አንድ የምክረ ሃሳብ ሰነድ ለማዘጋጀት በታቀደው መሰረት የምክረ ሀሳብ ሰነዱ ተዘጋጅቶ ለሚመለከታቸው የክልል አካላት በማድረስ ለተነሱ ቅሬታዎች እና አቤቱታዎች ምላሽ እንዲሰጣቸው የማስተባበር ስራ እየተሰራ ይገኛል፡፡ በተደረገ የመረጃ አሰባሰብና ትንተና የተገኘ ውጤት፡-

- ✓ የግጭት የሁኔታ ትንተና መረጃዎችን በማደራጀትና በመተንተን ለሚመለከታቸው ውሳኔ ሰጪ አካላት በማድረስና በማስተባበር መፍትሄ እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡
- ✓ አገራዊ የግጭት ጥልቅ ጥናት በማካሄድ አገራዊ የግጭት አካባቢዎችን የመለየት፣ መሰረታዊ ችግሮች፣ ዋና ዋና ተዋናዮችንና ኩነቶችን ያካተተት ሰነድ ተዘጋጅቷል፡፡

### 4.1.3. በተሰጠ ፈጣን ምላሽ የተደረሰ መግባባትና ማስቀረት የተቻለ ግጭት፤

የፌዴራል፣ የክልል እንዲሁም እስከ ወረዳ ድረስ የሚመለከታቸው አመራር አካላትንና ተቋማትን በማስተባበር ለተለዩ መረጃዎች ምላሽ ለመስጠት ሰፊ ስራ ተሰርቷል፡፡ ምላሽና መፍትሄ ያገኙ የአመላካች፣ የክስተትና የሁኔታ የግጭት ዓይነቶች በዋናነት ከዝርፊያ፣ ከስርቆት፣ ከሌብነት፣ ከግድያ፣ ከተፈናቃይ እርዳታ በወቅቱ ከማድረስ ጋር የተያዙ ናቸው፡፡

ምላሽ ያገኙ ነገር ግን በቂ መፍትሄ ያላገኙ ደግሞ የተወሰኑ በታጠቁ ኃይሎች የታገዙ ጥቃቶች (ሸኔ) ግጭቶች፣ ከመዋቅር ጋር የተያያዙ ቅሬታዎች፣ የማንነት፣ የድንበርና ከአስተዳደራዊ ወሰኖች ጋር የተያያዙ ናቸው፡፡ እነኚህ ጉዳዮች ጊዜ የሚፈልጉ፣ በተለያዩ አካላት ዘላቂ ምላሽና መፍትሄ የሚሰጥባቸው (በተለይም በፌደሬሽን ም/ቤት) ናቸው፡፡ ይሁንና ግጭቶቹ እንዳይባባሱና ወደ ሁከትና ብጥብጥ እንዳያመሩ ማድረግ ተችሏል፡፡ የወሰንና የማንነት ጉዳዮችም በፌደሬሽን ም/ቤት የሚፈቱበትን ሁኔታ በቅርብ ጊዜ የጋራ መድረክ ተዘጋጅቶ የሚፈጸም ይሆናል፡፡ በዚህም የተገኘ ውጤት፡-

- ✓ ከክልል እስከ ወረዳ የሚመለከታቸው ተቋማትና አመራሮች በቅንጅት ለመስራት እና ለሚከሰቱ ችግሮችም የጋራ መፍትሄና ምላሽ የመስጠት እንዲሁም የተከሰቱ ግጭቶችን የማስተዳደርና የመፍታት አቅም አድጓል፡፡
- ✓ የከፋ ጉዳት ሊያደርሱ የነበሩ ግጭቶች ቀድሞ መከላከል ተችሏል፣

## 4.2. ወደ ዘላቂ ሰላምና ልማት የተሸጋገሩ የግጭት ቀጠናዎች፤

### 4.2.1. በግጭት ምክንያት የሚከሰቱ ሰብዓዊ ቀውስና የንብረት ውድመት መረጃ ማሰባሰብና ማተንተን፡፡

በግጭት ምክንያት የሚከሰቱ ሰብዓዊ ቀውስና የንብረት ውድመት መረጃ ለማሰባሰብና ለመተንተን በታቅደው መሰረት አንድ ሰነድ ተዘጋጅቷል፡፡ በመሆኑም በሀገራችን በተከሰቱ ግጭቶች በርካታ ወገኖች ከቤት ንብረታቸው ተፈናቅለው በጊዜያዊ መጠለያ ጣቢያ የሚገኙ ሲሆን በአሁኑ ሰዓት ከክልሎች በተሰበሰበው መረጃ በኦሮሚያ፤ በቤንሻንጉል፣ በአማራ፣ በደቡብ፣ በሱማሌ፣ በአፋር፣ ሀረሪ፣ ደቡብ ምዕራብ ክልሎች በድምሩ 1,980,430 (ወ 818,162፤ ሴ 536,418) የህብረተሰብ አካላት ከቤት ንብረተቻው ተፈናቅለው ለችግር ተጋልጠዋል፡፡ በሌላ በኩል ከአፋር፣ ከኦሮሚያ፣ ቤንሻንጉል ክልሎች ወደ ቀያቸው የተመለሱት ወገኖች በድምሩ 1,119,184 ናቸው፡፡ ይህ መረጃ የትግራይ ክልል ተፈናቃዮችን አያካትትም፡፡

### 4.2.2. በተሰበሰበ መረጃና በተደረገ ትንተና መሰረት ዜጎች ድጋፍ እንዲያገኙ የተደረገ ድጋፍ፤

በአገር አቀፍ ደረጃ ተፈናቃዮችን መልሶ ለማቋቋም በሚኒስትሪያል ደረጃ ታክስ ፎርስ የተቋቋመ ሲሆን ታክስ ፎርሱን የመምራት ኃላፊነት ለተቋማችን ተሰጥቷል፡፡ በዚህ መሰረት በቅድሚያ የአገር ውስጥ መፈናቀልን ለመከላከል እና ጥበቃ፣ ድጋፍና ዘላቂ መፍትሄ ለማፈላለግ የሚያስችል ረቂቅ አዋጁ ተዘጋጅቶ ሁሉም ክልሎችና ባለድርሻ አካላት የተሳተፉበት የውውይትና የግብዓት ማሰባሰቢያ መድረኮች ተዘጋጅተው የተሰጡ ግብዓቶችና አስተያየቶች በማካተት የማጠናቀቅ ስራ ተሰርቷል፡፡ በቀጣይ በጀት ዓመት ከፍትህ ሚኒስቴርና ከሚመለከታቸው ተቋማትና አካላት ጋር በመሆን በማጸደቅ ወደ ትግበራ የሚገባ ይሆናል፡፡

በተሰበሰበው የተፈናቃዮች መረጃ መሰረት የሰብዓዊ ድጋፍ አሰጣጥ ሁኔታን የመከታተል ስራ የተሰራ ሲሆን በዚህ መሰረት በሚመለከታቸው አካላት ድጋፎች እየተደረጉ መሆኑ ታይቷል፡፡ ይሁንና የሚሰጠው ድጋፍ በተፈለገው መጠንና ጊዜ ከማድረስ አኳያ ክፍተቶች መኖራቸው፣ በተለይም የእናቶችና ህጻናት አልሚ ምግብም እጥረት መኖሩ እንዲሁም አንዳንድ አካባቢዎች ላይ እርዳታ የተቋረጡባቸው እንዳሉ ተስተውሏል፡፡ በመሆኑም ለብሄራዊ አደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን ያለውን ክፍተት በአካል እና በሪፖርት በማሳወቅ የማስተባበርና የመከታተል ስራዎች

በመስራት ያሉት ችግሮች እየተቀረፉ እንዲሄዱና ትኩረት እንዲሰጣቸው ተደርጓል፡፡ በዚህም የተገኘ ውጤት፡-

- ✓ የሀገር ውስጥ መፈናቀልና ዘላቂ መፍትሄ በሚመለከት ያለውን የህግ እና የአሰራር ክፍተት ለመቅረፍ የሚያስችል ረቂቅ አዋጅ ማዘጋጀት ተችሏል፣
- ✓ ተፋናቃዮች በወቅቱ ድጋፍ እንዲያገኙ በማድረግ ለተጨማሪ ቀውስ እንዳይጋለጡ ተደርጓል፡፡

### 4.2.3. ለተፈናቀሉ እና ጉዳት ለደረሰባቸው የስነ ልቦናና ማህበራዊ ድጋፍ ስልጠና እና ወደ ሰላማዊ ኑሮ የተሸጋገሩ ዜጎች፤

የስነ ልቦና እና የዓዕምሮ ጉዳት ለደረሰባቸው ለ1506 ተፈናቃይ ወገኖች በቤንሻንጉል ጉምዝ፣ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ እና ከአማራ ክልል በጊዚያዊ መጠለያ ተጠልለው ለሚገኙ ተፈናቃዮች የስነ ልቦና፣ ማህበራዊ ድጋፍ እንዲሁም ከዓዕምሮ ጉዳት ለማገገም የሚያስችል ስልጠና ከተፈናቃዩች መካከል የማህበረሰብ ደጋፊዎች በዘርፉ ሰፊና የካበተ ልምድ ባላቸው አማካሪዎች ስልጠና መስጠት ተችሏል፡፡ በተሰጠው ስልጠና ከደረሰባቸው የስና ልቦናና የዓዕምሮ ጉዳት እንዲያገግሙ ከፍተኛ እገዛ ያደረገላቸው ሲሆን ተፈናቅለው ከተጠለሉበት ማህበረሰብ ጋር በሰላም ለመኖር እንደሚረዳቸው በሰጡት አስተያየት ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

እንዲሁም ትጥቅ አንስተው ቤኒሻንጉል ጉምዝ ክልል ውስጥ ይንቀሳቀሱ የነበሩና ትጥቅ ፈትተው በሰላማዊ መንገድ ኑሯቸውን ለመምራት እጃቸውን ለሰጡ 270 የቤህነን አባላት እና በመልካም አስተዳደር እጦት መንግስትን አኩርፈው በደቡብ ኢትዮጵያ ህዝቦች ክልል ይንቀሳቀሱ የነበሩ እና በሰላማዊ መንገድ ኑሯቸውን ለመምራት እጅ የሰጡ 100 ወጣቶች ልምድ ባላቸው አማካሪዎች/አሰልጣኞ/ ስስልጠና እንዲሰጥ በማድረግ ዜጎችን የማረጋጋት ስራ ተሰርቷል፡፡ በተጨማሪም ተፈናቃይ ባለባቸው አካባቢዎች ላሉ 45 የሰላምና ፀጥታ አመራርና ባለሙያዎች በግጭት አስተዳደርና አፈታት ዙሪያ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

አፋር ክልል በሚገኙ ተፈናቃይ ተመላሾች ላይ የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት በሚደረግላቸው ሰብአዊና ቁሳዊ ድጋፍ እንዲሁም የሰላምና ፀጥታ አጠባበቅ ዙሪያ ጥናት አካሂዶ ያገኛቸውን መልካም የሆኑ ስራዎችና ጉድለቶች በማጠናቀር ያዘጋጀውን 12 ገጽ ሪፖርት ለመንግሥት ከማቅረቡ በፊት ከተቋማችን እና ከአደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽን የተወጣጣ አንድ ቡድን ወደ ቦታዎቹ እንዲሰማራ ተደርጎ የክልሉን ባለድርሻ አካላት፣ በክልሉ የሚንቀሳቀሱ አጋር ድርጅቶች እና የተፈናቃይ ተወካዮች ጋር በተደረገ ውይይት የተሰጠ መረጃና በአካል በመገኘት በተደረገ ምልከታ በሰብአዊና ቁሳዊ ድጋፎች እንዲሁም የፀጥታ አጠባበቅ መሻሻሎች የተገኙ ግኝቶችን የያዘ ሪፖርት ተዘጋጅቶ ቀርቧል፡፡ በዚህም የተገኘ ውጤት፡-

- ✓ በግጭት ምክንት ጉዳት የደረሰባቸው ተፈናቃዩች ከስና ልቦናና ዓዕምሮ ጉዳት አገግመው ከተጠለሉበት ማህበረሰብ ጋር በሰላም መኖር ጀምረዋል፡፡
- ✓ አደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽን በማስተባበር ለተፈናቃዮች ሰብኣዊና ቁሳዊ ድጋፍ በወቅቱ እንዲደርሳቸው ተደርጓል፡፡

- ✓ በተሰጠ ስልጠና በጸጥታ አካላት እና በተፈናቃዮች መካከል ጤናማ ግንኙነት እና የትብብር መንፈስ መዳበሩ፤

### 4.2.4. ወደ አንጻራዊ ሰላማዊነት የተሸጋገሩ የግጭት ቀጠናዎች፤

ከግጭት ቀጠናነት ወደ ሰላማዊነት የተሸጋገሩ አካባቢዎች በተመለከተ በሁሉም ክልሎች በባለሙያዎች በተደረገ የመስክ የዳሰሳ ጥናት ከግጭት ወደ ሰላማዊነት የተሸጋገሩ አካባቢዎችን የመለየት ስራ ተሰርቷል። በዚህ መሰረት፡-

ከቤንሻንጉል ጉምዝ ክልል መተከል ዞን 7 ወረዳዎችና ከአማራ ክልል ከአዊ ዞን 5 ወረዳዎች መካካል የነበረው ግጭት በእርቅ በመፈታቱ ከግጭት ቀጠና ወደ አንጻራዊ ሰላማዊ ቀጠና የተሸጋገሩ ሲሆን የአሶሳ ዞን በድበር አካባቢ ይቀሳቀስ የነበረው የቤነን ታጣቂ በተደረገለት የሰላም ጥሪ መሰረት ከፌደራል እና የክልሉ መንግስት ጋር ባደረገው የሰላም ስምምነት 500 የታጠቁ የቤነን አባላት እና አመራሮች እስከነ ትጥቃቸው እጃቸው ለመንግስት ሰጥተዋል። በዚህም በዞኑ የሚገኙ ሶስት የስጋት ቀጠናዎች (መንጌ፣ ሸርቆሌ እና ኩሙርክ) ወረዳዎች ወደ ሰላማዊ ቀጠናነት ተሸጋግረዋል ።

ከኦሮሚያ ባሌ ዞን እና ከሱማሌ ክልል ሊበን ዞን የሁለቱ ጉራዳማይሌ ወረዳዎች ተከስቶ ነበራው ግጭት በእርቀ ሰላም በመፈታቱ አካባቢው ወደ ሰላም ቀጠናነት ተሸጋግሯል።

ኦሮሚያ እና ሱማሌ ክልሎች በተመረጡ 2 ወረዳዎች (ኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ሀረርጌ ዞን ጉርሱም ወረዳ እና ሱማሌ ክልል ሲቲ ዞን ሽንሌ ወረዳ ደጃኔ ሳይት) ተጠልለው የሚገኙ ተፈናቃይ የህብረተሰብ ክፍሎች ከአካባቢው ማህበረሰብ ጋር በማዋሃድና በማቀራርብ ሰላማዊና ዘላቂ ወደ ሆነ ኑሮ ለማሸጋገር ጥረት እየተደረገ ይገኛል። በመሆኑም በ10 ቡድን በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ የተደራጁ ተፈናቃዮች የራሳቸውን ገቢ በመፍጠር ላይ መሆናቸው እንዲሁም ለአካባቢው ማህበረሰብ ለኑሮ አስፈላጊ የሆኑ መሰረታዊ ሸቀጦችን በአቅራቢያቸው ማግኘት መቻላቸው፣

በአማራ እና የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ዞን፣ ወረዳዎች እና ልዩ ልዩ አካባቢዎች የሚኖሩ ተጎራባች ማህበረሰቦች መካከል ተከስቶ ከነበረው ግጭት ወደ ሰላማዊ ቀጠናነት እየተሸጋገሩ ይገኛሉ። በዚህም የተገኘ ውጤት፡-

- ✓ ለቀጠናው የፀጥታ ስጋት የነበሩ የጉምዝ አማፂያን፣ የኢ-መደበኛ አደረጃጀቶች፣ ነፍስ ገዳይና ህገ ወጥ እንቅስቃሴ ላይ የነበሩ 4844 እና በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ህዝቦች ክልል 100 ታጣቂ ሃይሎችን፤ ጋምቤላ ክልል 195 ታጣቂዎችን እንዲሁም 420 የቅማንት ታጣቂዎች በሰላም እጃቸውን ሰጥተው የተሃድሶ ስልጠና ወስደው ወደ ሰላማዊነት እንዲመለሱ በማድረግ ወደ ህብረተሰቡ እንዲቀላቀሉ ተደርጓል።
- ✓ የህግ የበላይነት ተግባራዊ በመደረጉ ተቋርጦ የነበረው የአዋሳኝ ህዝቦች ግንኙነት ወደነበረበት ማህበራዊ ትስስር መመለስ ተችሏል። የቆየውን የአብሮነት መንፈስ በማደስ የአካባቢው ሰላምና ፀጥታ ተሻሽሏል።

- ✓ የችግሩ ምንጭና ስረ መሰረታዊ ምክንያት ኢትዮጵያን ለማፈራረስ የሚሰራ የውጭ ኃይሎች እጅ እንዳለበት የጋራ መግባባት በመደረሱ ችግራቸውን በጋራ ለመፍታት የጋራ እቅድ ተዘጋጅቶ ወደ ተግባር ተገብቷል።
- ✓ በአንዳንድ የሀገሪቱ አካባቢዎች የህግ የበላይነት ተግባራዊ ለማድረግ በተደረገው ጥረት ተቋርጦ የነበረው የአዋሳኝ አካባቢ ግንኙነት ወደነበረበት ማህበራዊ ትስስር መመለስ ተችሏል። የቆየውን የአብሮነት መንፈስ በማደስ የአካባቢው ሰላምና ፀጥታ ተሻሽሏል። ለአብነት ያህል በቤንሻንጉል ክልል መተከል ዞንና በተወሳኝ አማራ ክልል አዊ ዞን አካባቢዎች፤ በደቡብ ክልል ኮንሶ ዞንና በአካባቢው ልዩ ወረዳዎች መካከል፤ በኦሮሚያና ሲዳማ አዋሳኝ አካባቢዎች፤ያለውን ማየት ይቻላል።

## 4.3. የተጠናከሩና ጥቅም ላይ የዋሉ ሀገር-በቀል የግጭት አፈታት ስርዓት፤

### 4.3.1. ሀገር-በቀል የግጭት አፈታት ስርዓትን በጥናት መለየት

ሀገር-በቀል የግጭት አፈታት ስርዓት ያለባቸውን ችግርና ድክመት በጥናት የመለየት ስራ ተከናውኗል። በዳሰሳ ጥናቱ መነሻነት ችግሩ ለመፍታት የሚያስችል ወጥ የሆነ የባህላዊ የግጭት መፍቻ ረቂቅ ሰነድ ተዘጋጅቷል።

በኦሮሚያ ክልል የተሻለ ሀገር-በቀል የግጭት አፈታት አደረጃጀት ስላለ ይህንን ተሞክሮ ሁሉም ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ወስደው ከራሳቸው ልምድ ጋር አዋህደው እንዲጠቀሙበት ዶክመንቱን በመስጠት እና ገለጻም በማድረግ ወደ ተግባር እንዲገቡ ማድረግ ተችሏል።

### 4.3.2. በተለዩ ሀገር-በቀል የግጭት አፈታት ስርዓት ላይ የተፈጠረ የጋራ ግንዛቤ

የገለልተኛ አማካሪ ቡድንና የማህበረሰብ ደህንነት ፓትሮል/ቅኝት አደረጃጀቶችን ማጠናከርና አቅማቸውን መገንባት በሁሉም ክልልች እና በሁለቱ ከተማ አስተዳደሮች ለሚገኙ በየደረጃው ላሉ የፖሊስና የሰላምና ፀጥታ አመራሮች በየገለልተኛ አማካሪ ቡድንና የማህበረሰብ ደህንነት ፓትሮል/ቅኝት ዙሪያ ስልጠና ለመስጠት እና አደረጃጀቶችን ለማጠናከር ዕቅድ የተያዘ ሲሆን በቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ለ50 አመራሮች፤ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ህዝቦች ክልል 106 አመራሮች፤ በሲዳማ ክልል ለ70 አመራሮች እና በጋምቤላ ክልል ለ41 አመራሮች በድምሩ 267 ከፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን ዩኒቨርስቲ በተጋበዙ ከፍተኛ ልምድና ዕውቀት ባላቸው ምሁራን ስልጠና እንዲያገኙ ተደርጓል። እንዲሁም አደረጃጀቶችን የማጠናከር ስራ ተከናውኗል።

ከባለድርሻ አካት ጋር በመተባበር በስነልቦና ማህበራዊ ድጋፍ በሰንዳፋ፤ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ሰላምና ደህንነት በግጭት መከላከልና አፈታት ላይ 30 ባለሙያዎች ስልጠና እንዲያገኙ ተደርጓል።

በተለዩ ሀገር-በቀል የግጭት አፈታት ስርዓት ላይ 60 ለሚሆኑ የሀገር ሽማግሌዎችና የሃይማኖት አባቶች ሀገር አቀፍ መድረክ በማዘጋጀት ሀገር በቀል ባሕላዊ የግጭት መፍቻ ዘዴዎ/ህጐች/ ላይ በዘርፉ ምርምር በካሄዱ፣ መጽሐፍ ባዘጋጁ እና የካበተ ልምድ ባላቸው አካላት የአቅም መገንቢያ እንዲሁም የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና እንዲያገኙ ተደርጓል። በየክልሎቻቸው የሚገኙ ልሞዶችንና ተሞክሮዎችን እንዲለዋወጡ በማድረግ የጋራ ግንዛቤ እንዲይዙ ተደርጓል። በተጨማሪም በሀገር አቀፍ ደረጃ ያሉ አገር በቀል የግጭት አፈታት ዕሴቶችን በተመለከተ 20 ጥናታዊ ጽሁፎች

በዩኒቨርሲቲ ምሁራን እንዲቀርቡ ታቅዶ 17 ጥናታዊ ጽሁፎች በአርባ ምንጭ ዩኒቨርስቲ ለ70 የሀገር ሽማግሌዎች፣ የሚመለከታቸው የፌደራል ተቋማት፣ ከተወካዮች ም/ቤት ቋሚ ኮሚቴ አባላት፣ ከአርባ ምንጭ ዩኒቨርስቲ እና ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ተጋባዥ እንግዶች በተገኙበት ቀርቦ ውይይት ከተደረገበት በኋላ የጥናት ሰነዶቹ የበለጠ ተደራጅተውና ተጠናቅረው በፖሊሲ ደረጃ ተሰንዶ ስራ ላይ እንዲውል አቅጣጫ ተሰጥቶበታል፡፡ ጥናታዊ ጽሁፎች ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ኢትዮጵያን ስተዲስ ጋር በመሆን በጆርናል ታትመው ጥቅም እንዲሰጡ እየተሰራ ይገኛል፡፡ በዚህም የተገኘ ውጤት

- ✓ ሃገር በቀል የግጭት አፈታት መልካም እሴቶች እየዳበሩ መምጣታቸው፤

### 4.3.3. ሀገር-በቀል የግጭት አፈታት ስርዓት እንዲፈታ የተደረገ አለመግባባቶችና ግጭቶች

ግጭት በተከሰተባቸው አካባቢዎች የሚገኙ የሀገር ሽማግሌዎችንና የሀይማኖት አባቶች አባገዳዎች ታዋቂ ሽማግሌዎች ችግሮቹን እንዲፈቱ በማስተባበር በርካታ ችግሮች እንዲፈቱ ተደርጓል፡፡ በዚህ መነሻ፡-

- በኦሮሚያ እና ድሬዳዋ 5 ወረዳዎች አዋሳኝ አካባቢዎች ያለ ችግር፣ በኦሮሚያ እና በሶማሌ እስከ ሞያሌ ያለው (መዩ ሙሉቄ፣ ባብሌ፣ ጃርሶ) ያለ ችግር፣ ኦሮሚያ ከሀረሪ ክልል ጋር በተጎራባች አካባቢዎች ያለ ችግር፣ እንዲሁም ኦሮሚያ እና አፋርና አካባቢ ያለ ችግር በእርቅ እንዲፈታ ተደርጎ በአሁኑ ሰዓት ማህበረሰቡ በሰላም እየኖረ ይገኛል፡፡
- ምዕራብ አርሲ ዞን፤ ኮኮሳ፤ ሻላ፣ ሲራሮ፤ መንሰቦ ችግሮች እንዳይፈጠሩ በሁለቱ ህዝቦች እና በአመራር ለአመራር ግንኙነት በየጊዜው ውይይት በማድረግ መልካም ስራዎች ተሰርተዋል፡ ፡ ችግሮች እንዲረግቡ ተደርጓል፡፡ በተጨማሪም ጭናክሰን ወረዳ በጃርሶ እና የሱማሌ ክልል ቱሉጉሌድ ወረዳ ገሪ ጎሳዎች መካከል የነበረው ችግር እና በአዋሽ ፈንታሌ እና የአፋር አዋሽ የነበረው ችግር በእርቅ እንዲፈታ ተደርጓል፡፡
- ምእራብ አርሲ፤ ከሲዳማ ጋር፣ በወንዶ ወረዳ እንታዬ እና 01 ኬላ ቀበሌ በሚባል አካባቢ የነበረ ግጭት በውይይት እና በእርቅ ተፈቷል፣
- ከሲዳማ ክልል በቢላቴ ዙሪያ ወረዳና ከኦሮሚያ ሲራሮ ወረዳ ጋር በባሌላ አካባቢ በተፈጠረዉ ግጭት የሰዉ ህይወት መጥፋት፣ የንበረት መወደምና ከቀያቸዉ መፈናቀል የተከሰተዉን ችግር የሁለቱም ክልል አመራሮች፣ የሀገር ሽማግሌዎችና የሀይማኖት አባቶች በጋራ በባሌላ አከባቢ የሠላም ኮንፈራንስ በማዘጋጀት የተፈጠረዉን ችግር በእርቅ መፍታት ተችሏል፡፡
- የአፋር አማራ፣ ከውስጥ ችግሮች (ግጭቶች) አንጻር የኦሮሞ ብ/ዞንና የሰሜን ሸዋ ዞን፤ በቤንሻንጉል ክልል መተከል ዞንና በአማራ ክልል አዊ ዞን ተጎራባች ወረዳዎች መካከል እንዲሁም የቅማንትና አማራ ማህበረሰቦች መካከል ችግሮች የተፈጠሩ ቢሆንም በሀገር በቀል የግጭት መፍቻ ዘዴዎችን መሰረት በማድረግ የተለያዩ የሃገር ሽማግሌዎች፣ ተጽዕኖ ፈጣሪ ሰዎች እንዲሁም በአመራሩ እና በህዝቡ ተሳትፎ ችግሩን መፍታት ተችሏል፡፡

- ቤኒሻንጉል-ጉሙዝ ክልል መተከል ዞን በጉሙዝ ማህበረሰብና አማራ ክልል አዊ ዞን መካከል የነበረው ችግር በፌደራል መንግስትና የሁለቱ ክልሎች ባለ ድርሻ አካላት በተገኙበት በጋራ በእርቅ ተፈቷል፣
- በደቡብ ክልል በአማሮ፣ ገላና፣ ቡርጂ በውስጣቸውና ከምዕራብ ጉጂ ዞን ሰረበርጉዳ ወረዳ ጋር የነበረው በኮንሶ ዞን ኮንሶ ወረዳ፣ ደራሽ አማሮ፣ አሌ እና ሰገን ዙሪያ ወረዳ የነበረው ግጭት መፈታቱ
- ደራሽ ወረዳ በኩሱሜ ጎሳዎች መካከል የነበረው ችግር ተፈቶ የተፈናቀሉ ሰዎች ወደ ቀያቸው እንዲመለሱ ተደርጓል፡፡
- ደቡብ/ብ/ብ/ህ/ክልል በኦሞ ወንዝ ተፋሰስ ቤልት አካባቢ በተለይም በአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች የሚታዩ የግጭት መንስኤዎች፣ ሲሆኑ በአሁኑ ሰዓት በአብዛኛው ግጭቶች በአመራር ለአመራርና በህዝብ ለህዝብ ውይይት በእርቀ ሰላም ችግሮች እየተፈቱ በመሆኑ አንጻራዊ ሰላም መኖሩን በመስክ ዳሰሳ ጥናት ማረጋገጥ ተችሏል፡፡
- አማራ ክልል ከውስጥ ችግሮች (ግጭቶች) አንጻር የኦሮሞ ብ/ዞንና የሰሜን ሸዋ ዞን፤ በቤንሻንጉል ክልል መተከል ዞንና በአማራ ክልል አዊ ዞን ተጎራባች ወረዳዎች መካከል እንዲሁም የቅማንትና አማራ ማህበረሰቦች መካከል ችግሮች የተፈጠሩ ቢሆንም በሀገር በቀል የግጭት መፍቻ ዘዴዎችን መሰረት በማድረግ የተለያዩ የሃገር ሽማግሌዎች፣ተጽዕኖ ፈጣሪ ሰዎች እንዲሁም በአመራሩ እና በህዝቡ ተሳትፎ ችግሩን መፍታት ተችሏል፡፡ እርቀ ሰላምና የህዝብ ለህዝብ ኮንፈረንሶች በተደጋጋሚ ተደርገዋል፡፡ በዚህም በተደጋጋሚ ይከሰቱ የነበሩ ግጭቶችን ማስቀም ተችሏል፤ ተጎራባች ማህበረሰቦች በተለያዩ ማህበራዊ ጉዳዮች አብረው መዋል ጀምረዋል፡፡
- ጋምቤላ ክልል በሁለቱ ጎሳዎች መካከል(ኑዌር እና አኙዋክ) ከመሬት ጋር በተያያዘ የተከሰቱ ግጭቶች/ማጃንግ ዞን/ የሚፈጠሩ አለመግባባቶችና ግጭቶች በሀገር ሽማግሌዎች፣ የሀይማኖት አባቶችና ተፅኖ ፈጣሪ ሰዎች ሁለቱን አካላት በማቀራረብ እንዲፈቱ ጥረት ተደርጓል፡፡ በዚህም የተገኘ ውጤት፡-
    - ✓ የአመራር ለአመራር እና ህዝብ ለህዝብ ግንኙነት ተሻሽሏል፣
    - ✓ የተፈናቀሉ ማህበረሰቦች ወደ ቀበሌያቸው ተመልሰው መኖር ጀምረዋል፣
    - ✓ በገበያና በሌሎች ማህበራዊ ግንኙነቶች በጋራ መጠቀም ጀምረዋል፣
    - ✓ የንብረት ውድመት፣ መገዳደልና መጠቃቃት እየቀነሰ መጥቷል፣
    - ✓ ማህበረሰቡ ግጭትን በራሱ አቅም ለመፍታት ተነሳሽነቱ እያደገ መምጣቱ፣

## 5. የፌዴራል ስርዓቱንና የመንግስታት ግንኙነትን ማጠናከርና ማሳደግ

### 5.1. የተጠናከረ የፌዴሬሽን አባል መንግስታትና የማህበረሰብ የግንኙነት

#### 5.1.1. የፌዴራል ክልልና የክልል ክልል ግንኙነቶችን ለማጠናከር የተካሄደ የግንኙነት መድረክ

**የአፋርና ሶማሌ ክልል የአመራር መድረክ -** በአፋር ክልል በአፋርና ኢሳ ማህበረሰብ መካከል የተከሰተውን ግጭት በዘላቂነት መፍታት እንዲቻል ከአፋርና ሶማሌ ክልል በየደረጃው የሚገኙ ከፍተኛ አመራር የግንኙነት መድረኮች እንዲፈጠር ተደርጓል፡፡ በዚህም በማህበረሰቡ መካከል የተፈጠረውን ግጭት ለመፍታት የሚያስችል ዕቅድ እንዲዘጋጅ፣ የሚመለከታቸው አመራር በሰላም ሚ/ር አመራሮች አስተባባሪነት ወደ ቦታው በመውረድ የአመራርና የማህበረሰብ የውይይት መድረኮች እንዲዘጋጁና እንዲተገበሩ የተደረገ ሲሆን በወቅቱ ግጭቱ ተባብሶ የከፋ አደጋ እንዳይደርስ ያስቻለ ሲሆን ቀጣይ አቅጣጫዎች እንዲቀመጡ አስችሏል፡፡

**የአማራና የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል የአመራር መድረክ -** በአማራ ክልል (አዊ ዞን) እና በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል (መተከል ዞን) አዋሳኝ አካባቢዎች ተከስቶ የነበረው ግጭት በዘላቂነት ለመፍታት የፌዴራሉና የክልሎቹ መንግስታት አስፈላጊው የጸጥታ ኃይል በማስማራት ከፍተኛ ጥረት አድርገዋል፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ የሰላም ሚ/ር አመራሮች ከሚመለከታቸው የፌዴራልና የክልል አመራር ጋር በጋራ መድረኮች ተፈጥረው ችግሩ የሚቀረፍበትን ስልት በመንደፍና እንዲተገበር በማገዝ፤ የሎጅስቲክስ፣ የፋይናንስና የባለሙያ ድጋፍ በማድረግና እንዲሁም በየደረጃው ተከታታይ የአመራር ለአመራር እና የህዝብ ለህዝብ የግንኙነት መድረኮች እንዲፈጠሩ መግባባት ላይ በመድረስና ተግባራዊ እንዲሆኑ ማገዝ ተችሏል፡፡ በተጨማሪ ክልሎቹ በጋራ የሚሰሩበትን አሰራሮች እንዲፈጠር (የጋራ የሰላምና ልማት ፎረም እንዲቋቋም)፣ ችግሩን መቅረፍ የሚያስችል የጋራ ዕቅድ እንዲዘጋጅ፣ ዕቅዱን ሁሉም በኃላፊነትና በተጠያቂነት ተግባራዊ እንዲያደርግና አፈጻጸሙንም በጋራ መድረክ እንዲገመገም በማገዝ፤ ቀሪ መፈታት የሚገባቸው ችግሮች ተለይተው በአመራርና በህዝብ ለህዝብ ግንኙነት መድረክ እንዲፈታና በክልሎቹ መካከል የተፈጠሩ ችግሮች በዘላቂነት ተቀርፈው በኅብረተሰቡ መካከል ቀድሞ የነበረው የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ትስስሩ ወደ ቦታው እንዲመለስ ማድረግ ተችሏል፡፡

**የአማራና ኦሮሚያ ክልል የአመራር መድረክ -** በአማራና ኦሮሚያ ክልሎች መካከል ወደ አዲስ አበባ በሚያስኬደው መንገድ የተሽከርካሪ እንቅስቃሴ መገታትና ከመንገድ መዘጋት ጋር ተያይዞ የተፈጠረው ችግርን ለመቅረፍ በሰላም ሚ/ር ከፍተኛ አመራሮች አስተባባሪነት የሁለቱ ክልሎች ከፍተኛ አመራሮች መድረክ ተዘጋጅቶ በወቅቱ የተፈጠረው ችግር በውይይት እንዲፈታ ተደርጓል፡፡ እንዲሁም የሁለቱ ክልሎች የሰላምና ጸጥታ ቢሮ ኃላፊዎችና የየክልሎቹ ርዕሰ መስተዳድር አማካሪዎች የተሳተፉበት የውይይት መድረክ ማዘጋጀት ተችሏል፡፡ በዚህም በክልሎቹ መካከል ያለውን ግንኙነት በማጠናከር ችግሮችን ለመፍታትና ቀጣይነት ባለው መንገድ ትስስሩን ማጠናከር እንዲቻል የጋራ የሰላምና ልማት ፎረም የመመስረት አስፈላጊነትና በተለይም በሁለቱ ክልሎች አዋሳኝ አካባቢዎች (በአማራ ክልል ሰሜን ሸዋ እና በኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ሸዋ) ያለውን ያለመግባባትና ግጭት በዘላቂነት መፍታት በሚቻልበት ሁኔታ ላይ ውይይት ተደርጓል፡፡ በክልሎቹ መካከል የተከሰቱ/የሚከሰቱ ችግሮችን በተቀመጠ አሰራር በውይይት ብቻ በመፍታት አስፈላጊነት ላይ መግባባት የተደረሰ ሲሆን ቀጣይነት ያላቸው ተመሳሳይ የአመራር ለአመራር እና የህዝብ

ለህዝብ የግንኙነት መድረክ ማካሄድ እንደሚገባ ታምኖበት ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ከፍተኛ አመራር እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡

**በኦሮሚያ እና በሶማሌ ክልል የአመራር መድረክ፡- በኦሮሚያ ክልል** በባሌ ዞን እና **በሶማሌ ክልል** ሊበን ዞን ጉራ ዳሞሌ ወረዳዎች መካከል ተከስቶ የነበረውን የወሰን ይገባኛል ግጭት በዘላቂነት መፈታት እንዲችል የሰላም ሚኒስቴር አመራር በየደረጃው ተከታታይነት ያላቸው የተናጠልና የጋራ መድረኮች ከክልሎቹ ጋር በጋራ እንዲፈጠሩ አድርጓል፡፡ የተፈጠረውን ችግር መቅረፍ እንዲቻል ከሰላም ሚኒስቴር፣ ከፌደራል ፖሊስ እና ከሁለቱ ክልል አመራሮችን ያካተተ የመስክ ቡድን እንዲደራጅና በመስክ ተጨባጭ እርምጃዎች ደረጃ በደረጃ እንዲወሰድ ተደርጓል፡፡ እንዲሁም በሚመለከታቸው የፌዴራልና የክልል አመራር አካላት ተከታታይነት ያለው ድጋፍ፣ ክትትልና ግምገማ በማድረግ የእርምት እርምጃዎችን በመውሰድ የተፈጠረውን ችግር በዘላቂነት ለመቅረፍ እንቅስቃሴ ተደርጓል፡፡ በዚህም ተከስቶ የነበረው ደም አፋሳሽ ግጭት እንዲቆም፣ የታጠቁ የጸጥታ ሀይሎች ከአካባቢው እንዲወጡ ከማድረጉም በላይ ለረዥም ጊዜ የተዘጉ መንገዶች እንዲከፈቱና የተዘረፈ ንብረት (በተለይም 49 ግመል፣ 70 የቀንድ ከብት፣16 አህያ፣ 32 ፍየልና በግ፣ 1 ሲኖትራክ መኪና) ለባለቤቶቻቸው እንዲመለሱ ማድረግ አስችሏል፡፡ እንዲሁም በተፈጠረው ችግር ምክንያት ከቀያቸው የተፈናቀሉ የህብረተሰብ ክፍሎች እንዲመለሱ ማድረግ አስችሏል፡፡ በዚህም ኦሮሚያ ክልል 24,740 ሰዎች እና ሶማሌ ክልል 9,450 አባወራዎች ወደ ቀያቸው እንዲመለሱ ተደርጓል፡፡ ችግሩን በማህበረሰብ ውይይት በዘላቂነት መፍታት እንዲቻልም ህዳር 17 ቀን 2015 ዓ.ም ከሁለቱም ክልል ተዋሳኝ አካባቢዎች በድምሩ ከ5,000 በላይ የማህበረሰብ ክፍሎች በተገኙበት በሊበን ዞን ጉራዳሞሌ ወረዳ ሃሮ ድቤ ከተማ የሁለቱም ክልል ምክትል ርዕሰ መስተዳደሮችና ሌሎች የሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች በተገኙበት በተዘጋጀ ታላቅ የእርቀ ሠላም ኮንፈረንስ እርቅ እንዲፈጸምና ችግሩ እንዲቀረፍ ማድረግ ተችሏል፡፡

**በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ህዝቦች እና ጋምቤላ ክልል አመራር መድረክ -** የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ህዝቦች ክልል ከጋምቤላ ክልል በሚዋሰንባቸው ዞን ወረዳና ቀበሌዎች አካባቢ በሚካሄድ ግድያ፣ ዝርፊያ፣ ህገ ወጥ የመሳሪያ ዝውውር ወዘተ… ምክንያት የተፈጠሩ የሰላምና ጸጥታ እጦት ለመቅረፍ ክልሎቹ በጋራ ሲሰሩ ቢቆዩም ጠንካራ የሆነና ችግሮቹን መፍታት የሚያስችል የአመራር ለአመራርና የህዝብ ለህዝብ ግንኙነት ባለመፈጠሩ በሚፈለገው መልኩ ሰላምን ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡ በመሆኑም የሰላም ሚ/ር ከክልሎቹ ጋር በጋራ በተለይ በአካባቢው ዘለቂ ሰላም እንዲረጋገጥ በደቡብ ም/ኢ/ህ ክልል ሶስት ዞኖችና በጋምቤላ ክልል ሁለቱ ዞኖች አጎራባች አካባቢዎች የሚገኙ ዞን፣ ወረዳና ቀበሌ ጀምሮ የአመራርና የማህበረሰብ መድረኮችን በመፍጠር ችግሮች በተገቢው መንገድ እንዲለዩ፣ በተለዩ ችግሮች ላይ በሚመለከታቸው አካላት መግባባት ተፈጥሮና በዕቅድ ተይዘው በየደረጃው እንዲፈጸሙ የማድረግ ተግባራት በአመራር ደረጃ ሲከናወን ቆይቷል፡፡ ይህን ጥረት በማጠናከር ችግሮችን በጋራ ጥረት መቅረፍ እንዲቻል በየደረጃው የሚገኙ (የክልል፣ የዞንና የወረዳ) አመራሮች ቀደም ሲል በየክልሎቹ በተለዩ ችግሮች፣ የጋራ መግባባት ተደርሶባቸውና በእቅድ ተይዘው በጋራ ጥረት ተተግብረው ያስገኙትን ውጤት፣ በቀጣይ በሁለቱም ክልሎች መከናወን በሚገቡ ተግባራት ዙሪያ በሁለቱም ክልሎች ም/ር/መስተዳድሮች መሪነት በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ህዝቦች ክልል ሚዛን ከተማ በተዘጋጀ የጋራ የማጠቃለያ የአመራር መድረክ በክልሎቹ መካከል ዘላቂ ሰላምን በመገንባት በኩል የተከናወኑ ተግባራት ተገምግመዋል፡፡

በመድረኩም በፌዴራሊዝም፣ በመንግስታት ግንኙነት፣ በግጭት አፈታት (በመደበኛውና በአገር በቀል)፣ በአመራር ለአመራርና በህዝብ ለህዝብ ግንኙነት ችግሮችን በመቅረፍ ረገድ ግንዛቤ እንዲጨብጡ ተደርጎ በውይይት እንዲዳብር ተደርጓል፡፡ መድረኩ የሁለቱም ክልል አመራር አካላት በአዋሳኝ ዞኖች፣ ወረዳዎችና ቀበሌዎች በዕቅድ ተይዘው የተከናወኑ የተግባራት አፈጻጸም ያሉበትን ደረጃ መረዳት የተቻለበት፤ ችግሮችን ለመቅረፍ በአመራሩ በተደረገ ድጋፍና ክትትል በሁለቱ ክልሎች አዋሳኝ አካባቢዎች በማህበረሰቡ መካከል ቀድሞ የነበረው የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ግንኙነት ወደነበረበት እንዲመለስ ያስቻለበት፣ በአዋሳኝ አካባቢዎች ሊፈጠሩ የሚችሉ ችግሮችን መከላከል እንዲቻል የጋራ የጸጥታና ሰላም ጥምር ኮሚቴ ተደራጅቶ ወደ ሥራ እንዲገባ የተደረገበትና ችግሮች ቢከሰቱ እንኳን በአመራርና በማህበረሰብ ውይይት ብቻ መፍታት እንደሚገባ ትምህርትና ልምድ የተቀሰመበት እንደነበር ማየት ይቻላል፡፡ ከዚህ ባሻገር ሁለቱ ክልሎች በአካባቢያቸው ሰላምን ለማረጋገጥ በጋራ የጀመሩትን ግንኙነት በበለጠ በማጠናከር በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት በማስተሳሰር ህዝቡ ተጠቃሚ እንዲሆን የጋራ የሰላምና የልማት ፎረም ለመመስረት መግባባት ላይ ተደርሶ ወደ ተግባር የተገባበት ነበር፡፡

**አምስቱ የምስራቅ ተጎራባች ክልሎች/ከተማ አስተዳደር የአመራር መድረክ -** የምስራቁ ኢትዮጵያ ተጎራባች ክልሎች (የሐረሪ፣ የአፋር፣ የኦሮሚያና የሶማሌ ክልሎችና የድሬደዋ አስተዳደር) መካከል የነበረውን/ያለውን ግንኙነት በማጠናከር ትስስሩ ወደ ላቀ ደረጃ ማድረስ እንዲቻል በሰላም ሚ/ር ከፍተኛ አመራር፣ በክልሎቹ የሰላምና ጸጥታ ቢሮ አመራርና የሚመለከታቸው ባለሙያዎችን (በድምሩ 35 ወንድ 30 ሴት 5) ያሳተፈ የአመራር መድረክ በድሬደዋ ከተማ ሰኔ 11 ቀን 2015ዓ.ም ተዘጋጅቷል፡፡ በመድረኩ የፌዴራሊዝምና መንግስታት ግንኙነት ጽንሰ ሃሳብ፣ የመንግስታት ግንኙነት ሥርዓት መወሰኛ አዋጅ እና የክልል ክልል የጋራ የሰላምና ልማት የትብብር ቻርተርን የተመለከቱ ሰነዶች ቀርበው ግንዛቤ እንዲጨበጥባቸው የተደረገ ሲሆን በክልሎቹ መካከል የነበረውን ግንኙነት በላቀ ደረጃ ማጠናከር በሚያስችል መልኩ ውይይት ተደርጓል፡፡ በውይይቱ በተለይ በክልሎቹና በከተማ አስተዳደሩ የነበረው ግንኙነት የተቆራረጠ፣ የመደበኛ የአሰራር ሥርዓቱን ያልጠበቀና ሰላምና ጸጥታ ላይ ብቻ ያተኮረ መሆኑ የተነሳበትና የፎረሙ ቀጣይ ግንኙነቱ ይህን ክፍተት ያረመ በተለይም አሰራሩን በጠብቀና ከሰላምና ጸጥታ ሥራዎች ባሻገር የህዝቡ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ግንኙነትን በማጠናከር ረገድ ሰፊ ሥራ የሚሰራበት መሆን እንደሚገባው የጋራ መግባባት ተደርሶበታል፡፡ ስለሆነም በጋራ ፎረሙ ቻርተር በግብዓት ዳብሮ ለአሰራር በሚመች መልኩ ማስተካከል እንዲችሉ ሰነዱ እንዲደርሳቸው፣ በየካቢኔዎቻቸው እንዲታይና በቀጣይ መድረክ የጋራ ውይይት እንዲደረግበት በመግባባት ተጠናቋል፡፡

**የአማራ፣ አፋርና ትግራይ ክልል የአመራር መድረክ -** በሀገራችን ሰሜናዊ ክፍል የተከሰተው ጦርነት በሰላም ስምምነት ከቆመ በኋላ በክልሎቹ መካከል የነበረው ግንኙነት ወደነበረበት እንዲመለስ በሚያስችል መልኩ ባለመሰራቱ በህዝቡ የእርስበርስ ትስስር ላይ ከፍተኛ ጫና መፍጠሩ ይታወቃል፡፡ የተፈጠሩ ችግሮችን በሁሉም አካላት ርብርብ ለመቅረፍና በቀጣይ በክልሎቹና በህዝቡ መካከል የነበረውን ግንኙነት በማሻሻል ማጠናከር እንዲቻል የሰላም ሚ/ር ከሶስቱ ክልሎች የሰላምና ጸጥታና እንዲሁም የትራንስፖርት ቢሮ ኃላፊዎች ጋር ውይይት ተካሂዷል፡፡ በመደረኩ ከሰላም ስምምነቱ በኋላ የተጀመሩ ሰፋፊ ሥራዎች፣ የክልሎቹ ከፍተኛ አመራሮች መካከል የተደረጉ ግንኙነቶች ወዘተ... የሚያበረታቱ ቢሆኑም የተጀመሩ ሥራዎች ተጠናክረው የሚታዩ ችግሮች

እንዲፈቱ በሚያስችል አቅምና ፍጥነት ያለመሰራቱ፣ የሚታዩ ችግሮችን በመቅረፍ በክልሎቹና በህዝቡ መካከል የነበረውን ትስስር መልሶ በማስቀጠልና በማጠናከር ረገድ ሰፊ ክፍተት መታየቱ በውይይት ተነስቷል፡፡

ስለሆነም ያለፍንባቸው ጊዜያት በእጅጉ አስቸጋሪና ውስብስብ ቢሆኑም ያሉብንን ችግሮች በመለየት፣ ቅድሚያ ሊሰጣቸው የሚገቡ ተግባራት ቅድሚያ በመስጠትና በሁሉም ተቋማት በዕቅድ እንዲያዙና በጋራ እንዲፈጸሙ በማድረግ፣ በክልሎቹ መካከል በየጊዜው የሚታዩ ችግሮችን በየደረጃው በተቀናጀ አቅም በመቅረፍ ግንኙነቱ እንዲጠናከር ከአመራር ግንኙነት ባሻገር የህዝብ ለህዝብ ግንኙነቱ ላይ ትኩረት ሰጥቶ በመስራት ላይ፣ የህዝቡን ግንኙነት የበለጠ ሊያሳልጡ የሚችሉ የሰዎች ዝውውር፣ የትራንስፖርት እንቅስቃሴና የሸቀጦች ልውውጥ እንዲኖር የሚያስችሉ መንገዶች እንዲከፈቱ በማድረግና እንዲሁም ሌሎች ተግባራት በየጊዜው በሚደረጉ ምክክሮች ወደ ጋራ ዕቅድ መጥተው ተግባራዊ ማድረግ በሚገባበት ሁኔታ ላይ እና  በመድረኩ የተነሱ ተግባራት አፈጻጸሙ ከአንድ ወር በኋላ በመገምገም ቀጣይ አቅጣጫዎችን እንዲመላከቱ እንደሚደረግ መግባባት ላይ ተደርሶ ውይይቱ ተጠናቋል፡፡

በአጠቃላይ በበጀት ዓመቱ የፌዴራል ክልል የክልል ክልል የአመራር ለአመራር ግንኙነቶችን ማጠናከር እንዲቻል 12 የግንኙነት መድረኮችን ለማካሄድ ታቅዶ 15 (125%) መድረኮችን ማካሄድ ተችሏል፡፡ ከዚህም ግንኙነት መድረክ በተጨባጭ የተገኙ ውጤቶች ፡-

- ✓ በክልሎች አዋሳኝ አካባቢዎችና በክልሎች ውስጥ የሚከሰቱ ወይም ሊከሰቱ የሚችሉ ችግሮችን ተከታታይነት ባለው የአመራር ለአመራር የግንኙነት መድረኮች መፍታት እንደሚቻል ግንዛቤ አድጓል፡፡
- ✓ በክልሎች መካከል በሚደረግ የአመራር ለአመራር ግንኙነት የተከሰቱ የወሰን ይገባኛል ችግሮች እንዲፈቱ በማድረግ በሰውና በንብረት ላይ ይደርስ የነበረው የከፋ አደጋ እንዳይደርስ አስችሏል፣
- ✓ በክልሎች አዋሳኝ አካባቢና ተያይዞም በክልሎቹ ውስጥ ተከስቶ የነበረው ግጭት ደረጃ በደረጃ እንዲቀረፍ ተደርጎ በክልሎቹ ውስጥም ሆነ በአዋሳኝ አካባቢዎች የሚገኙ የህብረተሰብ ክፍሎች  መካከል የነበረው የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ግንኙነት (የገበያ ልውውጥ፣ የልማት ተቋማትን በጋራ መገልገል ወዘተ…) ተጠናክሮ እንዲቀጥል አስችሏል፡
- ✓ የክልል ክልል ግንኙነትን በማጠናከር ችግሮችን ለመቅረፍ ከሚያስችሉ ተግባራት አንዱ የአመራር ለአመራር ግንኙነት መድረክ ቢሆንም ግንኙነቱ በአሰራር ተደግፎ ቀጣይነት ባለው መልኩ የነበረውን ትስስር በአካባቢው ጸጥታን ከማስፈን ባሻገር በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት የታገዘ እንዲሆን  የጋራ የሰላምና ልማት ፎረሞች ማቋቋም አስፈላጊ መሆኑን ግንዛቤ የተያዘበት፣ ፍላጎቱ የጨመረበትና ለፎረሞቹ መቋቋም በአመራር ደረጃ መግባባት የተደረሰበት መሆኑ፤

**በአማራ እና ኦሮሚያ የማህበረሰብ አቀፍ ውይይትና ግንኙነት ለዘላቂ ሰላም**፡- የአማራ እና የኦሮሞ ህዝቦች በቋንቋ፣ በባህልና በሃይማኖት ቢለያዩም በሰላምና በመተሳሰብ አብረው የኖሩና ሀገራችን አሁን ለደረሰችበት እድገት ትልቅ ሚና ተጫውተዋል፡፡ የውስጥና የውጭ ለሀገራችን መልካም ነገር

የማይመኙ ሀይሎች ባደረጉት ሴራ ምክንያት በሁለቱ ማህበረሰቦች መካከል ጠላትነትን በመፍጠር አንድነቷ ለማፍረስ የሚደረገውን ክፉ ውጥኖች በጋራ ተከላክዋል፡፡ ይህ ለዘመናት የዘለቀው መስተጋብር እና ውህደት ለሀገራችንና ሌሎች አካላት የማዕዘን ድንጋይ ሆነው ሊያገለግሉ እንደሚችሉ ይታመናል፡፡

ይሁንና አሁን ላይ ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ አንዳንድ ልሂቃን ሆን ብለውም ይሁን በሌላ ምክንያት ለታሪካዊ ክፉ አሳቢ ሃይሎች እኩይ ዓላማ ማስፈጸሚያ መሳሪያ እየሁኑ ይገኛል፡፡ በዚህም ከእነዚህ ሁለት ብሄሮች የተውጣጡ አንዳንድ ልሂቃን በዚህ ወንጀል ሰለባ ሲሆኑ ይታያል፡፡

መንግስት ይህንን ሁኔታ ለመቀልበስና ልሂቃኑን ለማቀራረብ ብሎም በኢትዮጵያ ያለፈ ታሪክ ላይ በየፊናቸው የያዙትን በመሠረታዊነት የተራራቁ አመለካከቶችን በውይይት ለመፍታት የሚያስችሉ ስራዎችን በመስራት ላይ የሚገኝ ሲሆን በዚህም እነዚህ አካላት ሊያቀራርቡ የሚችሉ የተናጠልና የጋራ መድረኮች ከኦሮሚያ የተውጣጡ አካላት በደብረዘይት ከተማ እና ከአማራ ክልል የተውጣጡ አካላት በባህርዳር የተናጥል ውይይቶችን አካሂደዋል፡፡

እንዲሁም በሰላም ሚኒስቴር አስተባባሪነት አጠቃላይ ሂደቱን ማስፈጻሚ የሰነድ ዝግጅት እና ፕሮግራሞቹ የሚፈጸሙበት ሁኔታ የሚከታተል ከሁለቱ ክልሎች የተውጣጣ ግብረ ሀይል ተቋቋሞ ሂደቱ እየቀጠለ ይገኛል፡፡ በቀጣይ ከ230 በላይ ተሳታፊዎችን ያካተተ የጋራ መድረክ በአዲስ አበባ ለማካሄድ የሚያስችል የፋይናንስ ማፈላለግ ስራ ከUSAID አካላት ውይይት ተደርጎ ስምምነት ላይ ተድርሷል፡፡ እስካሁን ባለው ሂደት የተገኙነ ውጤቶችም፡-

- ✓ ሁለቱ ቡድኖች በየፊናቸው ምን አይነት ኢትዮጵያን ለመገንባት ከተወያዩ በኃላ የጋራ እስቤና አሰራር እንደሚስፈልግ ተስማምተዋል፤
- ✓ ለረጅም ጊዜ የቆዩ ግጭቶችን እና ውጥረቶችን በአካታች ውይይት በዘላቂነት ለመፍታት የጋራ መግባባት ተደርሷል፡፡
- ✓ ስላጋጠሙ ገደቦች እና መሰናክሎች እና እነዚህን የማሸነፍ መንገዶች በመወያየት ስልቶችን በጋራ ቀይሰው ለመስራት ተግባብተዋል፡፡

### 5.1.2. የመንግስታት ግንኙነቶችን ለማሳለጥ የተደራጁና የተቋቋሙ አዳዲስና ነባር ፎረሞች፤

### ነባር ፎረሞችን ማጠናከር

በፌዴሬሽኑ አባል ክልሎች መካከል የሚደረጉ ግንኙነቶችን የማሳልጡ 4 ነባር ፎረሞች (በቤ/ጉሙዝና አማራ ክልል፣ በቤ/ጉሙዝ፣ በጋምቤላና በኦሮሚያ ክልል፣ በኦሮሚያና በሶማሌ ክልል እንዲሁም በ5 የምስራቅ ኢትዮጵያ ተጎራባች ክልሎች) ያሉባቸውን ክፍተቶች ለመለየትና ክፍተቶችን መሠረት ያደረገ ድጋፍ ለማድረግ የዳሰሳ ጥናት ተደርጎ ሪፖርት ቀርቧል፡፡ ከጥናቱ ግኝት በመነሳት ፎረሞቹ በአደረጃጀት፣ በአሰራርና በሰው ኃይል (የአቅምና በስራ ላይ የተሰማራ የሰው ሃይል ቁጥር) ክፍተት ያለባቸው መሆኑን መረዳት ተችሏል፡፡ በመሆኑም ነባር ፎረሞችን ማጠናከር እንዲቻል በድምሩ 79 (ወ 70 ሴ 9) የፎረሞቹን አመራርና ባለሙያዎች እንዲሁም ከሁሉም ክልሎች ሰላምና ጸጥታ ቢሮዎች የተውጣጡ በመንግስታት ግንኙነት ዙሪያ የሚሰሩ አመራርና ባለሙያዎች አቅም የሚያጎለብት የሥልጠናና የልምድ ልውውጥ መድረክ በተለይም

በፌዴራሊዝም፣ በመንግስታት ግንኙነት፣ በመንግስታት ግንኙነት ሥርዓት መወሰኛ አዋጅ፣ በግጭት መከላከልና አፈታት ጽንሰ ሃሳብና የተግባር አፈጻጸም ዙሪያ ግንዛቤ እንዲጨብጡ ተደርጓል፡፡ በተጨማሪ የተሻለ አፈጻጸም ያላቸው ፎረሞች ያላቸውን ምርጥ ተሞክሮ ሌሎች መቅሰም በሚያስችል መልኩ ሰነዶች ቀርበው ነባሮቹም ሆኑ ፎረም ሊመሰርቱ ያቀዱ ክልሎች ልምድ የመቅሰም ዕድል ተፈጥሮላቸዋል፡፡ የነባር ፎረሞችን አፈጻጸም ማሻሻል እንዲቻል ከክልል ሰላምና ጸጥታ ቢሮ ኃላፊዎች ጋር ውይይት የተደረገ ሲሆን ድጋፋዊ ክትትል ተደርጓል፡፡ በተለይ 5ቱ የምስራቅ አጎራባች ክልሎች ፎረም መደበኛ አሰራርን የተከተለ ባለመሆኑ ግንኙነቶቹ መቆራረጥ የታየበት መሆኑን ከግንዛቤ ገብቶ በዘርፉ ሚ/ር ዴኤታ የተመራና የየክልሎቹ የሰላምና ጸጥታ ቢሮ/ም/ቢሮ ኃላፊዎች በተገኙበት የጋራ ውይይት በማድረግ የማጠናከር ሥራ ተሰርቷል፡፡ የፎረሞቹን ሥራ በቴክኖሎጂ ማገዝ እንዲቻል ለአማራና ቤ/ጉሙዝ እንዲሁም ለኦሮሚያ፣ ቤ/ጉሙዝና ጋምቤላ ክልሎች የጋራ የሰላምና የልማት ፎረሞች 35 ታብሌቶች ድጋፍ ተደርጓል፡፡ በተጨማሪ የተሻለ አፈጻጸም ያሳዩ ፎረሞች የጀመሩትን ሥራ አጠናክረው እንዲቀጥሉ ማድረግ እንዲቻል የአማራና ቤ/ጉሙዝ፤ የኦሮሚያ፣ ቤ/ጉሙዝና ጋምቤላ፤ አዲስ የሚቋቋመው የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ህዝቦችና ጋምቤላ ክልል የጋራ ሰላምና ልማት ፎረምና እንዲሁም ለአማራ ክልል በይነ መንግስታት ማስተባበሪያ ቢሮ በድምሩ 7 ላፕቶፖችን ድጋፍ ተደርጓል፡፡

## አዳዲስ ፎረሞችን ማቋቋም

በክልሎች መካከል ያለውን ግንኙነት በሁሉም መስክ (በሰላምና በልማት) ተጠናክሮ ትስስሩ የላቀ እንዲሆን ለማድረግ አዳዲስ ፎረሞችን ማቋቋም አስፈላጊ በመሆኑ 2 አዳዲስ ፎረሞችን (በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ህዝቦች ክልል እና በጋምቤላ ክልል እንዲሁም በአማራ ክልል እና በአፋር ክልል) ለማቋቋም እንቅስቃሴ ተደርጓል፡፡ በዚህ ረገድ ዘርፉ በየክልሎቹ ለአመራርና ባለሙያዎች በሥልጠና አቅማቸውን የመገንባት፣ በክልል የሚገኙ የሚመለከታቸው ከፍተኛ አመራሮች በጋራ ትብብር ቻርተሩ ዙሪያ ግንዛቤ እንዲጨብጡና ቻርተሩን በግብዓት እንዲያዳብሩ ተደርጓል፡፡ አዳዲስ ፎረም የሚያቋቁሙ ክልሎች ርዕሰ መስተዳድሮች ቻርተሩን ተቀብለው ለመፈራረም ዝግጁ ቢሆኑም አመራሮቹ በነበሩባቸው ተደራራቢ የመንግስት ኃላፊነት የተነሳ የፊርማ ሥነ ሥርዓቱ በታቀደው ጊዜ አልተከናወነም፡፡

በአጠቃላይ በፌዴሬሽኑ አባል ክልሎች መካከል የሚደረጉ ግንኙነቶች የሚያሳልጡ 4 ነባር ፎረሞችን ለማጠናከርና 2 አዳዲስ ፎረሞችን ለማቋቋም ታቅዶ 4 ነባር ፎረሞችን የማጠናከርና 2 (100%) አዳዲስ ፎረሞችን የማቋቋም ሥራ ተሰርቷል፡፡ በመሆኑም ዕቅዱን በመፈጸም የተገኙ ውጤቶች ፡-

- ✓ በፌዴራልና በክልሎች ተመስርተው ወደ ሥራ ገብተው የነበሩ ፎረሞች ያሉባቸውን ክፍተቶች በመለየት ለመደገፍና ውጤታማ ለማድረግ የሚያስችል አቅም አድኋል፡፡
- ✓ ነባር ፎረሞች አዳዲስ ለሚቋቋሙ ፎረሞች ያላቸውን ልምድ በማካፈላቸውና አቅማቸው በሥልጠና በመገንባቱ የክልል ክልል መንግስታት ግንኙነትን ለማጠናከር የሚቋቋሙ ፎረሞችን ወደ ሥራ በማስገባት ረገድ ግንዛቤው አድኋል፡፡

- ✓ በክልል ደረጃ በፌዴራሊዝምና መንግስታት ግንኙነት ዙሪያ አቅም ለመገንባት በተደረገ እንቅስቃሴ የክልል ክልል ግንኙነትን ለማሳለጥ የሚያስችሉ ነባር ፎረሞች እንዲጠናከሩ አዳዲስ የማቋቋሙ ፍላጎት ከፍ እንዲል ማድረጉ፤

### 5.1.3. በአጎራባች ክልሎች ያደገ የህዝብ ለህዝብ መተሳሰብና መተማመን፤

**በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ህዝቦች ክልል እና በጋምቤላ ክልል አዋሳኝ ነዋሪዎች መካከል -** በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ህዝቦች ክልል እና በጋምቤላ ክልል አዋሳኝ አካባቢዎች በሚካሄድ ግድያ፣ ዝርፊያ፣ ህገ ወጥ የመሳሪያ ዝውውር ወዘተ… ምክንያት የተፈጠረውን የጸጥታ እጦት በዘላቂነት መቅረፍ እንዲቻል በሁለቱም ክልሎች ትኩረት ተሰጥቶ ሰፊ እንቅስቃሴ ተደርጓል፡፡ በዚህም በሁለቱም ክልሎች አዋሳኝ አካባቢዎች የሚኖረው ማህበረሰብ በየአካባቢው የጸጥታ ችግር በሆኑ ጉዮች ዙሪያ እንዲወያዩ፤ ችግሩን ነቅሰው እንዲያወጡና በመፍትሔው ላይ መግባባት እንዲደረሱና የህዝብ ለህዝብ ትስስሩን እንዲያጠናክሩ ከየአካባቢው ማህበረሰብ ተደማጭና ተጽዕኖ ፈጣሪ የአገር ሽማግሌዎች፣ የሃይማኖት አባቶች፣ ሴቶች፣ ወጣቶች ወዘተ… በድምሩ 221 (214 ወ 7 ሴ) ተመርጠው የጋራ ውይይት ማድረግ ችለዋል፡፡ በዚህም ችግሮችን በየደረጃው በመቅረፍ ረገድ ሁሉም ኃላፊነት ያለበት መሆኑንና በቀጣይ የተፈጠሩ ችግሮችን ትኩረት በመስጠት መፍታት በሚያስችሉ ስልቶች (በዕቅድ ይዞ መፈጸም፣ በአዋሳኝ አካባቢዎች ጥምር የሰላምና ጸጥታ ጥምር ኮሚቴዎችን አቋቁሞ ወደ ሥራ በማስገባት) ዙሪያ መግባባት ተደርሶ ወደ ሥራ መገባት አስችሏል፡፡ መድረኩ በየአካባቢው የሚፈጠሩ ችግሮችን በሁሉም አካላት የጋራ ርብርብ መቅረፍ እንደሚቻል፣ የህዝብ ለህዝብ ግንኙነቱ እየተጠናከረ መምጣቱ የሚታዩ ችግሮች ተቀርፈው ግንኙነቱ ቀድሞ ወደነበረበት እንዲመለስ የሚያደርግና ሊከሰቱ የሚችሉ ችግሮችን ቀድሞ በመረዳት በጋራ መቅረፍ የሚያስችል መሆኑን ግንዛቤ ተይዞበታል፡፡

በተጨማሪ የአመራርና የህዝብ ለህዝብ ግንኙነት መፈጠሩ በክልሎቹ አዋሳኝ አካባቢዎች በሚኖሩ ማህረበረሰቦች መካከል ቀድሞ የነበረው የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ግንኙነቱ ተመልሶ እንዲጠናከር አስችሏል፡፡ ከሁሉ በላይ ሁሉም የመድረኩ ተሳታፊዎች ቀጣይነት ያለው ውይይትና የህዝብ ለህዝብ ግንኙነት መኖር በማህበረሰቡ መካከል የእርስበርስ መተሳሰብና መተማመን የሚያጎለብትና ችግሮች ቢከሰቱ እንኳን በመነጋገር ብቻ መፍታት የሚያስችል መሆኑን በማመን ለተግባራዊነቱ ድርሻቸውን እንደሚወጡ መግባባት ላይ ደርሰዋል፡፡ ከውይይቱ መድረኩ በኋላም ከሁለቱም ክልሎች የተወጣጡት የሃገር ሽማግሌዎች/የሃይማኖት መሪዎች የማህበረሰቡ ባህል በሚፈቅደው ባህላዊ የእርቅ ሥነ ሥርዓት መሠረት በሁለቱ ክልል አዋሳኝ አካባቢዎች በሚኖሩ ማህበረሰብ መካከል እርቅና ማህላ በመፈጸም ቀጣይ ግንኙነታቸውን እንዲጠናከር ቃል በመግባት መድረኩ ተጠናቋል፡፡

**በአማራ ክልል እና በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል** መካከል - **በአማራ ክልል (አዊ ዞን) እና በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል (መተከል ዞን)** አዋሳኝ አካባቢዎች መካከል በተለያዩ መነሻ ምክንያቶች ግጭት ተከስቶ ግጭቱ በአካባቢው ህብረተሰብ ግንኙነት ላይ የከፋ የሚባል አሉታዊ ተጽዕና አስከትሏል፡፡ ግጭቱን ለመፍታት በየደረጃው በአመራር የተጀመረውን ጥረት በህዝብ ለህዝብ ግንኙነት ለመፍታት እንዲቻል በአዋሳኝ ወረዳና ቀበሌ ነዋሪዎች መካከል ውይይትና እርቅ መካሄዱ በህዝቡ መካከል ያለው ግንኙነት እንዲሻሻል አድርጓል፡፡ በመሆኑም በሁለቱም ክልሎች አዋሳኝ ዞንና ወረዳና ቀበሌዎች መካከል በውይይት ከተሳተፉት የህብረተሰብ ክፍሎች መካከል በህብረተሰቡ የተለዩ

በድምሩ 389 (ወንድ 346 ሴት 43) በየአካባቢያቸው ተሰሚነት ያላቸው የአገር ሽማግሌዎች፣ የሃይማኖት አባቶች፣ አርሶአደሮች፣ ሴቶች፣ ወጣቶች ወዘተ... በአማራ ክልል ቻግኒ ከተማ የህዝብ ለህዝብ ግንኙነት መድረክ እንዲዘጋጅ ተደርጓል፡፡

በመድረኩ በአዋሳኝ አካባቢ ወረዳና ቀበሌዎች የሚኖረው ህዝብ በየአካባቢው ባደረጋቸው ውይይትና የእርቅ ሥራዎች ችግሮችን የመቅረፍ ሂደቱን ማቃለሉ፤ ችግሮችን በጋራ ተቀምጦ ተወያይቶ ለመፍታት ዕድል የሰጠበትና እንዲሁም በቀጣይ የሚታዩ ችግሮችን ለመቅረፍ ዕቅድ ተዘጋጅቶና ፈፃሚው ተለይቶ በየጊዜው ክትትል እየተደረገበት እንዲሰራ የማድረግን አስፈላጊነት ትኩረት ሰጥቶ የመከረበት ነበር፡፡ በውይይቱ መጨረሻም ከሁለቱም ክልሎች የተወከሉት የማህበረሰብ አካላት ባህላዊ እርቅ ሥነ ሥርዓት መድረኩ እንዲጠናቀቅ አድርገዋል፡፡ በየአካባቢውና በጋራ ችግሮችን በመቅረፍ ዘላቂ ሰላምን ለማረጋገጥ የተጀመሩ ተግባራት በመጠናከራቸውም ህዝቡ ቀድሞ የነበረውን ግንኙነቱን እንዲያስቀጥል አስችሎታል፡፡ በአዋሳኝ አካባቢ የሚኖረው ህዝብ በግጭቱ ምክንያት የነበረው አለመተማመን ተቀርፎ መተማመን ላይ መድረስ በመቻሉ በተለይ በአዋሳኝ አካባቢዎች የሚኖሩ የማህበረሰብ ክፍሎች መካከል የነበረው የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ግንኙነትን ወደ ነበረበት እንዲመለስ ከማስቻሉም በላይ በአዋሳኝ አካባቢዎች የሚኖሩ የህብረተሰብ ክፍሎች በሰላም እንዲንቀሳቀሱና በሚካሄዱ ገበያዎች ተገኝተው እንዲገበያዩ አስችሏል፡፡

**በምስራቅ ኢትዮጵያ ተጎራባች ክልሎች የህዝብ ለህዝብ መድረክ -** አምስቱ የምስራቅ ኢትዮጵያ ተጎራባች ክልሎች(ሐረሪ፣ አፋር፣ ኦሮሚያና ሶማሌ ክልል)/ከተማ አስተዳደር(ድሬደዋ) ለዘመናት እርስበርሳቸው የተሳሰሩና አብሮ የመኖር ባህል ያላቸው፣ ችግሮች ቢከሰቱ እንኳን የተፈጠሩ ችግሮችን በመፍታት ረገድ ማህበረሰቡ ያዳበራቸውን ባህልና እሴቶችን ተጠቅሞ በመፍታት ግንኙነቱን ከማጠናከር አልፎ በአካባቢው ሰላምና ልማት እንዲረጋገጥ ያለው ፋይዳ ከፍተኛ በመሆኑ ይህም ተጠናክሮ መቀጠልና ለሌላው ምሳሌ ይሆን ዘንድ የህዝብ ለህዝብ ግንኙነት መድረክ የሰላም ሚኒስቴር ከድሬደዋ አስተዳደር ፍትሕ፣ ጸጥታና የሕግ ጉዳዮች ቢሮ ጋር በጋራ እንዲዘጋጅ ተደርጓል፡፡ በመድረኩ ከሐረሪ፣ ከድሬደዋ አስተዳደር፣ ከኦሮሚያና ከሶማሌ ክልሎች በድምሩ 284 (249 ወንድ 35 ሴት) የሃይማኖት አባቶች፣ የሃገር ሽማግሌዎች፣ ሴቶች፣ ወጣቶች፣ በአካባቢው ከሚገኙ ዩኒቨርስቲዎች በጉዳዩ ላይ ጥናት ያደረጉ ምሁራን ተሳታፊ ሆነዋል፡፡ በአካባቢው ያለውን ብዝሃነት ማስተናገድ ስለመቻሉ፣ ማህበረሰቡ በፍቅር ተሳስሮ በሰላም ለረጅም ዘመናት አብሮ እንዲኖር ያደረጋቸው ሃይማኖታዊና ባህላዊ እሴቶች አሁን ላለው ሰላምና የእርስበርስ መተሳሰብ መፈጠር ምክንያት ስለመሆናቸው ሁለት ጥናቶች በዘርፉ ዕውቀትና ልምድ ባላቸው ምሁራን ቀርቦ በመድረኩ ውይይት ተደርጎባቸዋል፡፡

የመድረኩ ተሳታፊዎች በአካባቢው የነበረውና አሁንም ያለው የእርስበርስ መተሳሰብ እንዲላላ የሚያደርጉ ችግሮች ደረጃ በደረጃ እየተቀረፉ የማህበረሰቡ ትስስር በላቀ ደረጃ በማጠናከር ለሌሎች የሀገሪቱ አካባቢዎች ምሳሌ ሊሆን በሚችል መልኩ መስራት አስፈላጊ በመሆኑ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ተግባር መሆኑን በማንሳት ግንኙነቱ ቀጣይነት እንዲኖረው፤ የአካባቢው ማህበረሰብ ያለውን የእርስበርስ መተሳሰብና ፍቅር በላቀ ደረጃ እንዲጠናከር መስራት የሚገባ በመሆኑ የሃገር ሽማግሌዎች ህብረት እንዲኖር በማድረግ ችግሮች ከመከሰታቸው በፊት በመፍታት ሰላምንና ልማትን ማረጋገጥ የሚቻልበት ምቹ ሁኔታ ቢፈጠር (ሰላም ሚኒስቴር በዚህ ላይ ድጋፉን

ቢያጠናክር)፣ በአካባቢው ያለው ሰላም እንዲረጋገጥ ሁሉም ተግቶ መስራት የሚገባው መሆኑ እንዳለ ሆኖ አካባቢው በልማት እንዲተሳሰር በሚያስችል መልኩ ትብብሩ እንዲጠናከር ቢደረግ፣ የህዝብ ለህዝብም ሆነ የክልል ክልል ግንኙነቱ መጠናከር ለአካባቢው ዘላቂ ሰላምና ልማት ወሳኝ በመሆኑ ትኩረት ተሰጥቶ እንዲሰራ ቢደረግ ወዘተ.. የሚሉ ነጥቦች በመድረኩ ተነስተውና ውይይት ተደርጎባቸዋል፡፡

**በአማራና በአፋር ክልል መካከል የተካሄደ የህዝብ ለህዝብ መድረክ** - የአማራና የአፋር ክልሎች በ8 ዞኖች፣ በ27 ወረዳዎችና በ133 ቀበሌዎችና ከ400 ኪሎ ሜትር በላይ ይዋሰናሉ፡፡ በክልሎቹ አዋሳኝ አካባቢ የሚኖሩ የህብረተሰብ ክፍሎች ጠንካራ የሆነ ባህላዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ትስስራቸው ከፍተኛ እንደሆነ ይታወቃል፡፡ በሁለቱ ክልል በአዋሳኝ አካባቢዎች የሚኖሩ ማህበረሰቦች መካከል ለዘመናት ተቻችለውና ተከባብረው የኖሩ ቢሆኑም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ከተፈጥሮ ሃብት አጠቃቀም (በውኃና ግጦሽ/እርሻ መሬት አጠቃቀም፣ በህገ ወጥ የከሰል ምርት) ፣ከእንስሳት ዘረፋ ጋር በተያያዘ፣ ህገ ወጥ የጦር መሳሪያ ዝውውር፣ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊት(ብቀላ)፣ እርስበርስ መጠራጠር፣ የተዘረፉ ንብረቶችን በወቅቱ ካለመመለስ ወዘተ… ጋር ተያይዞ በሚከሰቱ አለመግባባትና ግጭቶች የሰው ህይወት መጥፋትና ንብረት መውደም አስከትሏል፡፡ ይሁን እንጂ በአንዳንድ አዋሳኝ አካባቢዎች የሚታዩ አለመግባባትና ግጭቶች ወደ ከፋ ሁከትና ብጥብጥ ደርሰው ወደ ከፋ ደረጃ ሳይደርሱ በችግሮችና መፍትሔዎች ዙሪያ ውይይት ማካሄድ በማስፈለጉ ከሁለቱ ክልሎች፣ ከአዋሳኝ ዞንና ወረዳዎች የተመረጡ አመራር አካላት፣ የአገር ሽማገግሌዎች፣ የሃይማኖ አባቶች፣ አርብቶአደሮች፣ አርሶአደሮች፣ ሴቶች፣ ወጣቶች ወዘተ… በድምሩ 396 (ወ 386 ሴ 10 /ወጣት ወ 150 ሴት 3) ተሳታፊ የሆኑበት የህዝብ ለህዝብ መድረክ የሰላም ሚ/ር ከሁለቱ ክልሎች ሰላምና ጸጥታ ቢሮ ጋር በመተባበር ደሴ ከተማ ላይ እንዲዘጋጅ ተደርጓል፡፡

በመድረኩም በአዋሳኝ አካባቢዎች ችግሩን ለመቅረፍ በአንዳንድ ዞንና ወረዳዎች የጋራ ዕቅድ ተዘጋጅቶ ወደ ሥራ መገባቱ፣ በተወሰነ መልኩ የንብረት ምልልስ፣ የካሳ ማስከፈልና የእርቅ ሥራዎች መካሄዱ፣ በየደረጃው የአመራር ለአመራርና እንዲሁም የህዝብ ለህዝብ ግንኙነት መድረክ መዘጋጀቱ የተነሳ ቢሆንም በተሟላ ደረጃ በዕቅድ ያለመመራት፣ የተካሄዱ የአመራርና የህዝብ ለህዝብ መድረኮች ችግር ፈቺ ያለመሆን፣ ህገ ወጥ የጦር መሳሪያ ዝውውርንና የህግ የበላይነትን እንዲረጋገጥ በቅንጅትና በትብብር የመስራት ክፍተት ወዘተ… በክፍተት የተነሱና ውይይት የተደረገባቸው ጉዳዮች ናቸው፡፡ መሰል መድረኮች ተከታታይነት ባለው መልኩ መካሄዳቸው ችግሮች ሳይባባሱ ለመቅረፍ የሚያስችሉ ስለመሆናቸው፣ የአመራር ለአመራርና የህዝብ ለህዝብ ግንኙነት መድረኮችን ውጤታማ በሆነ መልኩ ተግባራዊ ማድረግ፣ ጥምር የሰላምና ጸጥታ አደረጃጀቶችን በማጠናከር ወደ ሥራ ማስገባት፣ በአካባቢው ባህልና ወግ ችግሮች እየተፈቱ እንዲሄዱ ወዘተ… መስራት አስፈላጊ መሆኑ መግባባት ላይ ተደርሷል፡፡

**በዩኒቨርስቲ ማህበረሰብ መካከል ያለው የእርስበርስ ትስሰርን ማጠናከር** - በዩኒቨርስቲዎች በትምህርት ላይ የሚገኙ ተማሪዎች ከተለያዩ አካባቢዎች የመጡ እንደመሆናቸው በመካከላቸው ያለውን ግንኙነት በማጠናከርና ትስስራቸው ጎልበቶ በሰላም ትምህርታቸውን መከታተል እንዲችሉ ማድረግ ለዩኒቨርስቲዎቹና ለአካባቢው ማህበረሰብ ያለው ፋይዳ በቀላሉ የሚታይ አይደለም፡፡ ይህን ከግንዛቤ በማስገባት ዘርፉ ከታዋቂ የኪነ ጥበብ ባለሙያዎች ጋር በጋራ በዩኒቨርስቲዎችም ሆነ

በማህበረሰቡ ለሰላም ጠንቅ የሆኑና ለአለመግባባትና ግጭት መነሻ የሚሆኑ ችግሮች ተነቅሰውና ሊያስተምሩ በሚያስችሉ ኪነ ጥበባዊ ፈጠራዎች እንዲታከልባቸው በማድረግ በተመረጡ ዩኒቨርስቲዎች "ሰላም ለሁሉም ሁሉም ለሰላም" በሚል መሪ ቃል የዩኒቨርስቲው ማህበረሰብ ራሳቸውን እያዝናኑ ትምህርት እንዲቀስሙ ማድረግ ተችሏል፡፡

ከዚህ አኳያ በአዳማ ዩኒቨርሲቲ 680 (420 ወንድ 260 ሴት)፣ ባህር ዳር ዩኒቨርስቲ 672 (394 ወንድ 278 ሴት) እና እንጅባራ ዩኒቨርስቲ 2,591 (1,359 ወንድ 1,232 ሴት) በድምሩ 3,943 (2,173 ወንድ 1,770 ሴት) የሚሆኑ የዩኒቨርስቲ ማህበራሰብ አካላት በቀረቡ ኪነጥበባዊ ተውኔት ሰላማቸውን ሊያናጉ የሚችሉ ችግሮች መንስኤ፤ ችግሮቹን በሰከነ መንገድ በማጤንና ቀድሞ በመቅረፍ በመካከላቸው ያለውን ትስስር ማጠናከር የሚያስችል አቅም መፍጠር አስችሏል፡፡ ሰላም የአንድ አካል ብቻ ሳይሆን ሁሉም ዜጎች እርስበርስ በመተሳሰብ በጋራ ተረባርበው የሚገነቡት መሆኑን ግንዛቤ መፍጠር የተቻለበት እንደሆነ ከተሰጠው ግብረ መልስ መረዳት ተችሏል፡፡

በመሆኑም በሀገሪቱ ከሚገኙ 10 ክልሎችና 2 ከተማ አስተዳደሮች መካከል ግጭት የሚሰተዋልባቸውና በመካከላቸው ያለውን ግንኙነት በተሻለ ሁኔታ እንዲያጠናክሩ በ6 ክልሎች ላይ የህዝብ ለህዝብ ግንኙነት መድረኮችን በመፍጠር በህብረተሰቡ መካከል መተሳሰብና መተማመን ለመፍጠር ታቅዶ በ6 (100%) ክልሎች ማከናወን የተቻለ ሲሆን በተጨማሪ ከእቅድ ውጪ በተመረጡ ዩኒቨርስቲዎች በዩኒቨርስቲው ማህበረሰብ መካከል የእርስበርስ ትስስርን የማጎልበት ሥራ መስራት ተችሏል፡፡ በዚህም የተገኘ ውጤት፡-

- ✓ በክልሎች አዋሳኝ አካባቢዎችና በክልሎቹ ውስጥ በሚኖሩ የህብረተሰብ ክፍሎች መካከል የሚከሰቱ አለመግባባትና ግጭቶችን በአመራርና በህዝብ ለህዝብ የጋራ ግንኙነት መድረኮች (በውይይት) ለመፍታት የሚያስችል ፍላጎትና ዝግጁነት አድጓል፣
- ✓ በተመረጡና ኪነ ጥበብን በመጠቀም እየተዝናኑ ትምህርት እንዲያገኙ በተደረጉ የዩኒቨርሲቲ ማህበረሰቦች መካከል ያለውን የእርስበርስ ትስስርን ማጠናከር የሚያስችል አቅም ተፈጥሯል፣
- ✓ ሰላም ለሁሉም በእጅጉ አስፈላጊና ሁሉም ለሰላም ባለቤት በመሆኑ የራሱን ድርሻ መወጣት እንደሚገባው ግንዛቤ የተያዘበት መሆኑ፤

### 5.1.4. በመንግስታት ግንኙነት አዋጅ ላይ ስልጠና ያገኙ አመራርና ባለሙያዎች፤

በመንግስታት ግንኙነትና በመንግስታት ግንኙነት ሥርዓት መወሰኛ አዋጅ አፈጻጸም ዙሪያ ሁሉም ክልሎች/ከተማ አስተዳደር አስፈጻሚ መ/ቤቶች ያሉበትን ሁኔታ በመረዳትና በቀጣይ በተለዩ ክፍተቶች ላይ ድጋፍ ማድረግ እንዲቻል አንድ የዳሰሳ ጥናት ማካሄድ ተችሏል፡፡

የዳሰሳ ጥናቱን ውጤት መነሻ በማድረግ በክልሎቹ/በከተማ አስተዳደሮቹ ከሚገኙ 7 ዩኒቨርስቲዎች እና ከ8 የክልል ከ2 የከተማ አስተዳደር የሰላምና ጸጥታ ቢሮዎች ጋር ውይይት በማድረግ የክልሎችን የአቅም ክፍተት በጋራ መሙላት በሚቻልበት ጉዳይ ላይ መግባባት ተደርሷል፡፡ በመሆኑም ከዩኒቨርስቲዎችና ከ8 የክልል ከ2 የከተማ አስተዳደር የሰላምና ጸጥታ ቢሮዎች የተወጣጡ በድምሩ 75 (64 ወንድ 11 ሴት) ባለሙያዎችን በመምረጥ የአሰልጣኞች ሥልጠና ተሰጥቷል፡፡ በፌዴራል ክልል ግንኙነት ዙሪያ ግንዛቤ ጨብጠው ወደ ተግባር መግባት እንዲችሉ

ከፌዴራል ተቋማት ለተመረጡ በድምሩ 143 (ወ109 ሴ 34) አመራርና ባለሙያዎች በመንግስታት ግንኙነት ጽንሰ ሃሳብና ማስፈጸሚያ አዋጅ እንዲሁም "**በመንግስታት ግንኙነት ጽንሰ ሃሳብና አተገባበር የፌዴራል አስፈጻሚ ተቋማት ያሉበትን ሁኔታ**" ዳሰሳ ጥናቱ ላይ ግንዛቤ እንዲጨብጡ ተደርጓል፡፡

በአሰልጣኞች ሥልጠና የተሳተፉ የዩኒቨርስቲዎችንና የክልል የሰላምና ጸጥታ ቢሮ ባለሙያዎችን አቅም በመጠቀም በድምሩ 1,263 (ወ 1,096 ሴ 167) ከፌዴራል ተቋማት፣ ከአማራ፣ ከኦሮሚያ፣ ከአፋር፣ ከሲዳማና ከደቡብ ክልል፣ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ህዝቦች ክልልና ከጋምቤላ ክልል ለተመረጡ አመራርና ባለሙያዎች እንዲሁም የማህበረሰብ ተወካዮች በፌዴራሊዝም፣ በመንግስታት ግንኙነት፣ በመንግስታት ግንኙነት ሥርዓት መወሰኛ አዋጅ፣ በህዝብ ለህዝብ ትስስር ፋይዳ ዙሪያ ግንዛቤ እንዲጨብጡ ተደርጓል፡፡

በመሆኑም በበጀት ዓመቱ በመንግስታት ግንኙነት አዋጅ ላይ 1,250 አመራርና ባለሙያዎችን ሥልጠና ለመስጠት ታቅዶ 1,406 (112.5%) (ወ 1205 ሴ 201) አመራርና ባለሙያዎችን ሥልጠና በመስጠት አቅማቸውን መገንባት ተችሏል፡፡ በዚህም የተገኘ ውጤት፡-

- ✓ በአዋሳኝ አካባቢዎች የሚፈጠሩ ችግሮችን በመፍታት ቀጣይነት ያለው ትስስር ለመፍጠር የክልል ክልል መንግስታት ግንኙነት አስፈላጊነት ዙሪያ ያለው ግንዛቤ አድጓል፤
- ✓ ክልሎች በመካከላቸው ያለውን ትስስር ለማጠናከር ፎረሞችን በማቋቋም ወደ ተግባር ለማስገባት ያለው ተነሳሽነት አድጓል፤
- ✓ ከማኅበረሰቡ የተውጣጡ የህዝቡ አካላትም በህዝብ ለህዝብ ግንኙነት ትስስራቸውን በማጠናከር ችግሮችን በውይይት ብቻ ለመፍታት የሚያስችል ግንዛቤቸው አድጓል፡፡

## 5.2. የተጠናከረ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲ ሥርዓት፤

### 5.2.1. በፌዴራሊዝም ዙሪያ የአደረጃጀትና የአሰራር ለውጥ ሊያመጡ የሚያስችሉ ጥናት

የፌዴራል አስፈጻሚ ተቋማት የተዋረድ ግንኙነትን ለመረዳት የሚያስችል "**በመንግስታት ግንኙነት ጽንሰ ሃሳብና አተገባበር የፌዴራል አስፈጻሚ ተቋማት ያሉበትን ሁኔታ**" በሚል ርዕስ አንድ ጥልቅ ጥናት በራስ ኃይል በፌዴራል ተቋማት ላይ ያተኮረ እንድ ጥናት ማዘጋጀት ተችሏል፡፡

የዘርፉን የባለሙያዎች ቡድን በማሰማራት በሁሉም ክልሎች/ከተማ አስተዳደሮች 4 ዳሰሳ ጥናቶች (ነባር የክልል ክልል መንግስታት ግንኙነት ያሉበትን ሁኔታ፣ ተደጋጋሚ ግጭት በሚከሰትባቸው አዋሳኝ አካባቢዎች ያሉበትን ሁኔታ፣ የፌዴራልና የክልል ተቋማት በፌዴራሊዝምና በመንግስታት ግንኙነት ያላቸውን ግንዛቤ፣ በአርብቶአደር አካባቢዎችና ከፊል አርብቶአደር አካባቢዎች በተመረጡ ከተሞች የአቅም ክፍተት ዙሪያ) መረጃ የማሰባሰብ፣ የማደራጀት፣ የመተንተንና ለሥራ በሚመች መልኩ የጥናቱ ሰነድ ተዘጋጅቷል፡፡ የዳሰሳ ጥናቶቹ የሥራ ዘርፉ በዕቅድ ለሚያከናውናቸው ተግባራት እንደመነሻ ሆነው እንዲያገለግሉ ተደርጓል፡፡

በመሆኑም በበጀት ዓመቱ በፌዴራሊዝም ዙሪያ የአደረጃጀትና የአሰራር ለውጥ ሊያመጡ የሚያስችሉ 4 የዳሰስና 2 ጥልቅ ጥናቶችን ለማካሄድ ታቅዶ 4 የዳሰሳና 1 ጥልቅ ጥናት (83.3%) ማካሄድ ተችሏል፡፡ በዚህም የተገኘ ውጤት፡-

- ✓ በዳሰሳ ጥናት ሂደት የባለሙያዎች አቅም ጎልብቷል፡፡
- ✓ በመንግስታት ግንኙነት በተለይ በተዋረድ ግንኙነት የፌዴራል ተቋማት ያሉበትን አጠቃላይ ሁኔታና ያሉባቸውን የእውቀት፣ የአመለካከትና የክህሎት ክፍተት ለመሙላት የሚያስችል ግንዛቤ ተፈጥሯል፡፡

### 5.2.2. በፌዴራሊዝም ጽንሰ ሃሳብና አተገባበር ላይ የተገነባ ማህበረሰባዊ አቅም፤

የማህበረሰቡን አቅም በፌዴራሊዝም፣ በፌዴራሊዝምና ዴሞክራሲ፣ በመንግስታት ግንኙነት ወዘተ… ዙሪያ በመገንባት ለፌዴራል ሥርዓት መርሆዎች ተገዢ እንዲሆን ከማድረግ አኳያ የተለያዩ ስልቶችን ተግባራዊ ማድረግ ተችሏል፡፡

**ሥልጠናዎችን** በማካሄድ አቅም በመገንባት ረገድ ከ7 ዩኒቨርስቲዎች፣ ከ8 የክልልና ከ2 የከተማ አስተዳደር የሰላምና ጸጥታ ቢሮዎች ጋር እና እንዲሁም ከፎረም ኦፍ ፌዴሬሽን ጋር በጋራ በመቀናጀት የክልል፣ የተለያዩ ተቋማትና የሰላም ሚ/ር አመራርና ባለሙያዎች በፌዴራሊዝምና በመንግስታት ግንኙነት፣ በግጭት አፈታትና በሰላም ግንባታ ዙሪያ በድምሩ 195 (ወንድ 141 ሴት 54) ተሳታፊዎች የአሰልጣኞች ሥልጠና ተሰጥቷል፡፡ በሥልጠና የተሳተፉ አሰልጣኞችን በመጠቀም በፌዴራሊዝም ጽንሰ ሃሳብና አተገባበር ዙሪያ ለፌዴራል ተቋማት፣ ለአማራ፣ ለኦሮሚያ፣ ለአፋር፣ ለሲዳማ፣ ለደቡብ ብ/ብ/ብ/ክ፣ ለደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያና ጋምቤላ ክልሎችና እንዲሁም ለ5ቱ የምስራቅ ኢትዮጵያ ተጎራባች ክልሎች/ከተማ አስተዳደር አመራር፣ ባለሙያዎች እንዲሁም የህብረተሰብ ክፍሎች 1,211 (ወንድ 1,064 ሴት 147) ግንዛቤ እንዲጨብጡ ተደርጓል፡፡ በመሆኑም የአሰልጣኞች ሥልጠና ባገኙትና በሌሎች ምሁራን በተሰጠ ሥልጠና በድምሩ 1,451 (ወ 1,241 ሴ 210) አመራርና ባለሙያዎ አቅማቸው እንዲገነባ ተደርጓል፡፡

**አውደ ጥናቶችን** አዘጋጅቶ የህብረተሰቡን ግንዛቤ ከማስፋት አኳያ **"ፌዴራሊዝምና ሰላም ግንባታ በኢትዮጵያ"** በሚል መነሻ ሃሳብ በድምሩ 116 (111 ወንድ 15 ሴቶች) በማህበረሰቡ ዘንድ ተጽዕኖ ፈጣሪዎች የሆኑ የማህበረሰብ አንቂዎች፣ በሚኒስትሪም ሚዲያው አርታኢዎች፣ ታዋቂ ደራሲያን፣ ታዋቂ የኪነጥበብ ባለሙያዎችን ያሳተፈ የውይይት መድረክ ተዘጋጅቷል፡፡ በመድረኩም ሰፊ ልምድና እውቀት ያላቸው ምሁራንን በመጠቀም ተሳታፊዎች ከነባራዊው ሃገራዊ እውነታ ጋር የተጣጣሙ እውቀትን እንዲጨብጡና በማህበረሰቡ ውስጥ የሚፈጥሩት ተጽዕኖም ከእውነታው ጋር የተጣጣመ እንዲሆን ለማድረግ ጥረት ተደርጓል፡፡

በሰላም ሚኒስቴር፣ ሰላም ሚ/ር ከጀስቲስ ፎር ኦል እና ከዴስቲኒ ኢትዮጵያ ጋር በጋራ **"በጥላቻ ንግግርና ሐሰተኛ መረጃ ሥርጭት"** ዙሪያ ከሰላም ሚ/ር፣ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ ከፍትህ ሚ/ር፣ ከተለያዩ ሚዲያ ተቋማት (ሜይንስትሪምና ማህበራዊ ሚዲያ)፣ ከክልል ማስታወቂያ ቢሮዎች፣ ከሙያ ማህበራት፣ ከሃይማኖት ተቋማት፣ ከሴቶች የሙያ ማህበራት የተውጣጡ በድምሩ 283 (201 ወንድ 82 ሴት) ተሳታፊ የሆኑበት አውደ ጥናት ተዘጋጅቶ ግንዛቤ እንዲጨበጥበት ተደርጓል፡ ፡ በመድረኩ የተሳተፉ ባለሙያዎች በሀገራችን የጥላቻ ንግግርና የሐሰተኛ መረጃ ስርጭት

እያስከተለ ያለውን ጉዳትና የጥላቻ ንግግርና የሐሰተኛ መረጃ ስርጭትን ለመከላከልና ለመቆጣጠር በወጣው አዋጅ ዙሪያ ግንዛቤ በመጨበጥ በቀጣይ የህብረተሰቡን ግንዛቤ በማስፋት ረገድ የበኩላቸውን ድርሻ ለመወጣት እንደሚሰሩ መግባባት ላይ ተደርሷል፡፡

በፌዴራሊዝም፣ በመንግስታት ግንኙነትና በሰላም ግንባታ ዙሪያ ያለውን ግንዛቤ በማሳደግ ለፖሊሲ ግብዓት የሚሆኑ ሃሳቦች ማመንጨት የሚያስችል **"ፌዴራሊዝም፣የመንግስታት ግንኙነት እና የሰላም ግንባታ በኢትዮጵያ"** በሚል ርዕስ የሰላም ሚ/ር ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ከፌደራሊዝምና አስተዳደር ጥናት ማዕከል ጋር በመተባበር አገር አቀፍ ኮንፍረንስ አካሂዷል፡፡ በኮንፍረንሱ ፌዴራሊዝምና ህገ መንግስታዊነት ለሰላም ግንባታው ያለው አስተዋጽኦ፣ ፌዴራሊዝም የሰላም ግንባታ በኢትዮጵያ፣ በግጭትና ሰላም የሃይማኖት ሚና፣ የክልላዊ መንግስታት ትብብርና የሰላም ግንባታ በተለይ በኦሮሚያና በሶማሌ፣ የማዕድን ሃብት አስተዳደር እና በሰላም ላይ ያለው ተጽዕኖ በኢትዮጵያ ፌዴራል ሥርዓት በሚሉ ርዕሶች ዙሪያ ጥናታዊ ጽሁፎች በዘርፉ ምርምር ባደረጉ ምሁራን የቀረቡ ሲሆን ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ ከፌዴሬሽን ምክር ቤት፣ ከተወካዮች ም/ቤት፣ ከፎረም ኦፍ ፌዴሬሽን፣ ከውጭ ጉዳይ ጥናት ኢንስቲቲዩት፣ ከፖለቲካ ፓርቲዎች፣ ከፖሊሲ ጥናት ተቋም፣ ከሰላም ሚ/ር የተጋበዙ ምሁራንና ባለሙያዎች ተሳታፊ ሆነዋል፡፡ አገራዊ ኮንፍረንሱ በርዕሰ ጉዳዮቹ ዙሪያ እያጋጠሙ ያሉ ችግሮችን ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ በመለየት የመፍትሔ ሐሳቦች እንዲቀርቡ ከማድረጉም በላይ የጥናት ውጤት የሆኑ የአሰራር ማሻሻያዎች፣ አዳዲስ ሃሳቦች፣ የሌሎች የፌደራል ሃገራት ተሞክሮዎች ከሀገራችን ነባራዊ ሁኔታዎች ጋር ተጣጥሞ መተግበር የሚቻልበትን ሁኔታ ለመጠቆም አስችሏል፡፡ ኮንፍረንሱ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በቀጣይ የሚያከናውናቸውን ተግባራት በጥናትና ምርምር ላይ እንዲመሰረት ለማድረግ ከትምህርትና ምርምር ተቋማት ጋር የሚኖረውን ግንኙነት ያጠናከረ ነበር፡፡

**የመገናኛ ብዙሃንን በመጠቀም** የህብረተሰቡን አቅም ከመገንባት አንፃር **ከደቡብ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ድርጅት** ጋር በመተባበር በፌዴራሊዝም፣ በመንግስታት ግንኙነት፣ በህዝብ ለህዝብ ግንኙነት ችግሮችን መፍታት እና በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ህዝቦችና በጋምቤላ ክልል አዋሳኝ አካባቢዎች ያለውን አለመግባባትና ግጭት በአመራር ለአመራር/ በህዝብ ለህዝብ ግንኙነት በመፍታት በአካባቢዎቹ ባህል መሠረት እርቅ እንዲወርድ በማድረግ በማህበረሰቡ መካከል የነበረው ግንኙነት ተጠናክሮ ወደ መተማመን ደረጃ እንዲደርስ የተከናወኑ ተግባራትን ከሚመለከታቸው የፌዴራልና የክልል አመራር ውይይት በቀጥታ ሥርጭት እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡ እንዲሁም በድርጅቱ አማካኝነት የተለያዩ ፕሮግራሞች ተሰርተውና ዶክመንተሪ ተዘጋጅቶ ህብረተሰቡ ግንዛቤ እንዲጨብጥበት ተደርጓል፡፡ ፕሮግራሙ በሬዲዮ፣ በቴሌቪዥንና በማህበራዊ ትስስር ገጾች ወዘተ… እንዲቀርብ ተደርጎ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ህዝቦችና በጋምቤላ ክልል አዋሳኝ አካባቢዎች ለህዝብ ተደራሽ በመደረጉ ባጠቃላይ 500 ሺ የህብረተሰብ ክፍሎች ግንዛቤ ማስጨበጥ አስችሏል፡፡

**ከአማራ ሚዲያ ኮሙዩኒኬሽንና ከኢዜአ** ጋር በመተባበር በአማራና ቤ/ጉሙዝ ክልሎች (አዊና መተከል ዞንና ወረዳዎች) አዋሳኝ አካባቢዎች የነበረው ግጭት ለመፍታት በየደረጃው የተደረጉ ጥረቶች፤ የተፈጠረው ሰላም ዘላቂ ለማድረግ እየተከናወኑ ያሉ ተግባራት፣ የተገኘው ሰላም በክልሎቹና በህብረተሰቡ መካከል የነበረው ግንኙነቱ እንዲቀጥል ማድረጉ፤ በተለይ ቀድሞ በማህበረሰቡ መካከል የነበረው ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ግንኙነት (የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት

አገልግሎቶችን በጋራ የመጠቀምና የገበያ ልውውጥ) እንደገና መጀመሩና ይህ ጅምር በህዝብ ለህዝብ ግንኙነት ተጠናክሮ እንዲቀጥል ከሁለቱም ክልል የተወከሉ የማህበረሰብ መሪዎች በጋራ ያካሄዱትን የሰላምና የአብሮነት ውይይት፣ ባህላዊ የእርቅ ሥነ ሥርዓት በሚዲያ አካላቱ እንዲቀረጽ ተደርጓል፡፡ ይህው የህዝብ ለህዝብ ግንኙነትና ያስገኘው ለውጥ በወቅታዊ ዜናና እንዲሁም በዶክመንተሪ ተዘጋጅቶ ለህብረተሰቡ እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡ በዚህም በሁለቱም ክልሎች አዋሳኝ አካባቢዎችና በየዞኖቹ የሚኖረው ለሚዲያዎቹ ተደራሽ የሆነው በአጠቃላይ ከ500 ሺህ ህዝብ በላይ የሆነ የህብረተሰብ ክፍል ግንዛቤ እንዲጨብጥ ተደርጓል፡፡

በፌዴራሊዝምና መንግስታት ግንኙነት ላይ የተዘጋጁ **በራሪ ወረቀቶች በዘርፉ እውቀትና ሰፊ ልምድ ባላቸው ምሁራን እንዲዘጋጅና** 130,000 በራሪ ወረቀት እንዲታተም ተደርጓል፡፡ በራሪ ወረቀቱን በመጠቀም የፌዴራልና የክልል ተቋማት አመራርና ባለሙያዎንና እንዲሁም የማህበረሰቡን ግንዛቤ ማስፋት እንዲቻል በተለያዩ መድረኮች፣ በፌዴራልና ክልል ተቋማትና እንዲሁም ማህረበሰቡ በሚገኝበት ቦታዎች ሁሉ እንዲሰራጭ በማድረግ በድምሩ 100,000 ሰዎች ግንዛቤ እንዲጨብጡ ማድረግ ተችሏል፡፡

በበጀት ዓመቱ በፌዴራሊዝም ጽንሰ ሃሳብና አተገባበር ዙሪያ 1.2 ሚሊዮን የተለያዩ የማህበረሰብ አካላትን አቅም ለመገንባት ታቅዶ በተደረገ እንቅስቃሴ በድምሩ 1,101,850 (91.8%) መድረስ ተችሏል፡፡ በዚህም የተገኘ ውጤት፡-

- ✓ በየክልሎቹ የሚገኙ ዩኒቨርስቲዎችን በመጠቀም የክልሎችን ክፍተት መሠረት ባደረገ መልኩ አቅም ለመገንባት ዕድል ፈጥሯል፤
- ✓ በፌዴራሊዝምና መንግስታት ግንኙነት ጽንሰ ሃሳብና አተገባበር ዙሪያ የክልል አመራር፣ ባለሙያዎች እንዲሁም የህብረተሰብ ክፍሎችን ግንዛቤ ማሳደግ አስችሏል፡፡
- ✓ የአውደ ጥናቶቹ ተሳታፊዎች በፌዴራሊዝምና መንግስታት ግንኙነት፣ በጥላቻ ንግግርና ሃሰተኛ መረጃ ሥርጭት ወዘተ… ዙሪያ ግንዛቤያቸው እንዲያድግ በማድረጉ የሚሰሯቸውን ሥራዎች በእውቀት ላይ እንዲመሰረት አስችሏል፡፡

### 5.2.3. የመግባባት ዴሞክራሲ /Consociational Democracy ባህል እንደ አማራጭ ወስዶ በመቀመርና በተቀመረው ተሞክሮ ላይ ለሊሂቃን ስልጠና በመስጠት ያደገ ግንዛቤ

የመግባባት ዴሞክራሲ/Consociational Democracy ጽንሰ ሀሳብና የሌሎች ሀገራትን ተሞክሮ በማጥናትና ከሃገራችን ነባራዊ ሁኔታ ጋር ተጣጥሞ በዘርፉ እውቀትና ልምድ ባላቸው ምሁራን እንዲቀመር ተደርጓል፡፡ በመግባባት ዲሞክራሲ/Consociational Democracy ዙሪያ ተቀምሮ የተዘጋጀው ተሞክሮ በግብዓት ዳብሮ የምሁራን፣ የፖለቲካ መሪዎችን፣ ሊሂቃኑን ወዘተ… ግንዛቤ ማሳደግ የሚያስችል ሰነድ ሆኖ እንዲወጣ በዘርፉ እውቀትና ልምድ ባላቸው የዩኒቨርስቲ ምሁራንና ባለሙያዎች የተሳተፉበት መድረክ በማዘጋጀት እንዲገመገምና ሃሳብ እንዲሰጥበት በማድረግ 1(100%) ሰነድ ማዘጋጀት ተችሏል፡፡

በተዘጋጀውና በግብዓት በዳበረው የመግባባት ዴሞክራሲ/Consociational Democracy ሰነድ ዙሪያ የምሁራንን፣ የፖለቲካ መሪዎችን፣ የሊሂቃንን ወዘተ… ግንዛቤ በማስፋት አማራጭ የዲሞክራሲ ባህልን መገንባት አስፈላጊ በመሆኑ በድምሩ 85 (ወ 63 ሴ 22) ተጋባዥ ምሁራን፣ የፖለቲካ ፓርቲ መሪዎች፣ ሊሂቃንና የተቋማት አመራርና ባለሙያዎች የተሳተፉበት ሁለት መድረኮችን

በማዘጋጀት ግንዛቤ የማስጨበጥ ሥራ መስራት ተችሏል፡፡ በዚህም በዕቅድ የተያዘው ሙሉ በሙሉ ማከናወን ተችሏል፡፡  በመሆኑም  በመግባባት ዴሞክራሲ ባህል ዙሪያ የሌሎችን ሀገራት ተሞክሮ የሚያሳይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሰነድ ተቀምሮ እንዲዘጋጅ ተደርጓል፡፡ የመግባባት ዴሞክራሲ ባህል በሃገራችን እንደ አማራጭ እንዲወሰድ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች መሰራት መጀመሩ የተገኙ ውጤቶች ናቸው፡፡

;

## III. በብሔራዊ ተሃድሶ ኮሚሽን የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት

<u>የቅድመ ዝግጅት ስራዎች</u>

- ኮሚሽኑ በአዋጁ የተሰጡትን ተግባርና ሃላፊነቶች ለማስፈፀም እንዲችል ኮሚሽኑን በበላይነት ከሚመራው ብሄራዊ የተሃድሶ ም/ቤት (ካውንስል) አባል መ/ቤቶች (ከሰላም½ የስራና ክህሎት½ ሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ½ ጤና½ ትምህርትና ገንዘብ ሚኒስቴር) የተውጣጡ የኮሚሽኑ አደራጅ ቴክኒክ ኮሚቴ እንዲደራጅ ተደርጓል፡፡

- በተባበሩት መንግስታት የልማት ፕሮግራም በኩል በመስኩ ዕውቀትና ልምድ ያላቸው አማካሪዎች እንዲመደቡ ተደርጓል፡፡ በነዚህ አካላት እገዛ የኮሚሽኑ ድርጅታዊ መዋቅርና የሰው ሃብት ፍላጎት እንዲሁም የስራ መዘርዝር ተዘጋጅቶ በምክር ቤቱ ይሁንታ ካገኘ በኋላ ለሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ቀርቦ ጸድቋል፡፡ በዚህ መሰረት የዳይሬክተሮችና የቁልፍ ሥራ መደቦች ባለሙያዎች ቅጥር በማከናወን ወደ ስራ እንዲገቡ ተደርጓል፡፡

- በሌላ በኩልም Demobilizations and Reintegration ፕሮግራም ማዕቀፍ ተዘጋጅቷል፡፡ ይህ የፕሮግራም ማዕቀፍ ከUNDP በተገኘ የቴክኒክና የባለሙያ ድጋፍ እንዲሁም ኮሚሽኑን ለማደራጀት ከተቋቋመው የቴክኒክ ኮሚቴ ጋር በቅንጅት የተዘጋጀ ረቂቅ ሰነድ ነው፡፡ ዓላማውም ዝርዝር የፕሮጀክቶች እና ዓመታዊ ዕቅዶች ለማዘጋጀት የመነሻ ሰነድ ከመሆኑም በላይ የDDR መርሃ ግብር የሚያስፈልገውን ሀብት ለማሰባሰብ (Resource Mobilization) በሁለት scenarios የተዘጋጀ አጠቃላይ የሀብት ፍላጎት ያመላከተ ሲሆን የብሄራዊ ተሃድሶ ም/ቤት አባላት ይሁንታቸውን ሰጥተዋል፡፡

- ኮሚሽኑን ዓላማና የዝግጅት ምዕራፍ ስራዎችን ለማስተዋወቅ የፌዴራልና የክልል ከፍተኛ አመራች፣ መንግስታዊ ያልሆኑ የልማት አጋሮች፣ የሲቪክ ማህበራት፣ የግሉ ሴክተርና የሚዲያ አካላት በተገኙበት የአንድ ቀን አገር አቀፍ የምክር መድረክ በመቀሌ ከተማ ተካሂዷል፡፡ ከመቀሌ ምክክር በመቀጠል በሰባት ክልሎች ማለትም በአማራ፣ አፋር፣ ኦሮሚያ፣ ቤኒሻንጉል/ጉሙዝ በተናጠል እና ደቡብ ብ/ብ/ህ፣ ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ እና ጋምቤላ ህዝቦች ጋር የፕሮግራም ግንዛቤ ማስጨበጫ የጋራ ምክክሮች ተካሂደዋል፡፡

- ከተለያዩ ኤምባሲዎችና ዓለም አቀፍ አጋር ባለድርሻ አካላት ጋር በጋራ መስራትና ድጋፍ ለማሰባሰብ የሚያስችሉ ውጤታማ ውይይቶችን በማካሄድ የጋራ ግንዛቤ መፍጠር ከመቻሉም በላይ ለስራ አስፈላጊ የሆኑ ግብዓቶችን ከUNDP ጠረጴዛና ወንበሮች እና 2 ተሽከርካሪዎች እንዲሁም ከIOM 2 ተሽከርካሪዎች፣ 5 ላፕቶፖች፣ 10 ታብሌቶች በድጋፍ መልክ የማሰባሰብ ስራዎች ተከናውነዋል፡፡ እንዲሁም ለቢሮ አገልግሎት የሚውል ህንጻ ኪራይ የተፈጸመ ሲሆን ግብዓት የማሟላት ስራዎች እየተከናወኑ ይገኛሉ፡፡

- የተሃድሶ ኮሚሽን የማቋቋሚያ ደንብ የማስፈጸሚያ መመሪያ ላይ የማስተካከያ አስተያየቶች ተሰጥተው ከታረመ በኃላ ለምክር ቤቱ ቀርቦ በተጨማሪ አስተያየቶች እንዲዳብር ተደርጓል::

- የሥራውን ባህሪይ ለማስገንዘብና ቅንጅት ለመፍጠር እንዲያስችል በአደረጃጀት፣ የሥራ ኃላፊነትና ተግባር እንዲሁም በዲሞቢላይዜሽንና መልሶ ማቋቋም ፕሮግራም ይዘት ላይ ለኮሚሽኑ ሠራተኞች የ3 ቀን የግንዘቤ መስጨበጫ ሥልጠና ተሰጥተል፡፡ እንዲሁም ከ40 ላላነሱ የብሔራዊ ተሃድሶ ኮሚሽን ሠራተኞችና ባለድርሻ አካላት በኢጋድ በድህረ ግጭት አመራር፡ በዲሞቢላይዜሽንና መልሶ ማቋቋም የ5 ቀን ሰፊ ሥልጠና ተሰጥቷል፡፡

## የዋና ዋና ተግባራት ስራዎች

- የአገር መከላከያ ሚኒስቴርን ሎጂስቲክስ በመጠቀም በትግራይ ለሚገኙ የቀድሞ ተዋጊዎች ብር 2.3 ቢሊየን የሚያወጣ የአይነት ድጋፍ እንዲደርስ ተደርጓል፡፡

- በመቀሌ በህዋሃትና በመከላከያ መካከል በተደረገው የረጅም ጊዜ ምክክር የተወሰኑ የቡድን መሳሪያዎች ርክክብ እንዲፈጸም ተደርጓል፡፡

- በመቀሌ ኩሓ ካምፕ ለሚገኙ ከ3000 ላላነሱ የቀድሞ ተዋጊዎች በጦርነት አውዳሚ ገጽታዎችና በሰላም ፋይዳዎች እንዲሁም በመልሶ ማቋቋም ፕሮግራም ይዘት ላይ የግንዛቤ ማስጨበጫና የስነልቦና ግንባታ ሥልጠና ተከናውኗል፡፡

- የቀድሞ ተዋጊዎች የመረጃ ማሰባሰቢያ DREAM DATA BASE በዝርዝር ተገምግሞ ለፕሮግራሙ በሚሆን መልኩ የማዳበር ሥራ ተከናውኗል፡፡

- የቀድሞ ተዋጊዎችን የተጣራ መረጃ ከክልሎች ለማሰባሰብ በተደጋጋሚ መድረክ የግንዛቤ ማስጨበጫ ውይይቶች ተካሂደዋል፡፡ የተገኘውንም መረጃ ከመከላከያ መረጃ ጋር በመነፃፀር የማስተካከያ ሥራዎች ተሰርተው ለምክር ቤቱ ውሳኔ ቀርቧል፡፡ በዚህ መሰረት ምክር ቤቱም በመከላከያና በክልሎች በቀረበው መረጃ መሠረት እንደመነሻ እንዲያገለግል የ371,971 የቀድሞ ተዋጊዎች ቁጥር ሥራ ላይ እንዲውል ተቀባይነት አግኝቷል፡፡

- በመጀመሪያ ዙር 75,000 የቀድሞ ተዋጊዎችን መልሶ ለማቋቋም የሚያስችል የፕሮግራምና የበጀት ፍላጎት ዕቅድ ተዘጋጅቶ ከዓለም ባንክና ከሌሎች እርዳታ ሰጪ ድርጅቶች ሀብት ለማፈላለግ እንዲያስችል ለገንዘብ ሚ/ር ተልኳል፡፡

- በሌላ በኩል ለመልሶ ማቋቋሚያ ሊውሉ የሚችሉ 10 የካምፖች ልየታ የተከናወነ ሲሆን በነዚህ ካምፖች ላይ ያሉትን ክፍተቶች የማወቅ ስራ በተቋሙ እና ከአጋር አካላት ጋር በቅንጅት እየተሰራ ይገኛል፡፡

## IV. በአፈጻጸም ሂደት ያጋጠሙ ተግዳሮቶች፣ የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች እና የቀጣይ ምቹ ሁኔታዎች፤

### ሀ. ያጋጠሙ ተግዳሮቶች፤

- ✓ የታጠቁ ሃይሎች የሚፈጥሩት ችግር በሃገሪቱ ሰላም እንዳይሰፍን ማድረጉ፣

- ✓ በግጭት ምክንያት የተፈናቀሉ ዜጎች መበራከት እና ወደ ቀያቸው ለመመለስ አስቸጋሪ መሆኑና ለሰላም ግንባታ ስራ ፈታኝ መሆኑ፤

- ✓ የኢትዮጵያ ወንጌል አማኞች አቢያተ ክርስቲያናት ካውንስል በፈቃድ ላይ ፈቃድ የመስጠት ስራ በሃይማኖት ተቋማት እና አመራሮች መካከል አገልግሎት አሰጣጥ ላይ ተግዳሮት መሆን፡፡

- ✓ የሰላም ብሄራዊ በጎ ፈቃድ አገልግሎት እስከ ክልል የራሱ አደረጃጀት መዋቅር አለመኖር፣ የስልጠና ማዕከል አለመኖር፣ በአንዳንድ የክልል አመራሮች ለስራው በቂ ትኩረት አለመስጠት፣ በአንድ አካባቢዎች የጸጥታ ችግር በመኖሩ ሰልጣኞች ከቦታ ቦታ በነጻነት አለመንቀሳቀስ፤

- ✓ የዳሰሳ ጥናቶችን በማካሄድ ረገድ መረጃዎችን በሚፈለገው መልኩ ማግኘት ያለመቻል፣ ክልሎች መረጃ ለመስጠት ፍቃደኛ አለመሆንና መደበቅ፣

- ✓ በክልሎች በቅደመ ማስጠንቀቂያና ፈጣን ምላሽ ላይ የሚሰሩ በቂ የሰለጠነ የሰው ኃይልና የተደራጀ የሁኔታ መከታተያ ክፍሎች አለመኖሩ፣ በክልሎች ፈጣን ምላሽ አለመስጠት፤

- ✓ ለተቋሙ ከተሰጠው ተልዕኮ አንጻር የተመደበው በጀት በቂ ያለመሆን፣ ለአብነት የበጎ ፈቃድ አገልግሎት በጀት ዝቅተኛ በመሆኑ ሰልጥነው የሚሰማሩ በጎ ፈቃደኞችን መቀነስ፤

- ✓ አሁን ላይ ልዩ ሃይልን መልሶ ከማደራጀት ጋር ተያይዞ በአማራ ክልል የተፈጠረው ውጥረት፤

- ✓ የሰላም ሚኒስቴር ተልዕኮውን በተሻለ መልኩ ለመወጣጥ እና ትርጉም ያለው ስራ ተቀናጅቶ ለመስራት ተጠሪ ተቋማት የሌለው መሆኑ፣

- ✓ የበጀት እጥረት፣ አጋር አካላት የበጀት ድጋፍ ለማድረግ ቃል ከገቡ በኂላ ምላሽ አለመስጠት፤

## ለ. የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች፤

- ✓ ችግር በሌለባቸው ክልሎች ላይ በተናጠል ተግባራቶችን በጋራ መፈጸም ተችሏል፡፡

- ✓ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ስልጠናና ስምሪትን በተቻለ አቅም ከክልሎችና ከዩኒቨርሲዎች ጋር በጥምረት እየተሰራ መሆኑ፡፡

- ✓ የተሟላ መረጃ ለማሰባሰብ ጥረት መደረጉ፤ መረጃዎችን ከተለያዩ ምንጮችን በመዳሰስ ለመጠቀም ሙከራ መደረጉ፤

- ✓ የግጭት ቅድመ ማስጠንቀቂ ላይ ሚሰሩትን ባለሙዎች ስልጠና በመስጠት በተቻለ መጠን መረጃዎችን መሰብሰብና መተንተን መቻሉ፡
- ✓ በተወሰነ ደረጃ ከአጋር አካላት ተጨማሪ ሃብት የማፈላለግ ስራ መስራት፤

## V. ማጠቃለያ፤

ተቋሙ ለዝግጅት ምዕራፍ ሰፊ ጊዜ በመስጠትና የ2015 በጀት ዓመት ዕቅድን በተሻለ ሁኔታ በማቀድ በሁሉም ደረጃ አመራርና ፈጻሚን የማዘጋጀት ስራ አከናውኗል። እንዲሁም ለዋና ዋና ስራዎች ትኩረት በመስጠት ተግባራዊ ሲደረግ ቆይቷል። በተለይም በሰላም ግንባታ፣ በብሔራዊ መግባባት፣ በግጭት አስተዳደርና በመንግስታት ግንኙነት ዙሪያ የተሻለ ስራዎችን ለመስራት በልዩ ሁኔታ ፕሮግራምና ፕሮጀክቶችን በመቅረጽ ተግባራዊ ለማድረግ ቅድመ ዝግጅት ቢጠናቀቅም በበጀት እጥረት ምክንያት ወደ ተግባር መግባት አልተቻለም። ስለሆነም በቀጣይ የዝግጅት ምዕራፍ እና ከባለፈው ዓመት የተንጠባጠቡትን ስራዎች ጨምሮ የተቋሙን ተልዕኮ ሊያሳኩ የሚችሉ ተግባራት በልዩ ትኩረት የሚተገበሩ ይሆናል።

## VI. የሰላም ዘርፍ የዋና ዋና ግቦች አፈጻጸም፤

| ተ.ቁ | ስትራቴጂክ ግቦች፣ ዋና ዋና ተግባራት እና ዝርዝር ቁልፍ የአፈፃፀም አመልካቾች | ክብደት | መለኪያ | የ2014 (መነሻ) | የ2015 ዕቅድ | ክንውን | አፈጻጸም በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ተቋማዊ የማስፈጸም አቅም፣ የሀብት አጠቃቀም እና የአገልግሎት አሰጣጥ አሰራር ማጎልበት (ክብደት = 15) | | | | | | |
| 1.1 | የዕቅድ ዝግጅት፣ የክትትልና ግምገማ እና የስታቲስቲክስ መረጃ አስተዳደር አሰራር ማሻሻል (ክብደት = 1) | | | | | | |
| 1.1.1 | ወቅቱንና ጥራቱን የጠበቀ ዕቅድና ሪፖርት ሰነድ ማዘጋጀት | 0.4 | በቁጥር | 5 | 5 | 5 | 100 |
| 1.1.2 | የክትትልና ግምገማ ስርዓት መዘርጋት | 0.3 | በቁጥር | 3 | 4 | 4 | 100 |
| 1.1.3 | የዘርፉን መረጃ አያያዝ በቴክኖሎጂ በመደገፍ ማደራጀት | 0.3 | በመቶኛ | | 50 | 48 | 96 |
| 1.2 | የሰው ሀብት ልማት እና አስተዳደር አሰራርና ውጤታማነት ማሳደግ (ክብደት = 2) | | | | | | |
| 1.2.1 | ግልጽነት የሰፈነበት የሰው ኃይል ስምሪት ማካሄድ | 0.5 | በመቶኛ | 94 | 100 | 100 | 100 |
| 1.2.2 | ለአመራር እና ለሰራተኞች የሚሰጡ ሥልጠናዎችን ማሳደግ | 0.5 | በቁጥር | 13 | 17 | 17 | 100 |
| 1.2.3 | የውስጥ የማበረታቻ ስርዓት መዘርጋት | 0.5 | በቁጥር | 1 | 3 | 2 | 67 |
| 1.2.4 | የሰራተኛ እርካታን በማሳደግ ፍልሰትን መቀነስ | 0.5 | በመቶኛ | 10 | 5 | 2.7 | 100 |
| 1.3 | የፋይናንስና ንብረት አስተዳደር አሰራርንና ውጤታማነትን ማሳደግ (ክብደት = 3) | | | | | | |
| 1.3.1 | የተመደበ በጀት በአግባቡ ሥራ ላይ ማዋል (ድርሻ) | 0.5 | በመቶኛ | 90 | 95 | 99 | 100 |
| 1.3.2 | ነቀፌታ ያለበትን የኦዲት ግኝት መቀነስ | 0.5 | በመቶኛ | 40 | 20 | 25 | 75 |
| 1.3.3 | የመንግስት ኤሌክትሮኒክ ክፍያን ድርሻ ማሳደግ | 0.5 | በመቶኛ | 60 | 85 | 85 | 100 |
| 1.3.4 | የመንግስት ኤሌክትሮኒክ ግዢን ድርሻ ማሳደግ | 0.5 | በመቶኛ | 20 | 55 | 50 | 90 |
| 1.3.5 | መሰረታዊ አገልግሎትን በቅልጥፍና በመስጠት የደንበኞችን እርካታ ማሻሻል | 0.5 | በመቶኛ | 70 | 90 | 75 | 83 |
| 1.3.6 | የንብረት አያያዝ እና የጥገና ወጪዎችን መቀነስ | 0.5 | በብር | | 5ሚ | 5ሚ | 100 |
| 1.4 | የኢንፎርሜሽን፣ኮሙኒኬሽን እና ቴክኖሎጂ አሰራርንና ውጤታማነትን ማሳደግ (ክብደት = 2) | | | | | | |
| 1.4.1 | መረጃ ቋት ማደራጀት | 0.4 | በመቶኛ | | 50 | 48 | 96 |
| 1.4.2 | በተቋሙ ወረቀት አልባ አሰራርን መተግበር | 0.3 | በመቶኛ | 25 | 75 | 65 | 80 |
| 1.4.3 | በተቋሙ የሚሰጠ አገልግሎቶችን ኦቶሜት ማድረግ | 0.3 | በመቶኛ | 30 | 60 | 58 | 94 |
| 1.4.4 | የተገልጋዮችን እርካታ ደረጃ ማሳደግ | 1 | በመቶኛ | 70 | 80 | 75 | 93.75 |
| 1.5 | የአጋርነት እና የህዝብ ግንኙነት አሰራርንና ውጤታማነትን ማሳደግ (ክብደት = 1) | | | | | | |
| 1.5.1 | ለተቋም አቅም ግንባታ በሀገር ውስጥ አጋርነት የተገኘ ድጋፍ | 0.25 | በብር | | 10ሚ | 7.7ሚ | 77 |
| 1.5.2 | ለተቋም አቅም ግንባታ በውጭ ሀገር አጋርነት የተገኘ ድጋፍ | 0.25 | በብር | 18 ሚ | 50ሚ | 39.2ሚ | 78.4 |
| 1.5.3 | መረጃዎችን በተለያዩ የተግባቦት ዘዴዎች ተደራሽ ማድረግ | 0.5 | በመቶኛ | 77 | 85 | 84 | 98 |

| ተ.ቁ | ስትራቴጂክ ግቦች፣ ዋና ዋና ተግባራት እና ዝርዝር ቁልፍ የአፈፃፀም አመልካቾች | ክብደት | መለኪያ | የ2014 (መነሻ) | የ2015 ዕቅድ | ክንውን | አፈጻጸም በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1.6 | **ለተጠሪ ተቋማት እና ለክልሎች ድጋፍና ክትትል ማድረግ (ክብደት = 2)** | | | | | | |
| 1.6.1 | የክልሎችን ዕቅድ ከዘርፍ ዕቅድ ጋር ማናበብና ማጣጣም | 0.5 | በቁጥር | | 1 | 1 | 100 |
| 1.6.2 | በየሩብ ዓመት ከክልሎች ጋር የዘርፍ አፈጻጸም በጋራ መገምገም | 0.5 | በቁጥር | 3 | 4 | 3 | 75 |
| 1.6.3 | ለክልሎች ወቅታዊ የአቅም ግንባታ ድጋፍ መስጠት | 0.5 | በቁጥር | | 3 | 3 | 100 |
| 1.7 | **የስነ ምግባርና ፀረ ሙስና የክትትል ሥራዎችን ማጠናከር (ክብደት = 1)** | | | | | | |
| 1.7.1 | በብልሹ አሰራር ዙርያ ጥቆማ ከተደረገባቸው ውስጥ ማስተካከያ የተደረገባቸው | 0.25 | በመቶኛ | 85 | 100 | 100 | 100 |
| 1.7.2 | ለብልሹ አሰራር የተጋለጡ አሰራሮች በጥናት በመለየት የማሻሻያ ሀሳብ ማቅረብ | 0.25 | በቁጥር | 3 | 3 | 2 | 67 |
| 1.7.3 | የሀብት ምዝገባ ያካሄዱ አመራሮች እና ባለሞያዎች ድርሻ ማሳደግ | 0.5 | በመቶኛ | 100 | 100 | 100 | 100 |
| 1.8 | **የሴቶችና ማሕበራዊ ተሳታፊነትንና ተጠቃሚነትን ማሳደግ (ክብደት = 1)** | | | | | | |
| 1.8.1 | የህጻናት ማቆያ አገልግሎት ተጠቃሚ ሴት ሰራተኞች ብዛት ማሳደግ | 0.25 | በቁጥር | 2 | 10 | 8 | 80 |
| 1.8.2 | ወደ አመራር የመጡ ሴት ሰራተኞች ብዛት ማሳደግ | 0.25 | በቁጥር | 8 | 10 | 7 | 70 |
| 1.8.3 | ሥልጠና ያገኙ ሴት ሰራተኞች ድርሻ ማሳደግ | 0.25 | በመቶኛ | 51 | 100 | 100 | 100 |
| 1.8.4 | ለአካል ጉዳተኛ ሰራተኞችና ተገልጋዮች ምቹ የስራ ሁኔታና ቦታ መፍጠር | 0.25 | በመቶኛ | 80 | 90 | 90 | 100 |
| 1.9 | **የበጎ አድራጎት እና የማህበረሰብ አገልግሎት ሥራዎችን ማሳደግ (ክብደት = 2)** | | | | | | |
| 1.9.1 | የአረንጓዴ አሻራ ተግባራትን ማካሄድ/ችግኞችን መትከል | 0.5 | በቁጥር | 5,000 | 6,500 | 5,500 | 84.5 |
| 1.9.2 | የአቅመ ደካማ ማህበረሰቦች የመኖሪያ ቤቶች መገንባት | 0.15 | በቁጥር | 17 | 10 | 27 | 100 |
| 1.9.3 | የአቅመ ደካማ ማህበረሰቦች የመኖሪያ ቤቶች መገንባት | 0.15 | በብር | 3.6ሚ | 2ሚ | 2.4 ሚ | 100 |
| 1.9.4 | የአቅመ ደካማ ቤተሰብ ተማሪዎች ድጋፍ | 0.15 | በቁጥር | 100 | 100 | 100 | 100 |
| 1.9.5 | የአቅመ ደካማ ቤተሰብ ተማሪዎች ድጋፍ | 0.15 | በብር | 100 ሺ | 100ሺ | 100 ሺ | 100 |
| 1.9.6 | ለተለያዩ ማህበራዊ ቀውሶች የተደረገ ድጋፍ | 0.3 | በብር | 62ሚ | 5ሚ | 5ሚ | 100 |
| 1.9.7 | የተደረገ ደም ልገሳ (ድርሻ ከሰራተኛ ብዛት) | 0.3 | በሰው | 30 | 50 | 50 | 100 |
| 1.9.8 | ወላጆቻቸውን ያጡ ህፃናትን መደገፍ | 0.15 | በቁጥር | 15 | 15 | 15 | 100 |
| 1.9.9 | ወላጆቻቸውን ያጡ ህፃናትን መደገፍ | 0.15 | በብር | 81ሺ | 81ሺ | 81 ሺ | 100 |
| 2 | **አዎንታዊ ሰላም ማሳደግ (ክብደት = 25)** | | | | | | |
| 2.1 | **በአዎንታዊ ሰላም ግንባታ ያደገ የሃይማኖት ተቋማት ተሳትፎና የአገልግሎት አሰጣጥ (ክብደት = 10)** | | | | | | |
| 2.1.1 | በሃማኖት ተቋማቶች ፍላጎት መሰረት በተደረገ ድጋፍ ያደገ የሃይማኖት ተቋማት ውስጣዊ ሰላም | 2 | በመቶኛ | 75 | 85 | 70.55 | 83 |

| ተ.ቁ | ስትራቴጂክ ግቦች፣ ዋና ዋና ተግባራት እና ዝርዝር ቁልፍ የአፈፃፀም አመልካቾች | ክብደት | መለኪያ | የ2014 (መነሻ) | የ2015 ዕቅድ | ክንውን | አፈጻጸም በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 2.1.2 | ለሃማኖት ተቋማቶች በተሰጠ ድጋፍ ያደገ የሃይማኖት ተቋማቶች የእርስ በእርስ መቻቻል | 2 | በመቶኛ | 70 | 85 | 72.25 | 85 |
| 2.1.3 | የጎለበተ የመንግስትና የሃይማኖት ተቋማት መልካም ግንኙነት | 2 | በመቶኛ | 75 | 85 | 64.6 | 76 |
| 2.1.4 | የሃይማኖት ተቋማት በህብረተሰብ ሰላም ግንባታ ያላቸው ተሳትፎና ሚና ማሳደግ | 2 | በመቶኛ | 65 | 75 | 67.5 | 90 |
| 2.1.5 | ለሀይማኖት ተቋማት የተሰጠ የፈቃድ ምዝገባ፣ እድሳትና ተጓዳኝ አገልግሎት | 2 | በመቶኛ | 85 | 95 | 80 | 90 |
| **2.2** | **በማህበረሰብ ተሳትፎ ያደገ አዎንታዊ ሰላም (ክብደት = 15)** | | | | | | |
| 2.2.1 | በማህበረሰብ ምክክር ያደገ የዜጎች ሰላማዊነትና ችግር ፈቺነት | 5 | በመቶኛ | 81 | 85 | 79.9 | 94 |
| 2.2.2 | በመንግስት ሰራተኞች ምክክር ያደገ የተቋማትና የሰራተኞች ሰላማዊነት ምጣኔ | 5 | በመቶኛ | | 50 | 25 | 50 |
| 2.2.3 | የሰላም አደረጃጀቶች (ክበባት፣ ፎረሞች እና ሌሎች) ለአዎንታዊ ሰላም ያበረከቱት አስተዋጽኦና ውጤታማነት | 5 | በመቶኛ | 84 | 87 | 85 | 97.7 |
| **3** | **የሀገር መንግስት ግንባታን ማጎልበት (ክብደት = 15)** | | | | | | |
| **3.1** | **በበጎፈቃደኞች ተሳትፎ የጎለበተ ህብረ-ብሄራዊ አንድነት (ክብደት = 8)** | | | | | | |
| 3.1.1 | ከየክልሉ ተመልምለው የበጎ ፈቃደኝነት ስልጠና የወሰዱና ያጠናቀቁ ሰልጣኞች | 2 | በቁጥር | 16,618 | 25,000 | 14,774 | 59 |
| 3.1.2 | በተሰጠ ስልጠና የበጎ ፈቃደኞች አገራዊ አመለካከት ለውጥ እድገት | 1 | በመቶኛ | 55 | 70 | 61.17 | 87 |
| 3.1.3 | ከስልጠና በኋላ ከክልላቸው ውጭ ተሰማርተው አገልግሎት የሰጡ በጎ-ፈቃደኞች | 2 | በቁጥር | 16,203 | 25,000 | 18,934 | 75 |
| 3.1.4 | በጎ ፈቃደኞች በተሰማሩበት አካባቢ የሰጡት ማህበራዊ አገልግሎቶችና የሰላም ስራዎች | 2 | በመቶኛ | 60 | 80 | 76.8 | 96 |
| 3.1.5 | በጎ-ፈቃደኞች በቆይታቸው ወቅት ከተሰማሩበት አካባቢ ያገኙት የህይወት ልምድና ግንዛቤ | 1 | በመቶኛ | 60 | 90 | 85.6 | 95 |
| **3.2** | **ለህብረ- ብሔራዊ አንድነትና ብሔራዊ መግባባት እድገት የዋሉ ድልብ ማህበራዊ ሃብቶች (ክብደት = 3)** | | | | | | |
| 3.2.1 | ከሠላምና ሀገር ግንባታ አንፃር አዎንታዊ እሴቶችና አሉታዊ ልማዶችን መለየት | 1 | በሰነድ | - | 1 | 1 | 100 |
| 3.2.2 | በተለዩት አዎንታዊ እሴቶችና አሉታዊ ልማዶች ላይ የተፈጠረ የጋራ ግንዛቤ | 1 | በመቶኛ | - | 50 | 40 | 80 |
| 3.2.3 | የተለዩ አዎንታዊ እሴቶች ስርጸት | 1 | በመቶኛ | - | 50 | 40 | 80 |

| ተ.ቁ | ስትራቴጂክ ግቦች፣ ዋና ዋና ተግባራት እና ዝርዝር ቁልፍ የአፈፃፀም አመልካቾች | ክብደት | መለኪያ | የ2014 (መነሻ) | የ2015 ዕቅድ | ክንውን | አፈጻጸም በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 3.3 | **በልሂቃን ተሳትፎ ያደገ ብሔራዊ መግባባት (ክብደት = 4)** | | | | | | |
| 3.3.1 | ዋና ዋና አገራዊ ጥቅሞችን፣ አገራዊ መገለጫዎችና ህዝባዊ ፖሊሲዎችን በጥናት መለየት | 1 | በሰነድ | | 3 | 3 | 100 |
| 3.3.2 | በሃገራዊ አጀንዳዎች ላይ ሊሂቃንን በማወያየት ያደገ የልሂቃን መግባባት | 1 | በመቶኛ | - | 40 | 37 | 92.5 |
| 3.3.3 | የዋና ዋና አገራዊ ጥቅሞችና አገራዊ መገለጫዎች ስርጸት | 2 | በመቶኛ | | 60 | 50 | 83 |
| 4 | **የግጭት ተጋላጭነትን መቀነስና ግጭት የማስተዳደር አቅምን ማሳደግ (25)** | | | | | | |
| 4.1 | **በማዕከል፣ በክልሎች እና ከተማ አስተዳደሮች የተናበበ የቅድመ ግጭት ሁኔታ መከታተያ ክፍል በማደራጀት ግጭትን አስቀድሞ መከላከል (ክብደት = 12)** | | | | | | |
| 4.1.1 | በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈ የቅድመ ማስጠንቀቂያ ሥርዓት ሽፋን | 6 | በመቶኛ | 20 | 73 | 66 | 90 |
| 4.1.2 | ፈጣን ምላሽ ያገኙ የቅድመ ማስጠንቀቂያ መረጃዎች ምጣኔ | 4 | በመቶኛ | - | 80 | 70 | 88 |
| 4.1.3 | በተሰጠ ፈጣን ምላሽ የተደረሰ መግባባትና ማስቀረት የተቻለ ግጭት መጠን | 2 | በመቶኛ | - | 70 | 69 | 99 |
| 4.2 | **ወደ ዘላቂ ሰላምና ልማት የተሸጋገሩ የግጭት ቀጣናዎች (ክብደት = 9)** | | | | | | |
| 4.2.1 | በግጭት ምክንያት የሚከሰቱ የሰብዓዊ ቀውስና የንብረት ውድመት መረጃ ማሰባሰብና መተንተን | 1 | በሰነድ | 1 | 1 | 1 | 100 |
| 4.2.2 | በተሰበሰበ መረጃና በተደረገ ትንተና መሰረት ዜጎች ድጋፍ እንዲያገኙ የተደረገ ማስተባበር | 1 | በመቶኛ | | 80 | 70 | 88 |
| 4.2.3 | የድህረ ግጭት ቀውስ አካል የሆነውን የስነ ልቦና ስብራትና አለመረጋጋት ችግር ለመፍታት ለተጎዱና ለተፈናቀሉ ዜጎች የተሰጠ ስልጠናና ወደ ሰላማዊ ኑሮ የተሸጋገሩ ዜጎች | 3 | በቁጥር | 3 | 4 | 6 | 100 |
| 4.2.4 | ወደ አንጻራዊ ሰላማዊነት የተሸጋገሩ የግጭት ቀጠናዎች | 4 | በመቶኛ | - | 40 | 35 | 88 |
| 4.3 | **የተጠናከሩና ጥቅም ላይ የዋሉ ሀገር-በቀል የግጭት አፈታት ስርዓት (ክብደት = 4)** | | | | | | |
| 4.3.1 | ሀገር-በቀል የግጭት አፈታት ስርዓትን በጥናት መለየት | 1 | በሰነድ | - | 1 | 1 | 100 |
| 4.3.2 | በተለዩ ሀገር-በቀል የግጭት አፈታት ስርዓት ላይ የተፈጠረ የጋራ ግንዛቤ | 2 | በመቶኛ | 50 | 80 | 80 | 100 |
| 4.3.3 | ሀገር-በቀል የግጭት አፈታት ስርዓት እንዲፈታ የተደረገ አለመግባባቶችና ግጭቶች | 1 | በቁጥር | | 1 | 2 | 100 |
| 5 | **የፌደራል ሥርዓቱን እና የመንግስታት ግንኙነትን ማጠናከርና ማሳደግ(ክብደት = 20)** | | | | | | |
| 5.1 | **የተጠናከረ የፌዴሬሽን አባል መንግስታት እና የማህበረሰብ ግንኙነት (ክብደት = 10)** | | | | | | |
| 5.1.1 | የፌዴራል-ክልል እና ክልል-ክልል ግንኙነቶችን ለማጠናከር የተካሄዱ የግንኙነት መድረክ | 3 | በቁጥር | 10 | 12 | 15 | 100 |

| ተ.ቁ | ስትራቴጂክ ግቦች፣ ዋና ዋና ተግባራት እና ዝርዝር ቁልፍ የአፈፃፀም አመልካቾች | ክብደት | መለኪያ | የ2014 (መነሻ) | የ2015 ዕቅድ | ክንውን | አፈጻጸም በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 5.1.2 | የመንግስታት ግንኙነቶችን ለማሳለጥ የተደራጁና የተቋቋሙ አዳዲስና ነባር ፎረሞች | 2 | በቁጥር | 3 | 6 | 6 | 100 |
| 5.1.3 | በአጎራባች ክልሎች ያደገ የህዝብ ለህዝብ መተሳሰብና መተማመን | 3 | በመቶኛ | - | 60 | 70 | 100 |
| 5.1.4 | በመንግስታት ግንኙነት አዋጅ ላይ ስልጠና ያገኙ አመራርና ባለሙያዎች ብዛት | 2 | በቁጥር | 818 | 1,250 | 1406 | 100 |
| **5.2** | **የተጠናከረ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት (ክብደት = 10)** | | | | | | |
| 5.2.1 | በፌዴራሊዝም ዙሪያ የአደረጃጀትና የአሰራር ለውጥ ሊያመጣ የሚያስችል ጥናት ማካሄድ | 3 | በሰነድ | 1 | 6 | 5 | 83.3 |
| 5.2.2 | በፌደራሊዝም ፅንሰ-ሀሳብና አተገባበር ላይ ያደገ ማህበረሰባዊ አቅም | 3 | በመቶኛ | | 80 | 91.8 | 91.8 |
| 5.2.3 | የሌሎች ሃገራት የመግባባት ዴሞክራሲ ባህል ተሞክሮን ከሃገራችን ነባራዊ ሁኔታ ጋር ማጣጣም | 2 | በሰነድ | - | 1 | 1 | 100 |
| 5.2.4 | በተቀመረ የመግባባት ዴሞክራሲ ተሞክሮ መሰረት ለሊሂቃን ስልጠና በመስጠት ያደገ ግንዛቤ | 2 | በመቶኛ | - | 90 | 100 | 100 |